አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ

በ
ዓለሙ ካሣዬ

ለ ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረ-ምረቃ ትምህርት ቤት
በቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት
የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ድህረ-ምረቃ መርሃ-ግብር

አዲስ አበባ፣ ሰኔ 1999 ዓ.ም

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት
በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረ-ምረቃ ትምህርት ቤት
በቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት
የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር

ለ 'ኤም.ኤ.ዲግሪ' ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ

በ
ዓለሙ ካሣዬ

አማካሪ፡ ዘሪሁን አስፋው

አዲስ አበባ፣ዩኒቨርሲቲ
ሰኔ 1999 ዓ.ም

ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት

በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ

በ

ዓለሙ ካሣዬ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት
የድኅረ-ምረቃ መርሐ-ግብር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ

ፈታኝ

ፈታኝ

ፊርማ

ፊርማ

ፊርማ

ምሥጋና

ከሁሉ በፊት ጥናቱ በዚህ መልኩ ይዘጋጅ ዘንድ ጊዜያቸውን እና የዳበረ እውቀታቸውን ተጠቅመው የተሳተው እንዲታወስ፣ የጐደለው እንዲሟላ፣ የተዛባው እንዲቃና፣ ያጠረው እንዲረዝም፣ የተንዛዛው እንዲመጠን ላደረጉልኝ አማካሪዬ አቶ ዘሪሁን አስፋው የላቀ አክብሮት አለኝ።

አድካሚውን የጽህፈት ሥራ ሳትሰለች ለሠራችልኝ ወ/ሮ አበራሽ የሱፍ የማይዘነጋ እና ወደር የሌለው ውለታም ምሥጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤትም የጥናቱን ወጪ ስለሸፈነልኝ አመሰግናለሁ።

ገጽ

ር ዕ ስ

ምሥጋና I
ማውጫ II
አጠቃለሎ V

1. መግቢያ
1.1. የጥናቱ አቀራረብ 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 2
1.3. የጥናቱ ዳራ 2
1.4. የጥናቱ ዓላማ 3
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ 4
1.6. የጥናቱ ገደብ 4
1.7. የጥናቱ ዘዴ 4
1.7.1 ዕሞናዊ ምልከታ 5
1.7.2 ተሳትፎአዊ ምልከታ 6
1.7.3 ቃለ-መጠይቅ 6
1.7.4. እውናዊ ትውስታዎች 7
1.7.5 ቅንብር ምሰላ 7
1.8. ያጋጠመ ችግሮች 7
2. የላሎ-ማማ ምድር ወረዳ ዳራ
2.1. መልክዓ-ምድር 9
2.2. አስተዳደራዊ አወቃቀር 10
2.3. የሕዝቡ ማንነት እና የኋላ አመጣጥ 11
2.3.1. ከአሀን ምልከታ አኳያ 11
2.3.2. ከአፈ-ታሪክ አኳያ 12
2.3.3. ከታሪክ አኳያ 12
2.4. ማኅበራዊ ገፅታ 14
2.4.1. የትምህርት ሽፋን 14
2.4.2. የጤና ሽፋን 15

2.4.3. እምነት 15
2.4.4. ጋብቻ 19
2.4.4.1. የጋብቻ ቅድመ-መስፈርት 19
2.4.4.2. የጋብቻ አጠያየቅ እና አፈጻጸም 20
2.5. ስም አሰያየም 23
2.6. የሥራ ባህል 25
2.7. አሰፋፈር እና የቤት አሰራር 28
2.8. ኢኮኖሚያዊ ገጽታ 29
2.8.1. አመጋገብ 30
2.8.2. አለባበስ 31
2.9. ዓለማዊ አተያይ 33
3. የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት
3.1. የግጭት ምንነት 35
3.2. የግጭት መንስኤዎች 38
3.3. የግጭት ዓይነቶች እና ደረጃዎች 40
3.4. የግጭት አፈታት ሥልቶች 41
3.4.1. ሽምግልና ይቅርታ እና እርቅ 43
3.4.2. ሽምግልና ይቅርታ እና እርቅ በቀልን ከማስቀረት አኳያ 45
3.5. የኢትዮጵያ ሕጐች የግጭት አፈታት ተሞክሮ 45
3.6. የላሎ-ማማ ወረዳ ግጭት ምንነት ተግባራዊ ብያኔ 47
3.7. በላሎ-ማማ ሕዝብ ሕይወት ዙሪያ እና በባህላዊ የግጭት አፈታት ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች ክለሳ.. 48
3.7.1. በ'ሶሻል አንትሮፖሎጂ' የትምህርት መስክ የተደረጉ ጥናቶች ክለሳ. 48
3.7.2. በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር የትምህርት መስክ የተደረጉ ጥናቶች ክለሳ 51
4. የላሎ-ማማ ምድር ነዋሪዎች ግጭት እና የግጭት አፈታት ሥርዓት
4.1. የላሎ-ማማ ምድር ነዋሪዎች ግጭት መንስኤዎች 59
4.2. ቅድመ-ግድያ 63
4.3. ድህረ-ግድያ 64
4.4. የላሎ-ማማ ምድር ነዋሪዎች ግጭት አፈታት 65
4.4.1. የአገር ሽማግሌነት እና ሽምግልና 68
4.5. ቅድመ - እርቅ 70
4.5.1. የደም ግጭት እርቅ ጥያቄ አቀራረብ 70
4.5.2. የደም ግጭት እርቅ አመላለድ 74

4.5.3. የደም እርቅ ድርድር ሂደት 78
4.5.4. የደም እርቅ ሥርአተ-አፈፃፀም 79
4.6. ድህረ- እርቅ 89
4.7. ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓቱ ወቅታዊ ሁኔታ 89
5. ማጠቃለያ
የተጠቀሱ ምንጮች..... 95
አባሪ አንድ፤ ቁልፍ /አውራ/ የመረጃ ተባባሪዎች ዝርዝር..... 100
አባሪ ሁለት፤ የአገር ሽማግሌዎች ማንነት መግለጫ..... 101

አጠቃሉ

የዚህ ጥናት አነሳስ የላሎ-ማማ ምድር ወረዳ ነዋሪዎች የሚጋጩበትን እና ግጭታቸውን የሚፈቱበትን ባህላዊ ተቋም፣ ሥርዓት እና ዘዴ ለመመርመር ነው። በመሆኑም ጥናቱ የላሎ-ማማ ምድር ነዋሪዎች የሚጋጩባቸውን እና ግጭቶቻቸውን የሚፈቱባቸውን ባህላዊ የሽምግልና እና እርቅ ሂደት ይገልፃል፣ ይተነትናል። ገለጻው እና ትንተናው የተደረገውም የተለያዩ የመስክ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችንና ማለትም ዕሞናዊ ምልከታን፣ ተሳትፎአዊ ምልከታን እና ቃለ-መጠይቅን በመጠቀም ነው።

በተለይ ከአገር ሽማግሌዎች ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሠረትም ግለሰቦች በምጣኔ ሀብት ውሱንነት ወይም እጥረት፣ በአስተሳሰብ እና አመለካከት፣ ተግባቦት አለመጣጣም፣ በእምነት ማጉደል፣ ሥርቆት ዘረፋ፣ ማንነት፣ ማኅበራዊ ደረጃ፣ በመልካም አስተዳደር እጦት፣ በቂም በቀል ምክንያት ግጭት ይፈጥራሉ። ግጭት ሲፈጠርም በተለያዩ ደረጃ /በቤተሰብ፣ በአካባቢ፣ በኃይማኖት አባቶች፣ በሽማግሌዎች እና በአገር ሽማግሌዎች/ ተሸማግለው ይፈታሉ።

ጥናቱ በተለይም ትኩረት ሰጥቶ የደም ግጭት እርቅ ጥያቄ የሚቀርብበትን ሂደት ያመለክታል። በጥናቱ ግኝት መሠረትም የእርቅ ጥያቄው በገዳይ በራሱ፣ በገዳይ ወገኖች፣ በሟች ወገኖች፣ በገዳይ እና በሟች ወገኖች፣ በአገር ሽማግሌዎች ተነሳሽነት የሚቀርብበት ሁኔታ አለ።

የደም ግጭቱን ማቆሚያ እና ማስማሚያ ዘዴውም የተለያዩ ነው። ብዙውን ጊዜ ገዳይ መንዝን፣ አንዳንድ ጊዜም ወረዳውን ብቻ እንዲለቅ ይደረጋል። እጅግ አልፎ አልፎ ደግሞ ወጅ /የደም ካሣ/ በመቁረጥ እና በማገዳደብ እርቅ ይፈፀማል። እርቁ እንዲፀናም ተገላጋዮች ጠመንጃ እየተራመዱ፣ አፈር እየጨበጡ፣ ሽንጥ ሥጋ እየተቋረጡ፣ እርጥብ ሣር እየነጩ፣ መስቀል እየጨበጡ የመሐላ ቃል ይሰጣሉ። እነዚህን መሐላዎች ማክበርም በተለያዩ ስያሜዎች ማለትም የአባት፣ የአገር፣ የወንዝ አደር ወይም ዕድር/ ይላላል/ "አዳ" ማለትም ልማድ፣ ደንብ፣ ሕግ እንደመጠበቅ ይቆጠራል። ታራቂዎቹ ደመኞቹም ለዚህ ሕግ ተገዝተው ሰላም ፈጥረው ይኖራሉ።

ከዚህ በላይ ከተገለጸው የአባት፣ አገር፣ ወንዝ፣ አደር ወይም ዕድር "አዳ"/ ማለትም ልማድ፣ ደንብ፣ ሕግ፣ ማፈንገጥም "ውፀዕ፣ ጋጠወጥ፣ መልቲ፣ ነውረኛ፣ ባለጌ፣ ወዘተ" ያሰኛል። ማኅበራዊ መገለልም ያስከትላል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

1. መግቢያ

ይህ መግቢያ የጥናቱ አቀራረብ፤ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፤ ዳራ፤ ዓላማ፤ ጠቀሜታ፤ ገደብ፤ ዘዴ እና ያጋጠሙ ችግሮች የሚሉትን ያካትታል።

1.1. የጥናቱ አቀራረብ

ይህ "ባህላዊ የደም ማድረቅ ሥርዓት በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ" የተሰኘ ጥናት በአምስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው።

በምዕራፍ አንድ፤ በመግቢያው ሥር ይህን የያዝነውን የጥናቱ አቀራረብ የሚለውን ርዕስ ጨምሮ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፤ የጥናቱ ዳራ፤ ዓላማ፤ ጠቀሜታ፤ ገደብ፤ ዘዴ እና ያጋጠሙ ችግሮች የሚሉት ቀርበዋል።

የጥናቱ ምዕራፍ ሁለት የወረዳውን አጠቃላይ ገጽታ ማለትም መልክዓ ምድር፤ የሕዝቡን ማንነት፤ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ገፅታ፤ አፈ-ታሪክ እና ጽሑፍ ታሪክ ይዳስሳል። ከዚሁ ጋርም የሕዝቡን ዓለማዊ እና መንፈሳዊ አተያይ ይመለከታል።

የጥናቱ ምዕራፍ ሶስት ደግሞ ተዛማጅ ጽሁፎች የተቃኙበት ነው። በሥሩም የግጭት ምንነት፤ መንስኤዎች፤ ዓይነቶች እና ደረጃዎች እንዲሁም ዓለማቀፋዊ የግጭት አፈታት ትውሮች ተዳሰዋል። ከዚሁ ጋርም የኢትዮጵያ ሕጐች የግጭት አፈታት ተሞክሮዎች ተካተዋል። በማስከተልም ለላሎ ማማ ወረዳ ግጭት ምንነት የሚስማማ ተግባራዊ (የሥራ) ብያኔ /operational definition/ ተሰጥቷል። ምዕራፍ ሦስት የሚጠናቀቀው ግጭትን አስመልክቶ የተሰሩ ጥናቶችን በመቃኘት እና በመከለስ ነው። ይህም ክለሳ ከትምህርት ክፍሉ ውጪ በ"ሶሻል አንትሮፖሎጂ" የትምህርት መስክ የተሰሩትን እና አ-ቀጥተኛ በሆነ መንገድ በርዕሱ ዙሪያ የቀረቡትን እንዲሁም በትምህርት ክፍሉ ማለትም በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር የትምህርት ዘርፍ ተማሪዎች የተሠሩትን እና በቀጥተኛ ሁኔታ ከጥናቱ ጋር በተቀራረበ ሁኔታ የተከናወኑትን ጥናቶች ያካተተ ነው።

ምዕራፍ አራት ደግሞ የወረዳውን የግጭት ግኝት መንስኤዎች እንዲሁም የቀላል እና ከባድ ቅራኔዎች መፍቻ ዘዴዎችን አቅርቧል። በተለይም የከባድ ቅራኔ ወይም ደመኝነት መፍቻ (የሀገር ሽማግሌ፤ የቤተክርስቲያን አባቶች) ጥረቶችን እርቅ ማውረጃ እና ማስማሚያ ዘዴዎችን፤ ገደቦችን እና መደምደሚያ ወይም ማሠሪያ እና ማሳረጊያ መሐላዎችን ቃኝቷል።

የጥናቱ የመጨረሻ ክፍል የሆነው ምዕራፍ አምስት ማለትም የጥናቱ ማጠቃለያ ደግሞ የጥናቱን ግኝት አቅርቧል።

በመጨረሻም የተጠቀሱ ምንጮች እና አባሪዎች ተዘርዝረዋል።

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ላሎ-ማማ ምድር ውስጥ ነፍስ ማጥፋት ወይም ግድያ ነጋ ጠባ ይሰማል። የተለመደ ነው። የአማራ ክልል መንግሥት የፀጥታና ደህንነት ቢሮም በ1995 ዓ.ም በወረዳው "የደም አድራቂ ኮሚቴ" አቋቁሟል። ይሄም ሁኔታ ለመሆኑ እስከዛሬ ድረስ ግጭቱ በምን ይፈታ ነበር? የሚል ጥያቄ እንዳነሳ እና ሁኔታውም አሳሳቢ እየሆነ የመጣበትን ምክንያት እንድመረምር ገፋፍቶኛል። ይህንን የማወቅ ፍላጐቱም የመነጨው የወረዳውን ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት የሚመለከት ጥናት ያልተደረገ በመሆኑ እና በሌሎች አካባቢዎች ከተካሄዱት የግጭት አፈታቶችም የተለየ የግጭት መፍቻ ተቋም፣ ሥርዓት እና ዘዴ ሊኖር ይችል ይሆናል በሚል መላምት ክፍተቱን ለመመላት ነው።

በተጨማሪም በልጅነቱ አያቱ (የናቱ አባት) ደብተራ ወልደ ጊዮርጊስ በለጤ ቀን በተገን ማታ በእሳት ዳር ከተለያዩ እንግዶች ጋር እየሆኑ ስለ ጠበኞች እና ደመኞች ግልግል በሽክሽክታ እና በለሆሳስ ሲጫወቱ እሰማ ነበር። የሚነጋገሩትን ለመስማት ከነበረኝ ጉጉት እና ፍላጐት የተነሳ እንደምንም ሰበብ ፈጥሬ ሳልጠራ እየተጠጋሁ፣ እየተሻሸሁም እሰማው የነበረው "ድርድሩ ሳድሯል፣ አንቅፏል ለይደር ተቀጥሯል፣ ሰምሯል፤ እከሌ ነገሩን ተኝቼበት ልደር ከአልጋዬ እና ከዘመዴ ልምከርበት ብሏል ወዘተ" አገላለፅ አዳምጥ ስለነበር ያ ሁኔታ ዛሬ ላይ ደርሶ ነገሩን የማወቅ ፍላጐቴን ሳያነቃቃው አልቀረም።

1.3. የጥናቱ ዳራ

ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርዱ ሲዋረዱ የመጡ ልማዶች (traditions) እና ልማዳዊ ሥርዓቶች (customs) እንዲሁም እምነቶች ማለትም ኃይማኖት፣ አምልኮ (beliefs) በአጠቃላይ የጎበረተሰብ አኗኗር ዘዴ፣ ወግ፣ ሥርዓት ተዳምረው ባህል (culture) ይሆናሉ። ይህም ባህል (culture) ያደረበትን ጎበረተሰብ አስተሳሰብ፣ አድራጐት፣ ክንዋኔ ይቀነብበዋል ወይም ይቀርፀዋል። ባህልም ደግሞ ግጭትን የመቀስቀስ እና የማባባስ መልሶም የመግታት እና የመፍታት አስተዋፅዖ ይኖረዋል። ይህም ጥናት ባህል በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ ውስጥ ግጭትን፣ ፀብን እና ነፍስ መጠፋፋትን በማስከተል በአንዳንዱም እርቅን በማውረድ ረገድ ያላቸውን ተፅዕኖ (influence) በመመርመር ላይ ያተኮረ ነው።

ላሎ-ማማ ምድር ወረዳ የሚገኘው በአማራ ክልላዊ መንግሥት መስተዳደር በሰሜን ሸዋ ዞን ነው። በውስጡም አንድ መቶ ሀምሳ ሺህ የሚጠጋ ሕዝብ ይኖርበታል። ከነዋሪው

ሕዝብ ውስጥ አብዛኛው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትናን የሚከተል ሲሆን ጥቂቶች ደግሞ ሌሎቹን የክርስትና እምነቶችን እና የእስልምናን እምነት ይከተላሉ። ይህ ጥናት የሚያተኩረው በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና አማንያን ላይ ነው።

በቅርቡ ከወረዳው ፖሊስ ጽህፈት ቤት የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው ከ1997 ዓ.ም እስከ ታህሣሥ 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ብቻ አምሳ አምስት ሰዎች መገደላቸው፤ ሦስት መቶ ስድሳ አካላቸው መጉደሉ እና ግምቱ በውል ያልታወቀ የቤት ቃጠሎ፤ የንብረት መውደም የሀብት ዝርፊያ (ቅሚያ) መደረጉ ለፖሊስ ሪፖርት ተደርጓል (ረዳት ኢንስፔክተር አህመድ መሃመድ የወረዳው ፖሊስ አዛዥ በ24/5/99)። ይህም አሀዝ በየቀበሌው በሽማግሌ እና በሀገር ሽማግሌ (ሁለቱ የተለያዩ ደረጃ አላቸው) በባህላዊ መንገድ እየተፈታና እየተቀጨ እርቅ የወረደበትን በርካታ ግጭት አይጨምርም። ለናሙናነት ከተመረጡ የተወሰኑ አካባቢዎች ሽማግሌዎች እና የሀገር ሽማግሌዎች ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት እንደተቻለውም በ1998 ብቻ ከአሥር የማያንሱ የነፍስ ግድያ እና የአካል ማጉደል ግጭቶች በእርቅ ተፈተዋል (ቁስ ማሞ ጸደቀ አርሶ አደር በ7/5/99 እና አቶ ቀጥይበሉ አሳምነው አርሶ አደር በ17/5/99)። በመሆኑም ይህ "ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት በላሎ-ማማ ወረዳ" በሚል ርዕስ የተደረገ ጥናት ሕዝቡ ወደ ግጭት እና ደም መቃባት የሚገባባቸውን ምክንያቶች (ሰበቦች)፤ የግጭቶቹን ዓይነቶች እንዲሁም ግጭቱ በባህላዊ እና አካባቢያዊ በቀል ዕውቀት እየተፈታ የኖረበትን እና ያለበትን ተቋም፤ ሥርዓት እና ዘዴ ለመመርመር ያለመ ነው።

1.4. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ የላሎ-ማማ ምድር ወረዳ ሕዝብን ጥንተ-አመጣጥ፤ አኗኗር፤ እምነት፤ ዓለማዊ አተያይ(world view) እንዲሁም ፀብ ወይም ግጭት የሚያፈራበትን እና የሚፈታበትንም ተቋም፤ ሥርዓት፤ ዘዴ፤ መመርመር እና መግለጽ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘም :-

ሀ/ ላሎ-ማማ ምድር ውስጥ ፀብ ወይም ግጭት የሚቀሰቀስባቸው እና ግድያ የሚያስከትሉት የግጭት ሰበቦች ወይም ምክንያቶች ምን ምን ናቸው

ለ/ ግጭቱ የሚፈታበት ተቋም አደረጃጀት ምን ይመስላል?

ሐ/ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓቱ ምን ይመስላል

መ/ የደም እርቅ ማስማሚያው ሀሳብ እና ማገዳደቢያ ምንድነው? የእርቅ ማጽኛ ሥርዓቱስ?

ረ/ የደም ማድረቂያ እርቅ ሥርዓቱ ወቅታዊ ሁኔታስ ምን ይመስላል? ለሚሉት የምርምር ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል። ከነዚህ ጋር የተያያዙ ክንዋኔዎችንም ይዘግባል። ይሰንዳል።

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት አካባቢ፣ አፈ-ታሪክ፣ ጽሁፍ-ታሪክ፣ ሥራ ወይም ሙያ፣ የምጣኔ ሀብት ሁኔታ፣ አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ ተግባቦት በአጠቃላይም ባህል በአንድ ጎብረተሰብ አኗኗር ውስጥ ለፀብ መከሰት እና ለፀበኝነት ባህርይ መገንገን ማለትም መፋፋት ያላቸውን አሉታዊ ተዕዕኖ በአንዛሩም ደግሞ ፀብ ወይም ግጭትን ለማብረድ እና ለመፍታት ያላቸውን አዎንታዊ አበርክቶ ያስገነዝባል። የላሎ-ማማ ምድር ወረዳ ነዋሪዎች የግጭት መንስኤዎችን እና አፈታቶችንም ያሳያል። ይሄም ደግሞ ስለወረዳው ግጭት ምክንያቶች እና አፈታት ማወቅ ለሚሹ ዕውቀት ይሰጣል።

1.6. የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናት የተካሄደው በወጥ /indigenous/ እና በውሱን ወይም አነስተኛ /micro/ አካባቢ ሕዝብ መካከል በተለይም አንድ ዓይነት ባህል፣ ኃይማኖት፣ እምነት እና ልማዳዊ ሁኔታዎች በሚታዩበት ጎብረተሰብ ውስጥ ነው። በመሆኑም በሚሸፍነው አካባቢ እና ጉዳይ እጅጉን የተቀነበበ ነው። ምክንያቱም በአፅንኦት የሚዳስሰው የወረዳውን ሕዝብ ነባር ባህላዊ የግጭት እና የደም ማድረቅ ሥርዓት እና ዘዴ ነው። ስለሆነም ሌሎች ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች በእግረ መንገድ ካልሆነ በስተቀር በዝርዝር አልታዩም። ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓቱም ቢሆን ገፅታው እና አፈፃፀሙ እንጂ የተጀመረበት ዘመን፣ ያለፈበት ሂደት (ታሪክ) ሁሉ አልተካተተም። ይልቁንም በሽማግሌዎች እና በአገር ሽማግሌዎች እይታ የነበረው እና ያለው ፋይዳ አሁን ያለበት ሁኔታ ተገልጿል።

ጥናቱ ከላይ ለተጠቀሱት አፅንኦት በመስጠቱም መለስተኛ ግጭቶች የሚፈቱባቸውን ዘዴዎች የቤተሰብ፣ የአካባቢ ሽምግልና እንዲሁም ጠንቋይ (ውቃቢ፣ ቃልቻ) እና የሰፈር፣ የማኅበር (የሰንበቱ) የግልግል ዘዴዎችን በጥልቀት እና በስፋት አይዳስስም። ጥናቱ በአቢይነት የሚመለከተው ደመኝነት እና ደም መቃባትን ለማስቀረት የሚደረገውን ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት ብቻ ነው።

1.7. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ገለፃዊ (descriptive) እና ተንታኝ (analytical) ባህሪ አለው። ስለሆነም በወረዳው ውስጥ ሁለት ጊዜ የመስክ ሥምሪት አድርጌያለሁ። መጀመሪያ ከመስከረም 10/1999 ዓ.ም እስከ መስከረም 20/1999 ዓ.ም የአሰሳ ጥናት አከናውኛለሁ። እውቅ የመረጃ አቀባዮችንም አፈላልጊያለሁ። በሁለተኛው ዙር ጉዞዬ ከጥር 5 እስከ ጥር 30/1999 ዓ.ም መረጃ አቀባዮቼን በዝርዝር አነጋግሬያለሁ። የእርቅ ሥርዓቱንም በትንበር ምሰላ ዘዴ

ሰንጃለሁ። በቆይታዬም ጥናቱን ለማካሄድ የሚረዱኝን እና የሚበጁን የተመረጡ እና የተውጣጡ የመስክ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተጠቅሜያለሁ።

ለመስክ ጥናቱ ከቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ የተመረጡት ዕሞናዊ ምልከታ፤(passive observation) ተሳትፎአዊ ምልከታ (participatory observation)፤ ቃለመጠይቅ (interview) በኢ-መደበኛ (informal) እና በመደበኛ (formal) ገፅታው እና አቀራረቡ ናቸው። በቃለ-መጠይቅ ወቅት የተገኙ አንዳንድ የግጭት፣ የደም መቃባት መንስኤዎች፣ የግልግል እና እርቅ አፈፃፀም ሂደቶችም በታዋሽ እውናዊ ክስተትነት (memorable factual cases)እንዲካተቱ ተደርገዋል። እነዚህም የመረጃ መሰብሰቢያዎች የተወሰነ ማጎበረሰብን ባህል፤ልማድ እና እምነት ለማጥናት ጥቅም ላይ ይውሉ ዘንድ የሚመክሩ ዘዴዎች ናቸው(Kottak 1991፣ 23)።

በተጨማሪም ቅንብር ምሰላ (induced setting) ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። ይህን ለማድረግ ግድ የሆነውም እውነተኛ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት ለማግኘት ባለመቻሉ ነው።

በአጠቃላይ በሁሉም የመስክ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች እና ዘዴዎች የተገኙት መረጃዎችም እንደየአመቺነታቸው በማስታወሻ፣ በቴኘ፣ በቪዲዮ እና በፍቶግራፍ ተቀርፀዋል፣ ተቀድተዋል፣ ተሰንደዋልም።

ከላይ የተዘረዘሩት ድብልቅ (የተውጣጡ) የመስክ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተመረጡበትን ምክንያት አስፈላጊነት እና ጥቅም ላይ የዋሉበትን አኳኋን ቀጥዬ በዝርዝር አሳያለሁ።

1.7.1. ዕሞናዊ ምልከታ

የላሎ-ማማ ወረዳ ሕዝብ ስለ ጥንተ አመጣጡ ስለ አካባቢው፣ ስለአኗኗር ልማዱ፣ ስለ ፀብ፣ ግጭት፣ ሽምግልና እና እርቅ ያለውን አስተሳሰብ እና አገላለፅ ለማወቅ በመሃሉ ተገኝቶ መታዘብ እና መመልከት ግድ ይሆናል። ስለዚህም ዕሞናዊ ምልከታ ይህን ለማሳካት የተመረጠ አንድ ዋነኛ የመረጃ ማግኛ ዘዴ ሆኗል። ዕሞናዊ ምልከታውንም በማህበር (ሰንበቴ)፣ በእድር ቤት፣ በጅጌ (ደቦ) ሥራ ቦታ በቤተክርስቲያን እና በሽምግልና ቦታዎች ሁሉ በመገኘት ማከናወን ነበረብኝ። በዚህም ሕዝቡ እርስ በርሱ እንዴት እንደሚተያይ እንደሚግባባ ሰላምታ እና ሦፃብ እንደሚለዋወጥ ነገሮችን እንዴት እንደሚመነዝር፣ እንደሚተረጉም ወይም እንደሚበልት ለማስተዋል ችያለሁ ።

1.7.2. ተሳትፎአዊ ምልከታ

ተሳትፎአዊ ምልከታን የተጠቀምኩበት ሕዝቡ ዘና ለማለት በበዓላት እና በገበያ እንዲሁም አልፎ አልፎ በአዘቦት (በሥራ) ቀናት ጉራ በሚልባቸው ጠላ፤ አረቂ፤ ጠጅ መሸጫ (መሸታ) ቤቶች ነው። በዚህም ወቅት እንደ እንግዳም እንደ ውስጥ አዋቂም እየሆንኩ በጨዋታቸው ውስጥ አብሬ በመሳተፌ ስለአገባባቸው፤ ሰላምታ ልውውጣቸው፤ በትር (ዱላ) አያያዛቸው እና አቀማመጣቸው፤ አጠጣጣቸው፤ የሃሳብ ልውውጣቸው፤ በነገር ስለመግባባት እና አለመግባባታቸው (መጐነታተላቸው) ለማጤን እጅጉን የተመቸ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

1.7.3. ቃለ-መጠይቅ

ሦስተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ አድርጌ የተጠቀምኩት ኢ-መደበኛ (informal) እና መደበኛ (formal) ቃለ መጠይቅ ማድረግን ነው። ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃም በብዛት በማስታወሻ ተመዝግቧል። አልፎ አልፎም በቴኘ እና በቪዲዮ ተቀርጿል።

ኢ-መደበኛ ቃለ-መጠይቅን የተጠቀምኩት ጊዜ እና አጋጣሚ በፈቀደልኝ ቦታ ሁሉ ያገኘኋቸው እና ያነጋገርኳቸው ሰዎች ሁሉ ስለ ቂም በቀል ስለ ፀብ እና ግጭት ደም መቃባት እና ደመኝነት እንዲሁም ባህላዊ የደም ማድረቅ ሥርዓት ያላቸውን አስተያየት ለማወቅ እና ለማግኘት ነው። ይህንንም ዘዴ የተጠቀምኩት ተጠያቂዎቹ የሚገልፁት ሃሳብ የተጣራ ዕውቀታዊ እና ሥልጣናዊ ባይሆንም የመሰላቸውን እና የሚያውቁትን መረጃ፤ መረጃ እያቀበሉ መሆናቸውን ሳያውቁ እና ጥንቃቄ ሳያበዙ እንደልባቸው እንዲገልፁ ለማድረግ በማሰብ እና በማቀድ ነው። ይህም ዘዴ ከላይ እንደተገለፀው ብዙም ነገሮችን አበጥረውም ባይሆን በማኅበረሰቡ ውስጥ በመኖራቸው ብቻ የሚያውቁትን ያህል ለሚናገሩ በርካታ የመረጃ ተባባሪዎች (potential informants) ሃሣብ ማግኘነት የተመቸ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

መደበኛ ቃለ-መጠይቅ የተጠቀምኩት በከፊል በጥንቃቄ ለተቀረጹ እና ለተሰደሩ (semi-structured & sequenced) ጥያቄዎች አቀራረብ ነው። ይህንንም ዘዴ ለባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ-ሥርዓት ዕውቅ (ቁልፍ) የመረጃ ተባባሪዎቹ (key informants) አጠያየቅ የተጠቀምኩበት እጅጉን ጥብቅ (strict) በሆነ አቀራረብ እና መንገድ አይደለም። የጥያቄዎቹን ሥርዓታዊነት በማለዘብ እና ለሀገር ሽማግሌዎች አቀራረብ በሚያመች የአቀራረብ ሥልት ነው። በዚህም ዘዴ ከአሥር ያላነሱ የሀገር ሽማግሌዎች ስለ ፀብ ግጭት እና ደመኝነት መንስኤዎች እንዲሁም ስለ ደም ማድረቂያ እርቅ ማውረጃ ሥርዓት ልምዳቸውንና ዕውቀታቸውን አካፍለዋል። የሀገር ሽማግሌዎቹን ቁልፍ የመረጃ አቀባይ አድርጌ

የወሰድኳቸው የወረዳው ህዝብ የቸራቸውን ክበሬታ ተከትዬ ነው። በወረዳው ውስጥ ስማቸው የተጠራ ችሎታቸው የተመሰከረ የግጭት ችግር ፈቺዎች ሆነው ስላገኘኋቸው።

1.7.4. እውናዊ ትውስታዎች

እውናዊ ትውስታዎች የተባሉት የሀገር ሽማግሌዎች በመደበኛ ቃለ-መጠይቅ ወቅት ግጭት እንደተቀሰቀሰባቸው፣ ደም መቃባትንም እንዳስከተሉ እያስታወሱ የተረኳቸው የግጭት መንስኤዎች እንዲሁም የእርቅ አፈፃፀም ሥርዓት ትውስታዎች ናቸው።

1.7.5. ቅንብር ምሰላ

ይህን ቅንብር ምሰላ የተጠቀምኩት ባህላዊ የደም እርቅ ሥርዓትን በመስክ ላይ በቆየሁባቸው ቀናት ለማግኘት ለመቅረፅ፣ ለመቅዳት እና ለመሰነድ ባለመቻሉ ነው። ይህም የሆነው ደግሞ የመስክ ቆይታ ጊዜዬ በማጠሩ ሳይሆን የርዕሰ-ጉዳዩም ተፈጥሮ ስለሆነ ነው። ፀብ፣ ግጭት እና ደም መቃባት በቀጠሮ የሚደረግ፣ ወቅት የሚመረጥበት ባለመሆኑ እና የእርቅ ሥርዓቱም በዚሁ ስሌት የሚፈፀም ስለሆነ ነው። ይሁንና ተፈጥሮአዊ መቼትን ለመመልከት እና ለመሰነድ ባልተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሮአዊ የሚመስል መቼት ማለትም ቅንብር ምሰላ ማዘጋጀት እና ክንውኑን መሰነድም የሚቻል እና የተገባ ነው (ፈቃደ 1991:122-124)።

1.8. ያጋጠሙ ችግሮች

ይህ ጥናት ሲከናወን አንዳንድ ችግሮች ማጋጠማቸው አልቀረም። ችግሮቹ እዚህ የሚጠቀሱትም ችግርን ከመደርደር ልማድ በመነጨ ሳይሆን ነባራዊ ሁኔታን ከመግለፅ እና ለተመሳሳይ አጥኚዎችም የሚያጋጥሙ እንቅፋቶችን ለመጠቆም ከማሰብ ነው።

በደመኝነት የሚፈላለጉ ሰዎች (ደመኞች) እውነተኛ ባህላዊ የደም ማድረቅ ያደርጉ ዘንድ የእርቅ ጥሪ የሚደረግባቸው (የቤተክርስቲያን ደወል ማሰማትን፣ የታቦት ጃንጥላ መዘቅዘቅን፣ ታቦት ማውጣትን፣ እግዚኦታ ማሰማትን ወዘተን) ለመሰነድ አልተቻለም። ይህም የሆነው እምነቱ ያስከተለዋል ተብሎ በሚሰጋው ቁጣ ወይም "መዓት" ሳቢያ ማስመሰል ስላልተቻለ ነው።

በደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓቱ ማጠናቀቂያ ወይም መደምደሚያ ላይም እርቁ የሚታሰርባቸውን የመሐላ ሥርዓቶች /ጠመንጃ መራመድ፣ መስቀል መጨበጥ እርጥብ መንጨት፣ ጭብጥ አፈር በቤተክርስቲያን መቅበርን መመሰል አልተቻለም/። ይህም እንደላይኛው ሁሉ እምነቱ ሊያስከትለው ይችላል ተብሎ ከሚሰጋው "መዓት" እና ፍዳ በመነጨ ሁኔታ ነው።

በሕዝቡ መሀል በዕሞናዊ እና በተሳትፎአዊ ምልከታ እንዲሁም አልፎ አልፎ በኢ-መደበኛ ቃለ-መጠይቅ ወቅት ይህንን ማወቅ ለምን ፈለግህ? ምን ይጠቅምሀል? የፀባችንን፣ የመገዳደያችንን ምክንያት አውቀኸው ምን ትፈይድልናለህ? የመስማሚያችንስ ዘዴ ለምን ፈለግኸው? ወዘተ የሚል ጥያቄ እና ማንገራገርም ነበር።

በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ ውስጥ የደረሱ የረጅም ዓመታት ግጭቶችን እና ደም መፋሰሶችን አሀዞች በሰነድም ሆነ በቃል ማግኘት አለመቻልም ሌላው ችግር ነበር። ምንም እንኳን የወረዳው ፖሊስ ጣቢያ ከተቋቋመ አያሌ ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም የተመዘገቡ የነፍስ ማጥፋት ወንጀል ሰነዶችን ማግኘት አልተቻለም። ይህም የሆነው ሕዝቡም ሆነ ተለዋጮቹ መንግሥታት ማለትም ደርግ እና ኢሕአዴግ በየዘመናቸው ደርግ የጎይለሥላሴን ዘመን፤ ኢሕአዴግም የደርግን ዘመን ዶሴዎች ለመጠበቅ እና ለማስጠበቅ ባለመቻላቸው ነው።

ሌላው ችግር ደግሞ ብጤ አጥኚዎች (ተመራማሪዎች) በ1997 እና በ1998 ዓ.ም ያደረጓቸው ተከላሽ ጥናቶች በቤተመጻሕፍት ውስጥ በፍጥነት ተሰራጭተው አለመገኘ ታቸው ነበር።

በመጨረሻም ይህ ጥናት በርዕሱ እንደተመለከተው የቀረበው በትልመ-ጥናት (Proposal) ቀርቦ በፀደቀው መሠረት "ባህላዊ የደም ማድረቅ ሥርዓት በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ " በተሰኘ ርዕሱ ነው። በዚሁ ሁኔታ ጥናቱ በመካሄድ ላይ ሳለ ግን የክልሉ መንግሥት ላሎ እና ማማ ከመስከረም 1/1999 ዓ.ም ጀምሮ የተለያዩ ሁለት ወረዳዎች እንዲሆኑ ስያሜያቸውም መንዝ ማማ ምድር እና መንዝ ላሎ ምድር እንዲሆን ውሳኔ አሳልፏል። ሆኖም እኔ ጥናቱን በተወጠነበት መንገድ ለማዘለቅ ተገድጃለሁ። ይህንንም ያደረግሁት በላሎ-ማማ ወረዳ ስም ተሰልተው፣ ተደራጅተው እና ተካተው የተገኙ መረጃዎችን ሁሉ መሰንጠቅ (መክፈል) አዳጋች ስለሆነብኝ ነው።

2. የላሎ-ማማ ምድር ወረዳ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ የላሎ-ማማ ምድር መልክዓ-ምድር፣ አስተዳደራዊ አወቃቀር፣ የሕዝቡ ማንነት ከአሁን፣ ከአፍ እና ከጽሁፍ ታሪክ አኳያ ይገለፃል። ማኅበራዊ ገጽታው ይቃኛል። የሕዝቡ የሥራ ባህል፣ ኢኮኖሚያዊ ገፅታ እና ዓለማዊ አተያይ ይማተራል።

2.1. መልክዓ-ምድር

ላሎ-ማማ ወረዳ 1,080,045 (አንድ ሚሊዮን ሰማንያ ሺህ አርባ አምስት ሄክታር) ስፋት አለው። ከባህር ወለል ያለው ከፍታ ከዘጠኝ ሺህ እስከ አሥራ ሶስት ሺህ ጫማ እንደሚደርስ ይገመታል (አቶ ኃይሉ አሸቱ የወረዳው ግብርና ጽ/ቤት ባለሙያ በ22/5/99)። ላሎ-ማማን በሰሜን መንዝ ጌራ-ምድር፣ በሰሜን ምሥራቅ ኤፍራታና ግድም በደቡብ ሞጃና ወደራ፣ በደቡብ ምሥራቅ ጣርማ በር፣ በምሥራቅ ቀወት፣ በምዕራብ መንዝ-ቀያ ገብርኤል ወረዳዎች ያዋስኑታል።

የላሎ ማማ ምድር ካርታ

ምንጭ: የላሎ ማማ ምድር ወረዳ ጽ/ቤት

የመሬቱ አቀማመጥ አምባማ (highland plateau) የሚባለው ዓይነት ነው። አንዳንድ የ"ጂአግራፊ" መምህራን "The table land of Menz" እያሉ ይጠሩታል። ላሎ-ማማ፣ መንዝ እየተባለ የሚጠራው አካባቢ ደቡባዊ ክፍሉ ነው። ተራራ፣ ኮረብታ፣ ሸለቆ፣ ገደላ-ገደል፣ ዳገት፣ ቁልቁለት ይበዛበታል። ድንጋያማም ነው። በወረዳው ውስጥ ትናንሽ ወንዞች ይበዛሉ። ብዙዎቹም ወደምዕራብ ይፈሳሉ። ከእነዚህም መካከል ወረዳውን ከጌራ-ምድር

ወረዳ የሚለየው ዘንቻ እንዲሁም በውስጥ ማማን ከላሎ የሚለየው ረትመት፤ ላሎ-ማማን ከሞጃና ወደራ ወረዳ የሚለየው ሞፈር ውኃ፤ እና ጀማ፤ እንዲሁም ሌሎች ቀበሌን ከቀበሌ የሚለዩ፤ በየቀበሌውም ሥርጓጉጥ ውስጥ የሚፈሱ ትናንሽ ወንዞች እና ጅረቶች ወደ አዳባይ ይገባሉ። አዳባይም ወደ አባይ። ወደ ምሥራቅም የሚፈሱ ትናንሽ ጅረቶች አሉ። እነዚህኞቹ የሚገኙት የኢትዮጵያን ተፋሰስ በምዕራብ እና በምሥራቅ እያካፈለ ከደቡብ ወደ ሰሜን በሚዘልቀው እና ማማ ምድርንም ከሚነካው ሸንተረር በስተምሥራቅ ባለው አካባቢ ነው። እነሱም ተጠረቃቅመው ወደ ጀውኃ ይገባሉ። ከዚያም ወደ አዋሽ።

በአጠቃላይ የወረዳው መልክዓምድር ሲታይ ዳኛቸው ወርቁ (1962:5) የይፋትና ጥሙጋ አውራጃን "እግዚአብሔር ዓለምን ሰርቶ ሲያበቃ የተረፈውን ትርክምክም ያጐረበት ዕቃ ቤቱ ...." ብሎ ከገለፀበት ሁኔታ ጋር የሚመሳሰል ነው። ሁሉም ዓይነት የመሬት ቅርፅ ለዓይነት ለዓይነት የተከማቸበት ይመስላል።

የአየር ንብረቱ 49.3% (አርባ ዘጠኝ ነጥብ ሦስት ከመቶ) ደጋ፤ 39.5% (ሰላሣ ዘጠኝ ነጥብ አምስት ከመቶ) ወይና ደጋ፤ እንዲሁም 11.2% (አስራ አንድ ነጥብ ሁለት ከመቶ) ቆላ ነው። ወረዳው የተለያዩ የመሬት፤ የቅዝቃዜ፤ የእርጥበት፤ የዝናብ መጠን ይስተዋልበታል። ከጥቅምት እስከ ታህሣሥ ከፍተኛ ቅዝቃዜ ያጋጥማል። በተለይ ሌሊትና እና ማለዳ ላይ ውርጭም ይኖራል (አቶ ኃይሉ እሸቱ በ22/5/99)። ስለሆነም ከጥቅምት እስከ ታህሣሥ ያለው ጊዜ የቆፈን ወቅት ነው ማለት ይቻላል። አልፎ አልፎ ደግሞ በደጋው ላይ ከፍተኛ የደመና ቁልል ይኖራል። አገሬው ደመናው ሲከፋበት "ዓይን ቢወጉ የማያሳይ ደመና" በማለት ይገልፀዋል።

ከጥር እስከ መጋቢት የበልግ ዝናብ አለ። የበልግ ዝናብ ቆይታው አጭር ነው። ስለሆነም በዚህ ወቅት አካባቢው ደረቅ እና ፀሐያማ ይሆናል። ኃይለኛ ቅዝቃዜ አይኖርም። ከሚያዚያ እስከ ግንቦት በአመዛኙ በሁሉም የወረዳው ክፍታዎች ማለትም ደጋ፤ ወይና ደጋ እና ቆላ ሞቃታማ አየር ይኖራል። የላሎ-ማማ ሰው "ፀሐዩ አሳረረን" የሚለው በነዚህ ወራት ነው።

2.2. አስተዳደራዊ አወቃቀር

ላሎ-ማማ በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር የሚገኝ ወረዳ ነው። ወረዳው በተለያዩ መንግሥታት የተለያዩ የአስተዳደር መዋቅር ሲሰጠው ኖሯል። አቶ ገብረወልድ ገብረፃድቅ የመንግሥት ጠረተኛ እና አርሶ አደር (በ18/5/99) እንዳጫወቱኝ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ-መንግሥት አንድ ወረዳ ሆኖ በሥሩ አምስት ምክትል ግዛቶች/ ገዢዎች/ በርካታ አጥቢያ ዳኞች፤ ምስለኔዎች፤ ጭቃ ሹሞች እና ነጭ ለባሾች አስተዳደር እና እዝ ሥር ነበር።

በደርግ ዘመነ-መንግሥትም አንድ ወረዳ ሆኖ በሥሩ ሀምሣ ሰባት ቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ነበሩ። በገበሬ ማኅበራቱም ውስጥ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች እና የእዝ መዋቅሮች እና ኮሚቴዎች ነበሩ። ዛሬ ደግሞ አቶ ግርማ ይታፈር የወረዳው አፈ-ጉባኤ (በ24/5/99) እንደነገሩኝ በሃያ ስድስት ቀበሌ ገበሬ ማኅበራት አስተዳደር እና አመራር ሥር ነው። የቀበሌዎቹ ብዛት የቀነሰው አንዳንዶቹ ወደ ሌላ ወረዳ በመካለላቸው እንዲሁም በውስጥ የታጠፉ በመኖራቸው ነው።

2.3. የሕዝቡ ማንነት እና የኋላ አመጣጥ

2.3.1. ከአሁን ምልከታ አኳያ

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በአሁኑ ወቅት የላሎ-ማማ ሕዝብ ፖለቲካዊ እና አስተዳደራዊ መዋቅር ምድብ ከአማራ ብሔር እና ከአማራ ክልል ነው። ይሁንና ይህ ምደባ እና ፍረጃ ከላዕላይ መዋቅር (surface structure) እይታ የመነጨ ይመስላል። ምክንያቱም ብዙኃኑ የላሎ-ማማ ህዝብ እራሱን አማራ አድርጐ አማራ ነኝ ሲል ብዙም አይሰማም። ከአካባቢው ራቅ ብሎ ሲሄድ ምንድነህ? ተብሎ ሲጠየቅ "መንዜ ነኝ" የሚለውን ያደምቃል። በቅርብ ርቀት ላይ ሳለም "ላሎ-ምድር፣ ማማ-ምድር፣ ደንጋዜ፣ አፍቀራ፣ ላሊማ ነኝ" ነው የሚለው። በወረዳው ውስጥም እያለ ምንድነህ ሲሉት ሞላሌ፣ እመጓ፣ ወምቻ፣ ጉርምኛ፣ ታች ዘራም፣ ላይ ዘራም፣ አጐ፣ ሰዋሮ፣ የጫ፣ ጐሽበር ወዘተ እያለ ሲመልስ ይደመጣል። ሌላው ቀርቶ በሚኖርበት ቀበሌ ወይም አጥቢያ ውስጥ እያለ ቢጠየቅ ቤቱ ማለትም መኖሪያው ያለበትን ጐጥ እና ሸጥ ይጠራል።

በአጠቃላይ ሕዝቡ ማንነቱን የሚገልፀው ከርቀትም ይሁን ከቅርበት ከመጣበት ሥፍራ አኳያ ነው። አማራነት ለላሎ-ማማ ሰው ክርስቲያንነት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይነት መግለጫ ነው። የሀገር ሽማግሌዎችንም፣ ሽማግሌዎችንም ተራ ሰዎችንም ለመሆኑ የላሎ-ማማ ሕዝብ ዘሩ ከወዴት ነው? ማለቱ አልቀረም። ምላሻቸው

> *"የሰው ዘሩ የዘማት ሥሩ (ዘማት የአትክልት /ዛፍ/ ዓይነት ነው) መቼ ይታወቃል ብለህ ነው ወዳጅ እና "የእኛ ዘርና የሸመታ ጥሬ አንድ ናቸው አባክህ አሁን የተቀላቀለን የሸመታ ጥሬ ምን ትለዋለህ ቅልቅል፣ ድብልቅ ነው እንጂ" የሚል ነው (አቶ ሸዋ ይርጋ አስፋው አርሶ አደር በ11/5/99፣ አቶ እንግዳ አልታዬ አርሶ አደር በ13/5/99)።*

አማራ ስትሉ ምን ማለታችሁ ነው? ብያቸውም "ክርስቲያን ነዋ! እርስ በርሳችን ስንጣላ እንኳ ጠቡ የከረረ ለሸማግሌ ያስቸገረ የሚሆነው እኔና አንተ ከዛሬ ጀምሮ እስላምና አማራ ሆነናል የተባባልን እንደሆነ ነው።" በማለት መልሰውልኛል። ሕዝቡ አሁን ራሱን ከላይ በተመለከትነው መሠረት ያያል፣ ይገልፃል። አፈ-ታሪክ እና ጽሁፍ-ታሪክ ደግሞ ከሩቅም ከቅርብም ክንዋኔዎች አንጻር የሚተርኩት አለ።

2.3.2. ከአፈ-ታሪክ አኳያ

በሕዝቡ ውስጥ ሥር የሰደደው ባህርይውን እና አመለካከቱን እንዲሁም አስተያየቱንም የቀረፀው ይበልጡንም ደግሞ ያጐለበተው የሚመስለው ስለ አካባቢው አቀናን የሚነገረው አፈ-ታሪክ ነው። አፈ-ታሪኩን አዋቂውም ልጁም ይተርከዋል። ብዙዎች ዘመኑን አይጠቅሱም። አንዳንድ አዛውንቶች ግን ምናልባትም የግራኝ (የኢብን ኢብራሂም መሐመድ) ሠራዊት ከተመታ በኋላ ሳይሆን እንደማይቀር ይገምታሉ። (ኢብን ኢብራሂም መሐመድ እ.ኤ.አ. ከ1531 ዓ.ም ጀምሮ ለአሥራ አምስት ዓመታት ያህል እስከሰሜን ዘልቆ መቆየቱ አይዘነጋም)።

አፈ-ታሪኩ እንዲህ የሚል ነው። "መንዝ በጠቅላላው የቀናው በሦስት ፈረሰኛ ወንድማማቾች (አንዳንዶች ወንድማማችነታቸውን አያፀድቁም) ነው። ሦስቱም ፈረሰኞች እና ጦረኞች በአንድ ቀን ውሎ የደረሱበትን አገር ያዙ ያም መንዝ ነው።" የሚል ነው (አቶ ቀጥይበሉ አሳምነው በ17/5/99 እና ሌሎችም)። እንደ አፈ-ታሪኩ አገላለፅ አቅኚዎቹ በያዙት መልክዓ-ምድር አቀማመጥ ከደቡብ ሲታዩ ማማ፣ ላሎ፣ ጌራ የተባሉትን አካባቢዎች ከደቡብ መንዝ በኩል ከተገለት ሞፈር ውኃ ከጀማ፣ አዳባይ ተሻግረው ይዘዋል። ጋልበው የዘመቱበት አካባቢም ግዛታቸው ሆነ። ከዚህም የተነሳ አካባቢው ማማ ምድር፣ ላሎ ምድር፣ ጌራ ምድር ተሰኘ። የጌራ ፈረስ ኃይለኛ ስለነበር ጌራ ሰፋ ያለ መሬት ሊይዝ ቻለ የሚል ገለፃ ይሰጣል። ገለፃው እንደሚጠቁመው እና አሁንም እንደሚታየውም ጌራ ምድር ሰፊ አካባቢን ይሸፍናል። ማማ ምድር በስፋቱ ሁለተኛ ነው። ላሎ-ምድር አነስ ይላል።

በአጠቃላይ ሲታይ ይህ ጥናት የሚሸከረከርበት የላሎ-ማማ ወረዳ ሕዝብ እስካሁን ከተጠቀሱት አፈ-ታሪካዊ ሁነቶች የቀሰመው፣ የወሰደው እና ልማድ እና ባህል ያደረገው የማንነት እና የባህርይ መግለጫ የፈጠረ ይመስላል።

2.3.3. ከታሪክ አኳያ

በታሪክ ረገድ የላሎ-ማማ ሕዝብ ማነው? የሚለውን ማየት እና መመለስ የሚቻለው አማራ ማነው? የሚለውን የኋሊት ሄዶ በመመርመር ከዚያም የላሎ-ማማን ትስስር በመመልከት ነው። አማራ ማነው? ከየትስ መጣ? የሚለውን ተክለጻድቅ (1966፣8) የሚገልጹት ከጠቅላላው የሲም ነገድ ማንነት እና አመጣጥ ጋር አስተሳስረው ነው።

> *"በደቡብ አረብ ፊት ለፊት የሚታየው የኢትዮጵያ ሰሜን ነው። ስለዚህ የሳባ ወገኖች ወደ ኢትዮጵያ ተሻግረው በሐማሴን፣ በአካለ-ጉዛይ፣ በአጋመ፣ የሀበሳን ወገኖች በአሳሆርታ፣ በሐውዜን ሲሰማሩ በአረብ አገር ሳሉ ከሳባ በስተደቡብ የሚኖሩት ሂሜሪያትና ሆሚሪት የኤርትራን ባህር ከተሻገሩ በኋላ ሳባና ሀበሳን ከሰፈሩበት በስተደቡብ በኩል ያለውን ሰፋፊ አውራጃ ይዘው ስለሰፈሩ ሂሜያሪት ወይም ሆሜሪት የሚባለው ስያሜ በጊዜ ብዛት ትንሽ ፊደሉንና አባባሉን እየለወጠ መጥቶ በሂሜያሪት አምሐራ ተብሎ ይሆናል።*

እውነትም የአማሮች የመጀመሪያው መሠረታዊ አገር አምሐራ ሚይንትና ቤተአምሐራ የሚገኝበት ሐይቅ ደብረ-አስጢፋናስ ግሼን መካነ-ንገሥት እነ ተድባበ ማርያም እነ አትሮንስ ማርያም የሚገኙበት ታላቅና ለምለም አውራጃ ነው።"

ተክለሐዋርያት፡ (1998:160) ደግሞ፡-
"አማራ በተባለው ሕዝብ (የትግራይና የሐማሴን ተጨምሮ የሚበዛው፣ የእስያውንና የአውሮፖውያን ደም ነው። ደግሞ የሸዋ የወሎ፣ የየጁ የጎጃም በትርብ ጊዜ የአሮም ደም በብዙ ተቀላቅሎበታል፣ (ከግራኝ አህመድ ወረራ በኋላ) እንደዚሁም የአዳል ደም ተቀላቅሎበታል" ብለዋል።

አሁንም ይህ የዘር መደበላለቅ በተለይ በሸዋ እጅግ ከፍ ያለ መሆኑን Levine በ Aspn (1994፣99) ውስጥ :-

"ሰሜን ሸዋ የባህል እና የኃይማኖት ውህደት፣ ድብልቅነት ወይም ዝንቀት ይታይበታል። ዛሬ አማራ የሚባለው ሕዝብም ከአንድ ነጠላ ጐሣ ወይም ቡድን የመጣ አይደለም። ከተለያየ ጐሣ የመጣ እና የተዋሃደ የአንድ ቋንቋ ባለቤት ማኅበረሰብ እንጂ። አማርኛም የአንድ የተለየ ጐሳ ቋንቋ አይደለም። ከኩሽ ከሰሜን እና ደቡባዊ ሴም ቋንቋዎች የተውጣጣ የጋራ መግባቢያ እንጂ" በማለት ገልያታል።

ከዚህ ገለፃም አማራም ሆነ አማርኛ አንድ ዘር እና የአንድ ዘር ፍጥር ቋንቋ አለመሆናቸውን እንረዳለን።

የላሉ-ማማ ወረዳ ሕዝብ ዛሬ ፖለቲካዊ አደረጃጀቱ በአማራነት ይሁን እንጂ ራሱን ወይም ማንነቱን (identity) አስፍቶም ሆነ አጥቦ የሚገልፀው በአካባቢው ስም ነው። "አማራ ነኝ" የሚለው ደግሞ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው እምነቱን ሲጠየቅ ብቻ ነው። አማራ የሚለው የዘር፣ የብሔር ስያሜም ከዚህ በላይ ለማሳየት እንደተሞከረው ያወዛግባል። እንዲያውም በላይ ግደይ (1995:132-133) ደግሞ አማራ ነገድ አይደለም፤ አማርኛም ራሱን የቻለ የነገድ ወይም የብሔር ቋንቋ አይደለም። ይልቁንም አማርኛ የአክሱም ወታደሮች ከግዕዝና ከትግሪኛ አውጣጥተው ይጠቀሙበት የነበረ ምስጢራዊ የሠራዊት ቋንቋ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያን የመንግሥት ታሪክ አካሄድ እና የሕዝብ ንቅናቄ አያይዞ ዝርዝር የታሪክ ምልከታ ማድረግ እና ማከልም የበለጠ የላሉ-ማማን ህዝብ ማንነት ለመመልከት እና ለማጤን የሚያስችል ይመስለኛል።

ለምሳሌም የሰለሞናዊ ሥርወ-መንግስት በአገው እና በቤጃ ንቅናቄ ምክንያት ከ937-950 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ አክሱም ላይ ሲደመሰስ አንበሳ ውድም የተባለው የዘርዓ መንግሥቱ ተወላጅ እና ተከታዮቹ ወደዚህ ወረዳ አቅራቢያ እና ቀስ በቀስም ወደ አካባቢው ዘልቀዋል። (ማህተመ ሥላሴ 1965:7፣ ኪሮስ እና ማዘንጊያ 1972፣62)። ይህም ለሕዝብ እና ለባህል መዛነቅ አስተዋፅኦ አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪም በ1262 ዓ.ም የአክሱም መንግሥት የመጨረሻ ንጉሥ ድልነዓድ ዘጠነኛ ወይም አስረኛ ትውልድ ነው የሚባለው

ሸዋው ይኩኖ አምላክ ንግሥናውን ከዛጉዬ መንግሥት ላይ መቀማቱ ይታወሳል።(ተክለፃድቅ 1966፣ 2-6)። እንዲሁም ደግሞ የኢብን ኢብራሂም መሐመድ (በተለምዶ ግራኝ መሐመድ) ጦር የአፄ ልብነ ድንግልን ጦር በ1515 ዓ.ም ድል መምታቱ እና ወደ ሰሜን ማስፈግፈጉ እና የሸሸውም የአባረረውም ሠራዊት በዚሁ ወረዳ የተራራ ስንሰለት (የዘማች ጉዳና) መቆየቱ እና ማለፉ ሁሉ ተዕፁል (ማህተመ ሥላሴ 1965:8፣ ኪሮስ እና ማዘንጊያ 1972፣74፣ ተክለ ፃድቅ 1966፣ 353-357)። ይህም የበኩሉን የሕዝብ ለሕዝብ ቅይይጥ ፈጥሯል።

የአካባቢው ሕዝብ የዝርያ መቀያየጥ የሚገለፀው ከላይ በቀረበው የታሪክ ማስረጃ ብቻም አይደለም። የ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኦሮሞ ማኅበረሰብ በምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ መስፋፋት እና በላሉ ማማ ወረዳ በኩልም ወደ ሰሜን መዝለቅም ይጠቀሳል። (ተክለፃድቅ 1966፣ 8፣ Assefa፣1993፣16)። እንደዚሁም የአፄ ገላውዴዎስ ከሰሜን ኢትዮጵያ ወደ ደቡብ ማምራት እና የመልሶ ማቅናት ጥረት ያስከተለው የሕዝብ መቀያየጥ መደበላለቅ እና ትውልድ ማፍራት ሁሉ አለ (ተክለፃድቅ 1966፣637-643)።

የአፄ ቴዎድሮስ የ1855 ዓ.ም የሸዋ ዘመቻ፤ (ጳውሎስ 1985: 82፣ ኪሮስ እና ማዘንጊያ 1972፣91) የአፄ ምኒልክ ከመቅደላ ወደ ሸዋ መዝለቅ እና በዚሁ ወረዳ መቆየትና ወደ አንኮበር ማለፍ (ተክለፃድቅ 1964፣75)፤ እንዲሁም ከ1928-1933 ዓ.ም ኢትዮጵያን የወረረው የፋሽስት ኢጣሊያ የጦር አመራር የሃማሴን፣ የጅሌ ኦሮሞን፣ አፋሮችን በአካባቢው ላይ አደራጅቶ ማዝመቱ እና ማቆየቱ (የአካባቢው ሽማግሌዎች ተረክ) ሁለንተናዊ መስተጋብር መፍጠሩ አልቀረም።

በመጨረሻም የአፄ ኃይለሥላሴ፣ የደርግ እና የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር አገራቱን የማማከል ጥረቶች፣ ዘመቻዎች እና ሌሎችም ሁነቶች ሁሉ በዚህ ሕዝብ ደኅና ያለፉ የተፈጸሙ ሕዝቡም (በክፉም በደጉም) የተሳተፈባቸው በሂደትም ስም፣ ዝና፣ ማዕረግ እንዲሁም ውድቀት ጭምር ያገኘባቸው በዚያው ልክም ከሌሎች የተዋሃደባቸው በመዋለድም አጥንትና ደሙ የተቀላቀለባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ።

2.4. ማኅበራዊ ገፅታ

በዚህ ርዕስ ሥር የወረዳው የትምህርት፣ የጤና፣ የእምነት፣ የጋብቻ፣ የስም አሰያየም፣ የሥራ ባህል እና የአሰፋፈር ሁኔታ ይቀርባል። የሕዝቡ ዓለማዊ አተያይም ይመላከታል።

2.4.1. የትምህርት ሽፋን

የመጀመሪያው ዘመናዊ ትምህርት ቤት ላሎ-ማማ ውስጥ የተከፈተው በ1940 ዓ.ም ነው። ስሙም "አቤቶ ኒጋሲ ክርስቶስ ወረደ ቃል ትምህርት ቤት" የሚል ነበር። ትምህርት

ቤቱ በመጀመሪያ ከ1-8ኛ ክፍል ኋላ ላይ ደግሞ ከ1-10ኛ ክፍል ድረስ ትምህርት ሲሰጥበት ቆይቷል። የደርግ መንግሥት ሥልጣን እንደያዘ አካባቢ ደግሞ የትምህርት ቤቱ ደረጃ ከፍ ብሎ ነገር ግን ስሙ ተቀይሮ "ሞላሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት" ተብሏል። አሁን ደግሞ የቀድሞ ስሙ ይመለስልን የሚሉ ሰዎች በቀድሞ ስሙ ለማስጠራት እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ነግረውኛል (አቶ ተሰማ ዝቂ ነጋዴ በ18/5/99)።

ከዛሬ 59 ዓመት በፊት በወረዳው አንድ ብቻ የነበረው ዘመናዊ ትምህርት ቤት በጊዜ ሂደት በአፄ-ኃይለሥላሴም፤ በደርግም በአሁኑም መንግሥት በተደረጉ የማስፋፋት ጥረቶች ቁጥሩ ጨምሯል። የወረዳው የትምህርት ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ ደምሰው ተምትሜ እስከ 1998 ዓ.ም የተጠናቀረውን የትምህርት ሽፋን መግለጫ ሠንጠረዥ መሠረት አድርገው እንዳሳዩኝ እና እንደነገሩኝ በወረዳው ውስጥ ሁለት አፀደ ህፃናት፤ አርባ ዘጠኝ የመጀመሪያ "ሳይክል" ሃያ ሰባት ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ፤ ሁለት ከዘጠነኛ እስከ አሥረኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጥባቸው እና አንድ የመሰናዶ ትምህርት መስጫ በጠቅላላው ሰማንያ አንድ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። በነዚህም ውስጥ ሰላሳ አምስት ሺህ የሚደርሱ ተማሪዎች ይማራሉ። በተለያዩ ደረጃ የሰለጠኑ ከአምስት መቶ በላይ የትምህርት ባለሙያዎችም በመማር ማስተማሩ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ (አቶ ደምሰው ተምትሜ የወረዳው ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት ምክትል ኃላፊ በ22/5/99)።

2.4.2. የጤና ሽፋን

የመጀመሪያው የጤና ተቋም በወረዳው ርዕሰ ከተማ ሞላሌ የተከፈተው በ1946 ዓ.ም ነበር። የሞላሌ ጤና ጣቢያ ከተከፈተ ዛሬ አምሳ ሦስት ዓመት ሆኖታል። የወረዳው ጤና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ፀጋዬ ሰይድ (22/5/99) እንደነገሩኝ በዚህ የጊዜ ሂደት ውስጥ ወገሬ ላይ አንድ ጤና ጣቢያ ተከፍቷል። አስራ አምስት የጤና ኬላዎች ደግሞ በየቀበሌ ገበሬ ማህበሩ አማካይ ሥፍራ ተከፍተዋል። ባለፈው ዓመት 1998 ደግሞ ሰላሳ ስድስት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በየቀበሌው ተሰማርተዋል። የጤና ተቋማቱ ቁጥር እድገት እያሳየ የመጣ ቢሆንም የጤና ጣቢያዎቹም ሆነ የጤና ኬላዎቹ በየደረጃቸው ሊኖራቸው የሚገባቸው የጤና መኮንኖች ነርሶች፤ ፋርማሲስቶች፤ የላቦራቶሪ ቴክኒሻኖች እና ቁሣቁሶች ግን የተሟሉ አይደሉም።

2.4.3. እምነት

ላሉ-ማማ ውስጥ 99% (ዘጠና ዘጠኝ ከመቶ) የሚሆነው እና በግብርና ሥራ የሚተዳደረው ሕዝብ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና እምነት ተከታይ ነው። በከተሞች እና በገጠርም በመንግሥት ሥራ ከሚተዳደሩ መካከል ደግሞ ሌሎቹን የክርስትና እምነቶች (ፕሮቴስታንት እና ካቶሊክ) የሚከተሉ አሉ። እንደዚሁም ማያጮጥ ገበሬ ማህበር ውስጥ እስልምናን የሚከተሉ አርሶ አደሮች አሉ (አቶ ግርማ ይታፈር በ24/5/99)።

ይሁን እንጂ በህዝቡ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚታዩ ሌሎች ልማዳዊ እምነቶችም አሉ። ከእነዚህ ልማዳዊ እምነቶች መካከልም አንዱ በአድባር ማመን ነው። በአድባር ማመን የሚገለፀው በጥቅምት ለእንሰሳት ደህንነት በሚል በብዙ ሰዎች ግቢ በሚደረግ የቦረንትቻ እርድ፣ ቡና ቂጣ፣ ቆሎ፣ ጠላ፣ አረቄ መሰናዶ እና በክብት በረት ውስጥ በመመገብ እና በመጠጣት ነው። በአድባር ማመን እና ለአድባር "ምስ" /መስዋዕት ለማለት ነው/ የሚቀርበው በጥቅምት ብቻ አይደለም። በግንቦት ልደታ /ግንቦት አንድ ነው/ በቤት ውስጥ በሚደረግ በኑግ፣ በሰሊጥ በተልባ በሚዘጋጅ ቂጣ ቆሎ እንዲሁም ጠላ እና አረቄ ዝግጅት እና ማሻተትም ጭምር ነው። ይህ ለግንቦት ልደታ የሚደረግ ዝግጅት በአንዳንድ ሰዎች ቤት እስከ ግንቦት አምስት ባሉት ቀናት በአንዱ እንደ ጥቅምቱ ሁሉ በክብት በረትም ይደረጋል። በየግለሰቡ ከሚደረገው የአድባር እምነት መግለጫ ዝግጅት በተጨማሪም በተለይ ለገና የአንድ ጮጥ ወይም አካባቢ ሰዎች ተሰባስበው ነጭ፣ ወይም ጥቁር በሬ ገዝተው በአጠገባቸው በሚፈስ ወንዝ ዳርቻ ወይም ገደል አፋፍ አሊያም ዋሻ አጠገብ እርድ ይፈፅማሉ። ከሥጋው ብልቶችም ቀነጣጥበው አድባር ለሚሉት ይጥላሉ። እነሱም ከየብልቱ ዓይነት ወስደው በጨው እና በበርበሬ ጥሬውን ይቃመሳሉ። አልፎ አልፎም ጠላ እና አረቄ ለአድባሩ ይደፋሉ፣ ይረጫሉ። ለራሣቸውም ይጠጣሉ። ሰፈሩን፣ ሰውንና ከብቱን፣ አዝመራውን ይባርከው፣ አማን ያደርገው ዘንድም ይመርቃሉ።

ይህ በቤት፣ በግቢ፣ በሰፈር የሚደረግ የአድባር ሥርዓት በተለይ ቀደም ባለው ጊዜ እስከ 1960ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ድረስ በአጥቢያ (በአንድ ቀበሌ) ደረጃም ይካሄድ ነበር። ይህ በአንድ ቀበሌ ደረጃ የሚደረገው የአድባር እምነት "ራሄሎ" ይባል ነበር። "ራሄሎ" የሚደረገው አንድን ቀበሌ ተስቦ፣ ጉንፋን፣ የከብት በሽታ፣ የአዝርዕት ተውሳክ፣ ሲያጠቃው እና ነዋሪው አድባሯ ተቆጥታለች ብሎ ሲያምን ወይም የተጠቀሱት ችግሮች በጐረቤት ቀበሌ ሲታዩ ችግሩ ወደ ሌላኛውም ቀበሌ እንዳይተላለፍ ለማድረግ ነው።

ራሄሎ የነጭ በሬ እርድን፣ የቂጣ፣ ቆሎ፣ ቡና፣ ጠላ፣ አረቄ፣ ዝግጅትን የሚሻ ሲሆን፣ ሥርዓቱም የሚከናወነው በቀበሌው ውስጥ ባለ ከፍተኛ ኮረብታ ላይ ነበር። በዚህም ወቅት

ራሄሎ ሂድ ቶሎ ቶሎ፣
አገራችንን እለፈው ቶሎ።

እየተባለ ይዘመርለት ነበር። ይሁንና ይህ የራሄሎ ሥርዓት በአንድ ቀበሌ ተራራ ላይ ከመፈፀሙ በፊት በተራራው ትይዩ የሚገኙ እና ቀድመው የራሄሎ ሥርዓት ያልፈጸሙ ቀበሌዎች ካሉ የአገር ሽማግሌዎች ስለ ራሄሎው በዓል ሀሳብ ሊያካፍሏቸው ወይም ሊያጋሯቸው ይገባል። የተጐራባች ቀበሌዎቹ በሀሳቡ ከተስማሙም በጋራ ድንበር ኮረብታ ላይ በጋራ ይከበራል።

ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ቀበሌዎቹን በሚመሩ ባላባቶች እና አጥቢያ ዳኞች ወይም በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ላይ የቆዩ "ቁርሾ" (ቂም በቀል) ካለ የራሄሎ ሽኝቱ የአድባር ድግስ ለአጉራባች ቀበሌዎች ላይነገር ይችላል። ተነግሮም ደግሞ ስምምነት ሊታጣ ይችላል። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ አንድ ቀበሌ በኩረብታው ላይ የራሄሎ ሽኝቱን ሲደግስ ሌሎቹ ቀበሌዎች ጉንፋኑ፣ ተውሳኩ፣ በሽታው በአጠቃላይ መጥፎ ምልኪው ሁሉ ተረጨብን እያሉ በዱላ፣ በድንጋይ፣ በጩቤ እና በጥይት የሚጠፋጠፋበት ሁኔታ ይከሰት ነበር። በዚህም የተነሳ የአገር ሽማግሌዎችም የመንግሥት ባለሥልጣኖችም የራሄሎ ሽኝት የአድባር ድግስ እንዲቀር አድርገዋል። (ራሴ የማውቀው)።

ሌላኛው ልማዳዊ እምነት ዛር ወይም ውቃቢ የሚባለው ነው። ዛር ወይም ውቃቢ ወጣብን! አለብን! የሚሉ ሰዎች አንዳች መንፈሳዊ ኃይል እንዳደረባቸው እና እንዳለባቸውም ይቆጠራሉ።

ስለዚህ ሕዝቡ ልዩ ልዩ ችግሮች ሲያጋጥሙት ወደነዚህ ባለዛሮች ወይም ባለውቃቢዎች እየሄደ፣ "ስጤ ሳስቶ፣ ጨርቄ በምላጭ ተቦጭቆ፣ ላሜ ጡቷ አብጦ፣ በደጄ ደንቃራ ተጥሎብኝ፣ በጐቼ፣ በቅሎዬ፣ በሬዬ ወዘተ ተሰርቆ" እያለ መማፀኛ ብጤም እያቀረበ መፍትሄ ይጠይቃል። አቶ ሺፈራው ደምሴ እና አቶ ገብረህይወት አሳምነው እንደነገሩኝ (9/5/1999) ባለዛሮቹም (ባለውቃቢዎቹ) ጠላ፣ ብርዝና ጠጅ፣ አረቄ፣ እየተገመጠመጡ ወይ የጫት አመንሽርኳቸውን ከአንዱ ጉንጫቸው ወደ ሌላው ጉንጫቸው እያሟሟሩ እና "ቡፍ ቱፍ" እያሉ ለዚህ ተጠያቂው እንዲህ ዓይነት፣ እንዲህ ዓይነት ሥፍራ የሚኖር፣ እንዲህ ዓይነት ሰው ነው። ስለዚህ "የእገሌ ውቃቢ ነው ብለሽ/ህ/ ጥራ/ሪ/ው እኔ ዘንድ" በማለት ያሰናብቷቸዋል።

ተጠሪዎች በጥሪው መሠረት ከተገኙ የማውጣጣት ዳኝነቱ ይቀጥላል። ተጠሪዎች ካልተገኙ ግን አንድ ወይም ሁለት መልዕክት ተልኮባቸው ደጅ-ጠኚ በባለዛሩ(ውቃቢው) የፍርድ መስጫ እልፍኝ ምሰሶ ወይም አጥር ላይ "ውስል" ማለት ጧፍ አስራ/አስሮ እንድትሄድ/ እንዲሄድ ይነገረዋል። ጧፍ ካሠረ/ች በኋላ ጧፍ ከታሰረባቸው ሰዎች ጋር የሰውም ሆነ የእንሰሳት መቀላቀል እንዳያደርጉ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል። ጧፍ በታሰረባ/በ/ት ወይም በታሰረባቸው ሰዎች ላይም የንብረት እና የሕይወት መጥፋት እንደሚደርስባቸው ይገለፅላቸዋል። ለዚህም "ስለት" ማለት ቃልህ(ሽ) ደርሶኛል መግለጫ ኮርማ /ለስሪያ ያልደረሰ፣ ያልተቀጠቀጠ ወይፈን/ እንዲያቀርቡ ይታዘዛሉ። በታዘዙት መሠረት ራሳቸውን ማግለል የማይችሉ ደግሞ "ደባልቀህ(ሽ) አውጣኝ አውጪኝ" በማለት ይሰናበታሉ። እንደተገመተው አንዳንድ ምልክት ከታየም ዛሩ ወይም ውቃቢው ዝናው

እየገነነ ደጀ-ጠኜውም አበረከተ ይሄዳል። ይህም ባይሆን በአጠቃላይ ዛር(ውቃቢ) በአብዛኛው የላሎ-ማማ ህዝብ ዘንድ መኖሩ ይታመናል።

የዛር ዓይነቶቹም /ጠቋር፣ ወሰን ጋላ፣ ብር አለንጋ፣ አዳል ሞቲ፣ ወሰን ገፊ፣ ቸር ቦደስ፣ ግራኝ ወርቂት፣ ዋስ አጋች፣ ከድር፣ ሼህ ጨንገር፣ ሼህ አምበሲ፣ ኑር ሁሴን፣ ወርዚይላ፣ ወዘተ/ ይባላሉ። እነዚህም የላሎ-ማማ ዛሮች (ውቃቢዎች)ም ተወላጅ እና መጤ ተብለው ይከፈላሉ (ታደገኝ መርን 1992፡ 28-29)።

ከዛር ጋር ተካቶ መታየት ያለበት የሚመስለው ሌላው ልማዳዊ እምነት አቴቴ ወይም ጨሌ ነው። አቴቴ ወይም ጨሌ በአብዛኛው የሚከበረው ከነሐሴ መጨረሻ እስከ መስከረም አጋማሽ ባለው እጅግ ለምለም ወቅት ነው። ለአቴቴ ወይም ጨሌ የሚደገሰው ቅንጪ ነው። በወተት እና በቅቤ የተንጨፈጨፈ። "አውዛ" ማለትም ጫትም እየቀቀሉ እና እያንፈቀፈቁ ይጠጣሉ። አቴቴ ወይም ጨሌው በቂቤ ይነከራል።ከተነከረ በኋላ በሴቶች አንገት ላይ ይጠለቃል። አቴቴ ወይም ጨሌ ከማጥለቃቸው በፊት ሴቶች ንጽህናቸውን ይጠብቃሉ። የወር አበባ ሊኖራቸው አይገባም። ገላቸውን ይታጠባሉ። "የርጅት ልብስ" የሚሉትን ከተለያዩ ጥለቶች የሚሠራ ዝንጉርጉር ልብስ ይለብሳሉ። የእጅ ፊትል ጉፍታ ይከናነባሉ (ወይዘሮ ወለተዮሐንስ ወልደ ጊዮርጊስ የቤት እመቤት በ12/5/99)።

ከአድባርና ከዛር በተጨማሪም በሕዝቡ አስተሳሰብ እና አድራጐት ውስጥ የሚታዩ እና የሚገለጹ ልማዳዊ እምነቶች አሉ። ከእነዚህም መካከል አንዱ "ቡዳ" ማለትም "ሰውን በዓይናቸው አይተው የሚበሉ ዘሮች ወይም ትውልደ-ቤተሰቦች" አሉ የሚለው አስተሳሰብ ነው። በ"ቡዳነት" የተፈረጁ ወገኖች አይተውኝ "ታመምኩ" የሚል ሰውንም የምሥር ቂጣ በማብላት ወይም አመድ በማስቃም እናስለቅቃለን የሚሉ ራሳቸውን "መጽሐፍ ገላጭ" ብለው የሚሰይሙ "ደብተራዎች" አሉ። ይህ "የቡዳ በሽታ" የሚባለውም ቢሆን ግን ስለ ቡዳ እና ቡዳ ዘርነት ሲነገር፣ ሲደመጥ ከመጣ ሁኔታ እና የአዕምሮ ጭንቀት ልቀት መሆኑ ባይቀርም በሕዝቡ ውስጥ ግን የሚታይ እምነት ነው።

ከ"ቡዳ" በሽታ ፈዋሽነት ጋር ተያይዞ የመጣው ሌላው የ"መጽሐፍ ገላጭነት" ጥንቆላም ቢሆን "ዐውደ ነገሥት" የተሰኘውን መጽሐፍ በመጠቀም የሚካሄድ ተግባር ነው። የተጠቀሰው መጽሐፍ አለን የሚሉ ሕጋቸውን ያፈረሱ ደብተራዎች "ከኮብ እንቆጥራለን ፀር እና ፀርን እንነግራለን። የጋብቻ እና የመኖሪያ ቦታ ስምምን እናውቃለን፣ ልቦናችን ባልፈቀደው ሰው ላይ "አስማት" እናደርጋለን "እንደርቢ እናወርዳለን" የሚሉ ሰዎች ናቸው። (አያቴ /የናቴ አባት ደብተራ ወልደጊዮርጊስ/ እና አጐታቸው ደብተራ ዘወልዴ በህይወት ሳሉ ደብተራ ዘወልዴ "መጽሐፍ እገልባለሁ" ይሉ ስለነበር "ለመሆኑ ምን ምን እያልህ

ትጠነቁላለህ" ሲሏቸው እና ሲጫወቱ የሰማሁት እና የማስታውሰው።) ይህም ቢሆን በሕዝቡ ዘንድ የሚከበርም የሚፈራም ልማዳዊ እምነት ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪም ሕዝቡ "አጋንንት፤" "ሰይጣን" እና "ጭራቅ" የሚባሉ በእግዚአብሔር የተረገሙ የሰውን ደህንነት እና ህይወት የሚተናኰሉ፤ አደጋ ላይ የሚጥሉ መናፍስት አሉ ብሎ ያምናል።

በተለይ "አጋንንት" እና "ሰይጣን" ደግሞ ፀብን፤ ግጭትን በማባባስ ለነፍስ መጠፋፋት ይዳርጋሉም ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም "እከሌ እና እከሌ የተጣሉት እመህላቸው ሰይጣን ገብቶ ነው"፤ "እከሌና እከሌ አልታረቅ ያሉት "የሰይጣን ክንፍ አልሰበር ብሎ ነው"፤ "እከሌ እከሌን የገደለው ውኃ በማያነሳ ነገር ሰይጣን በል በል ብሎት ወይም ገፋፍቶት ነው"፤ "እከሌ ሰይጣናም ነው፤ ሰይጣኑ እስቲበርድለት ተውት" እንዲሁም "ሰይጣን አሳሳተኝ"፤ "ሰይጣን ጋልቦኝ እጁ አለፈብኝ" የሚሉ አባባሎች ተደጋግመው ይደመጣሉ።

"ጭራቅ" ሰውን የሚበላ አውሬ ተደርጎ ይወሰዳል። አልፎ አልፎም ህፃናት ከአንዳንድ እንቅስቃሴ እንዲገቱ ማስፈራሪያ ከሆኑት "ጐለጐሉ" እና ጅቡ ይበላሃል ቀጥሎ "ዋ ጭራቁ እንዳይበላህ" በማለት ያስፈራሩበታልም። ምናልባትም ቀደም ሲል የሚፈፀመው የአድባር "መካደሚያ" እርድ እና ድግስም በተለይ "አጋንንትን /ሰይጣንን" ለመማለድ እና ለመደለል ይመስላል።

በተለይ ይህ የአድባር መካደሚያ ምግብ ከየዓይነቱ ተውጣጥቶ በመንታ ወይም በአራት ፋና መንገድ ላይ ከተጣለ "ደንቃራ" ሆኖ መጀመሪያ የደረሰበትን ሰው ጤንነት በማወክ የ"ደንቃራ" ጣዩን ቤተሰብ ከመጥፎ " ምልክ" ማለትም የወደፊት መጻኤ-ክፉ ነገር ይሰውራል የሚል እምነትም አለ (አቶ ሽዋይርጋ አስፋው በ12/5/99)።

በአጠቃላይ ብዙኃኑ የላሎ-ማማ ሕዝብ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትናን በይፋ (በገሃድ) ይመን እንጂ ከላይ የተዘረዘሩትን የአድባር፤ የዛር(ውቃቢ)፤ የቡዳ፤ የአጋንንት (ሰይጣን) ጭራቅ እና መጽሐፍ ገላጭ ልማዳዊ እምነቶችንም ያዛንቃል። እነዚህም ሁሉ አስተሳሰቡን እና ግብሩን ይመሩታል ማለት ይቻላል።

2.4.4. ጋብቻ

2.4.4.1. የጋብቻ ቅድመ-መስፈርት

ላሎ-ማማ ውስጥ በጋብቻ ለመተሳሰር በቅድሚያ በተጋቢዎች መካከል የሥጋ ዝምድና አለመኖሩን ወደ ላይ እስከ ሰባት ትውልድ (ሰባት ቤት) ድረስ ቆጥሮ ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ከሥጋ ዝምድና ቆጠራ በተጨማሪም የክርስትና እና የጡት ልጅነት ተዛምዶ

አለመኖሩ ይረጋገጣል። እንደዚሁም ወንድም ሆነች ሴት ከመጋባታቸው በፊት እንዳቸው ከሌላኛቸው የሥጋ ዘመድ፤ የክርስትና እና የጡት ልጅ ተዛምዶ ካላቸው ወንዶች እና ሴቶች ጋር ቢያንስ የሚታወቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አለመፈፀማቸው ይጣራል። እነዚህን ማጣራት የወንድም ሆነ የሴት ወገን ግዴታ ነው። ይህንን መጣስም ከቤተ-ዘመድ ያርቃል፤ ያስገልላል፤ ያስነውራል፤ ያስረግማልም።

2.4.4.2. የጋብቻ አጠያየቅ እና አፈጻጸም

ቀደም ባለው ዘመን አንዳንድ ጊዜ የጋብቻ ጥያቄ ይፈፀም የነበረው ገና ተጋቢዎቹ ሳይወለዱ ጭምር ነበር። በተለይ በችሎት፤ በአደባባይ፤ በጋራ ዘመድ፤ በወንድነት፤ በዘር ሐረግ፤ በአጥንተ-ነጭነት (ለምጥ፤ሥጋ ደዌ፤ ሽባነት፤ ቀጥቃጭነት ሽክላ ሰሪነት፤ ቡዳነት፤ ባሪያነት ውጭ) የሚተዋወቁ እና የሚግባቡ ሰዎች ልጆቻቸውን በጋብቻ ለማስተሳሰር፤ ነባር ግንኙነታቸውን ወይም መቀራረባቸውን ለማደርጀት እና ለማጠናከር "ልጅህን ለልጄ" ይባባሉ የነበረው ገና ተጋቢዎቹ ሣይወለዱ ወይም አንዱ ወልዶ ሌላኛው ገና በሆነበት ጊዜ ሁሉ እንደነበር ይተረካል (አቶ ገብረወልድ ገብረዓድቅ እና አቶ መንግሥቱ አማረ በ18/5/99)። እንዲህ ዓይነቱ መቀራረብ እና መፈቃቀድ በነበራቸው ቤተሰቦች መካከል መተጫጨቱ የሚያልቀውም ከላይ እንደተጠቆመው በወንድ እና በሴት ልጅ አባቶች ውሳኔ ወይም መዋያ ሽንጉ ነው። በቃላቸው መሠረትም የማይተዋወቁ ልጆቻቸውን ዕድሜያቸው ለአካለ መጠን (አቅመ አዳም እና አቅመ ሄዋንም ይባላል። አቅመ አዳም ከ15-18 ዓመት ሲሆን፤ አቅመ ሐዋን ደግሞ ከ12-15 ዓመት ነው ይላሉ።) ሲደርስ ድል ያለ ሰርግ ደግሰው አዝማሪ አቁመው ያጋቡ ነበር።

እጅግም የችሎት፤ የአደባባይ ሰዎች ያልሆኑት እና መለስ ያለ ሕይወት የሚመሩት ደግሞ አልፎ አልፎም በደረጃቸው "ልጅህን ለልጄ" ተባብለው፤ ብዙውን ጊዜ ደግሞ የደረሰ ልጅ ሲኖር በቤተሰብ መካከል ምክክር ተደርጐ ጋብቻ ይፈፀማል። ምክክሩ የሚያተኩረው ይዛ ልጅ ለአቅመ አዳም እየደረሰ ነው። "ሰው እየሆነ ነው ውኃ አጣጪ ይፈለግለት" በሚል ሀሳብ ላይ ሲሆን ከፍተኛ ቀረቤታ ያላቸው የቤተሰቡ ቤተ ዘመዶች አውጥተው አውርደው "እከሌም የደረሰች ልጅ አለችው ። እከሌም እንዲሁ። ሁለቱም ዘንድ መከፋፋት ቂም በቀል ደም የለንም ። ቤተ-አግባብ ነን" ብለው አማርጠው ለመጠየቅ ይወስናሉ። ይህንኑ ሐሳብም የልጁ አባት ወንድሙን ወይም የባለቤቱን (የሚስቱን) ወንድም ወይም እጅግ የሚቀርበውን አንድ ሰው እና ቀደም ብሎ የተዳረ የበኩር ልጅ ካለውም እርሱንም ጨምሮ ወደ እምትታጨው ሴት ልጅ ቤተሰብ ለማጨት ይሄዳል።

የሴት ወላጆችም የመጡባቸውን ሰዎች የመጡበትን ምክንያት ቢጠረጥሩም ባይጠረጥሩም "ምን እግር ጣላችሁ? ጥቁር እንግዶች" ብለው ቤታቸው ያፈራውን ይጋብዛሉ።

አጨ.ዎች የሚያጫት ልጅ በቤት ውስጥ አለመኖሯን አረጋግጠው ከባልና ሚስቱ ውጪ ሌላም ሰው ካለ ለሰዎቹ ያለውን የቅርበት ደረጃ እዚያው ጠያይቀው አውቀው ከተረዱ በኋላ "ጉዳያችን ከባለቤቶቹ /ባልና ሚስቱ ለማለት/ ጋር ነበር" ሊሉ ወይም የእንግዳው መኖር ችግር የማይፈጥር /ወሬ የማያባክን/ መሆኑን ካወቁ ስለተደረገላቸው መስተንግዶ አመስግነው የመጡበትንም ምክንያት ይናገራሉ። ሀሳባቸውንም የሚገልጹት "በቤታችን እና በቤታችሁ (በትውልዳችን ለማለት) ከላይ የወረደ መከባበር አለ። ጊዜው ሳይደርስ ቀርቶ እስከ ዛሬ በዝምድና አልታሰረም። እነሆም ዛሬ መቸም ዘር ወደ መሬት እንጂ መሬት ወደ ዘር አይሄድምና ልጅ ታደርጉን ብለን እከሊትን ለልጃችን ለእከሌ ትሰጡን ብለን መጥተናል" ይላሉ።

የሴት ልጅ ቤተሰቦችም ምንም እንኳን ቀድሞውኑ ለጋብቻ ጥየቃ ስለመምጣቸው ጥርጣሬ ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም "መልካም ነው እኛ የደረሰች አልመሰለንም ነበር ካላችሁ ደግሞ ከዘመድ እንምከርበት፣ እናስብበት ጊዜ ስጡን" ይላሉ። ይመክሩበታልም። ከዚያም ጠያቂዎቹ እንደቦታው ርቀት ሁኔታ አንዳንዴ ጊዜ "ቀን ቁረጡልን እስከመቼ" ሊሉ አንደንዴም "ያው እንግዲህ የናንተን ትንፋሽ እንጠብቃ" ብለው ተሰናብተው ሊሄዱ ይችላሉ። ምላሹንም ከሁለት ሣምንት እስከ አንድ ወር ጊዜ ይለዋወጣሉ።

ጥያቂው ይሁንታ ካገኘም በመዳሪያ ሀብት እና በሰርግ አፈፃፀም ላይ ተወያይተው ቀን ይቆርጣሉ። በተቆረጠውም ቀን ሰርግ ይደረጋል። በሰርጉ ማግስትም ልጅቷ ድንግል መሆን አለመሆኗ የሚገለፅበት ሥርዓት አለ። ይህ ሥርዓት ለጋብቻው መፅናት ለቤተ-ጋብቻዎቹም መከባበር የሚያደርገው አዎንታዊ እና አሉታዊ አስተዋፅኦ አለው። ይኸውም ልጅቷ ድንግል ሆና ከተገኘች በነጭ ሻሽ ላይ የደም ምልክት ተደርጉ ጨዋ የጨዋ ልጅነቷን የሚያረጋግጥ ጭፈራ እየተደረገ ድፍን ዳቦ ተይዞ እንደየምሥራች ወደ ሙሽራዋ ቤተሰብ ማለዳ ይኬዳል። ከዚያም የደስታ ግብዣ ይደረግ እና ዳቦው በመጣበት መሶብም ውስጥ የመልስ ስጦታ በሶ ይላካል። ይኸው ለሙሽሮቹ ጉልበት ማፅኛ ይሆን ዘንድ ይታሰባል።

ልጅቷ በድንግልና ካልተገኘች ግን ደም የነካው ሻሽ እና ሙሉ ዳቦ ሳይሆን ነጭ ሻሽ እና የተቆረሰ ዳቦ ለወላጆቿ ይላካል። ይህም ጋብቻው በቀላሉ ሊፈርስ እንደሚችል ያመለክታል። ይሁንና አንዳንድ ጊዜ ሽማግሌዎች "ልጅ በዋለበት ወላጅ አይውልም አረፋ ጠባይዋና ሙያዋ ይታይ" የሚል ማግባቢያ ምክር ሰጥተው ሻሹ በነጩ ሣይሆን የጣት ወይም የዶሮ ደምም ቢሆን ነክቶት ዳቦውም ሳይቆረስ እንዲላክ ይደረጋል።

ቀደም ባለው ጊዜ ደግሞ በዝቅተኛ ደረጃ ያሉ ቤተሰቦች ወንድ ልጃቸውን ከላይ በተገለፀው መንገድ ለመዳር አቅም ስለሚያንሳቸው ቆጥ አስር የተባለውን ጋብቻ መፈፀም ይመርጡ ነበር። ቆጥ አስር ጋብቻ ማለት ወንዱ ለአቅመ አዳም ደርሶ ሴቷ ሳትደርስ ልጁ ለአማቶቿ የሚያገለግልበት ሁኔታ ነው። እነሱም ባህርዩውን እና የሥራ ትጋቱን አይተው በራሳቸው ጊዜ ከልጅቷ ጋር እንዲያድር ጉጅ ሊያመቻቹለት ወይም ልጅቷ እና ልጁ በአዩን አላዩን ግንኙነት ተጣጥመው ጉጅ ለመውጣት የጋራ ጥያቄ ያቀርባሉ። ሲፈቀድላቸውም እዚያው በሴቷ ልጅ ቤተሰቦች ግቢ ለብቻቸው ማደር ምግባቸውንም ማብሰል፣ ይጀምራሉ፣ ጉጅ ወጡ ይባላሉ። የልጅቷም ወላጆች ከእርሻ ምርታቸው ከበረት ከብቶቻቸው፣ በጉቻቸው እና ፍየሎቻቸው ለጉጅ ወጪዎች ድርሻ ያወጡላቸዋል።

ከላይ ከተጠቀሰው የጋብቻ አጠያየቅ እና አፈፃፀም ውጪም ቢሆን ጋብቻ ይፈፀማል። ይኸውም በክፍተኛ፣ በመካከለኛ እና በድህነትም ደረጃም ቢሆን ወጣቶች ለአቅመ አዳም እና አቅመ ሔዋን ሲደርሱ ወላጆቻቸው በተለያዩ ምክንያት ሳቢያ ማለትም የመዳሪያ ስጦታ ችግር (በጉች፣ ላሞች፣ በሬዎች ወዘተ) የሰርግ ወጪ እጥረት ወይም ሌላ ምክንያት አጋጥሟቸው ያልዳሯቸው ወይም በዚህ ሥርዓት ለማለፍ ዕድሉ ያልቀናቸው ትዳር ለመመሥረት፣ ጉጅ ለመውጣት ቢያስቡ ዕጮኛም ሆነ ባል የሌላትን ሴት ከስመ-በዓል፣ ከገበያ፣ ከልዩ ልዩ ማኅበራዊ ሥርዓት፣ ሰርግ፣ ክርስትና መልስ "አንቺ ነይ ለእኔ አብስይ" ብሎ በመጥለፍ እና ከጠለፋ በኋላ እንደሁኔታው ሽማግሌ ወይም መልዕክት ልኮ ለቤተሰቧ በማሳወቅ የሚፈፀም ጋብቻ ነው። ጠለፋው እጅግ ብርቱ ጥናት ይሻል። ምክንያቱም ልጁ ወይም ልጅቷ ቀደም ሲል እላይ ከተጠቀሱት የዝምድና ዓይነቶች ውስጥ የሚፈረጁ ከሆነ ወይም ልጅቷን የሚጠብቅ ወንድ ካለ የሚያስከትለው የከፋ መዘዝ አለውና ነው።

ቀደም ሲል በሀብታም፣ በመካከለኛ እና በድኃም መካከል ይፈፀም የነበረው የጋብቻ አጠያየቅ እና አፈፃፀም ሁኔታ ዛሬ ዛሬ መልኩን እየለወጠ መጥቷል። ጠለፋም መጠኑ ቀንሷል። ምክንያቱም በአብዛኛው የሕዝቡ የሀብት ምንጭ የነበረው ርስት በ1967 ዓ.ም በመወረሱ እና በባለርስትነትና በርስት አናሳነት እንዲሁም ርስት የለሽነት መካከል የነበረው ልዩነት በመጥፋቱ እና የአብዛኛውም ሰው ሕይወት የኑሮ ደረጃ ልዩነት በርስት ሣይሆን ባለው መሬት ላይ ተግቶ በመሥራት፣ በጉች እና ላሞች በማርባት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፣ እንዲሁም በኢ-መደበኛ ትምህርት እና በባህል አብዮት (ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ ያለትውውቅ ጋብቻ፣ የሰርግ አላስፈላጊ ወጪ) ወዘተ እየተወገዙ በመምጣታቸው ወጣቶች የትዳር ጓደኛቸውን እራሳቸው አይተው ለእከሊት ወይም ለእገሌ ዳሩኝ ማለት በመጀመራቸው ምክንያት መሆኑ ይነገራል።

በአጠቃላይ ሲታይ ዛሬም ቢሆን የወንድ ልጅ አባት ከልጁ ጋር ተመካክሮ እንደቀድሞው ሁሉ ቢጠይቅም፤ የሴት ወገኖችም በተተከለው ባህል እና ልማድ መሠረት ቢመልሱም የሰርግ መጠን እና ወጪ እየቀነሰ መጥቷል (አቶ ገብረወልድ ገ/ዓድቅ እና አቶ መንግሥቱ አማረ አርሶ አደር በ18/5/99 እና አቶ ግርማ ይታፈር በ24/5/99)።

ቆጥ አሥር ጋብቻም ሀብት ያላቸው የሴት ልጅ ቤተሰቦች የጉልበት አገልግሎት በመፈለግ፤ ድሃ ቤተሰቦችም ልጃቸውን ከነርሱ የተሻለ ሰው ለማድረግ፤ እስከዚያውም ከልጃቸው ጉልበት ለመደጉም "አንድም ከሀብታም ተወለድ አለያም ከሀብታም ተጠጋ" በሚል እሳቤ ይፈፅሙት የነበረ ጋብቻ በመሆኑ እየጠፋ ነው። ምክንያቱም የሀብት መሠረት እና ምንጭ የነበረው ርስት በገመድ በመሸንሸኑ እንዲሁም የወጣቶቹም አስተሳሰብ እየተሻሻለ በመምጣቱ እና የወንዱን አገልጋይነትም በማነወራቸው ነው።

የመጨረሻው አማራጭ የጋብቻ መፈፀሚያ ጠለፋም ቢሆን በአስተሳሰብም መሻሻል እንዲሁም "ሰው ያልነካው ሰው እህል ያልተቋጠረበት ስልቻ አይኖርም" በሚል ከሴትዮዋ ኋላ ማን እንዳለ ስለማይታወቅ እና ችግር ላለማስከተል በማሰብ እየቀነሰ መምጣቱ ይነገራል። ይሁንና አልፎ አልፎም ሲያጋጥም ክፉኛ ያማዝዛል፤ ነፍስ ያጠፋፋል።

ላሎ-ማማ ውስጥ ከላይ የተጠቀሰው የጋብቻ መስፈርት፤ አጠያየቅ እና አፈፃፀም ዋነኛው የአካባቢው ልማድ ይሁን እንጅ ከዚህ ውጪም "አስነግረው" ወይም "አዋቂ" ጠይቀው "ከኮብ" አስቆጥረው "ራወዲ" አስተያይተው ማለትም "ከኮብቸው" መገጣጠሙን "ራወዲያቸው" ፀር እና ፀር አለመሆኑን አረጋግጠው ጋብቻ የሚፈፅሙ አሉ። ድንገት ከኮብቸው፤ "ራወዲያቸው" ያልገጠመላቸው ደግሞ "ከጠየቁ አይንቱ" ብለው እንደገና ወደ አዋቂው ተመልሰው "መላ ይፈለግልን" ብለው መላም ተፈልጐላቸው እና አንዳቸው ስማቸውን መቀየር እንዳለባቸው ተነግሯቸው ወይ ስም አስመርጠው እና አስፈቅደው ወይም ተሰይሞላቸው ወይም ሊኖሩበት ያሰቡትን የመኖሪያ ጐጣቸውን ቀይረው የሚጋቡበት ሁኔታ አለ። የላሎ-ማማ ሕዝብ የዛሬው የጋብቻ ህይወትም ከሞላ ጐደል ይህንኑ ይመስላል።

2.5. ስም አሰያየም

ላሎ-ማማ ውስጥ አንድ ሰው አገልግሎታቸው እና ደረጃቸው የተለያዩ ሦስት ስሞች ሊኖሩት ይችላሉ። በተለይ ወንዶች ደግሞ ብዙውን ጊዜ ሦስቱም ስሞች ይኖሯቸዋል። እነዚህንም ሦስት ስሞች ዓለማዊ፤ መንፈሳዊ ወይም የክርስትና እና የሞጋሳ ስሞች ብለን ልንመድባቸው እንችላለን።ዓለማዊ ስም የሚባለው ህፃኑ እንደተወለደ ወይም ህፃኗ እንደተወለደች እናቶቻቸው፤ አባቶቻቸው፤ አያቶቻቸው ወይም የቅርብ ቤተሰቦች የሚያወጡት ወይም የሚሰይሙት ስም ነው።

ይህ ዓለማዊ ስም ታዲያ ዝም ብሎ እንደመጣ፤ ያለአንዳች ምክንያት እና ሰበብ አይወጣም፤ አይሰየምም። ይልቁንም የቤተሰቡን የኋላ ሕይወት ታሪክ፤ የአሁን ሁኔታ፤ የወደፊት ተስፋ ገላጭ፤ ጠቋሚ እና አመላካች እንዲሆን ይደረጋል። ለምሳሌ የህፃኑ ወላጆች ህፃኑ ከመወለዱ በፊት ውስጣዊ ሰላም ካልነበራቸው የልጁ ስም ምንዳዬ፤ ዋጋዬ፤ ትርፌ፤ ወንድማገኘሁ፤ አደናግር፤ አርጋው ወዘተ ሊሆን ይችላል። ሴትም ከሆነች ዓለምነሽ፤ ዓለሚቱ፤ ትርፍነሽ፤ እቴነሽ፤ ፋንታዬ፤ እታፈራሁ፤ ተገረሙ ወዘተ.. ይሰኛል።

ቤተሰቡ በማኅበራዊ ህይወቱ ወስጥ ፀብ አፍርቶ፤ ውጣውረድ ውስጥ ገብቶ ወንድ ልጅ ከተወለደም ለልጁ የሚወጣለት ስም የወደፊቱን የኃይል መምጣት አመላካች እንዲሆን ይደረጋል። ስለሆነም የልጁ ስም መክቱ፤ መከታዬ፤ በላቸው፤ ይደንግጡ፡ ይጨነቁ፤ ደም-መላሽ፤ ጭጭ ይበሉ፤ ጥላዬ፤ አጥላባቸው፤ ጋርጠው፤ ግረፌ፤ ዳምጠው፤ አጥርሁን፤ አላጋው፤ ዘርጋው፤ ድፈሬ፤ ተምትሚ ወዘተ ሊሆን ይችላል። የእነዚህም ዓለማዊ ስሞች አሰያየምም በአብዛኛው ሕዝቡ ያለበትን ታሪካዊ እና ባህላዊ ሁኔታ የሚጠቁም ይመስላል።

ቀደም ሲል ለማሳየት እንደተሞከረው ሕዝቡ የሰፈረው ሰሜን እና ደቡብ ኢትዮጵያን በሚያገናኘው የተራራ ሰንሰለት እና መተላለፊያ ላይ ነው። በመሆኑም አገሪቱን ለመግዛትም ይሁን ለማማከል ከሰሜን ወደ ደቡብ፤ ከደቡብም ወደሰሜን የተደረጉ ዘመቻዎች እና ጦርነቶች፤ የህዝብ መደበላለቆች ሁሉ ነክተውታል። ስለሆነም አካባቢው መማከቻም፤ መዋሃጃም፤ መመሸጊያም፤ መዋጊያም መሆኑ አልቀረም።

ስለዚህም ሕዝቡ ከአፈታሪክ እንደ ላሎ፤ማማ እና ጌራ የፈረሰኝነት እና የጦረኝነት ዘመቻ እና አገር አቅኚነት፤ ከታሪክ የአክሱም መንግሥት በአገው እና በቤጃ ንቅናቄ ሲደመሰስ የአንበሳ ውድም ወደ አካባቢው መሰደድ እና መሸሸግ (ማህተመ ሥላሴ 1965፤ ኪሮስ እና ማዘንጊያ 1972) ፤ የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ (1434 -1468)፤ የአፄ በዕደ ማርያም (1468-1478) ፤ የአፄ ልብነ ድንግል (1507-1540) በአካባቢው መዝለቅ፤ መቆየት፤ ልዩ ልዩ ተግባራትን ማከናወን Levine (እ.ኤ.አ 1972) ለሕዝቡ ህይወት ተሞክሮ ማለትም አፍቃሪ ወንድነት ወይም ጀግንነት መንፈስ መስረፅ አስተዋፅኦ ሳያደርግ አልቀረም። ይህም የወንድነት ወይም የጀግንነት መንፈስም ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ ይጠበቅ ዘንድ ዓለማዊ ስም አወጣጥ ወይም አሰያየም መሣሪያ ሆኖ ሳያገለግል የቀረ አይመስልም። ይህም አስተሳሰብ "ኅብረተሰብ የግለሰብ ሥራት እና ውጤት፤ ግለሰብም እንደገና የማኅበረሰብ ሥራት እና ውጤት ነው" የሚለውን የEitizin እና Zinn (1988:148-149) አባባል ያስታውሰናል።

በግዕዝ "እስመ ስሙ ይመርሆ ሀበ ግብሩ" ማለትም ስም ግብርን ይመራዋል እንደሚባለውም የላሎ-ማማ ሕዝብ እንደ ዓለማዊ ስሙ አሰያየም ሁሉ ስሙ ግብሩን ወይም

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ተግባሩን ሳይመራው የቀረ አይመስልም። የሕዝቡን በቀላሉ ለግጭት ተጋላጭነት እና ደም ተቃቢነት ህይወትም ቀደም ሲል የተዘረዘሩት ስሞች በመጠኑም ቢሆን የሚጠቁሙ ይመስለኛል።

ሁለተኛው ዓይነት ስም መንፈሳዊ ወይም የክርስትና ስም ነው። ይህ ስም ለወንድ ልጅ በተወለደ በአርባኛው ቀን፤ ለሴት ልጅ ደግሞ በተወለደች በሰማኒያኛው ቀን በቤተክርስቲያን ውስጥ ሲጠመቁ የሚሰጣቸው ስም ነው። ይህም ስያሜ የመላዕክቱን የሐዋርያቱን፤ የሰማዕታቱን ወዘተ ባህርይ እና ግብር ወይም ሙያ ስሙ ለሚሰየምላቸው ህፃናት የሚያወራርስ ነው። ስለሆነም በህፃኑ የወደፊት ህይወት ላይ የመላዕክቱ፤ የሐዋርያቱ እና የሰማዕታቱ የሀያልነት፤ የገባሬ ተአምርነት መንፈስ ይረብባቸው ዘንድ ይተነበይላቸዋል።

ሦስተኛው ዓይነት ስም የሞጋሳ ስም የሚባለው ነው። ይህ የሞጋሳ ስም የሚሰየመው ክፉ እና በጐውን ለለዩ ሰዎች ነው። የስሙም አወጣጥ ስሙ የሚወጣለት ሰው ጠባይ፤ ዓመል፤ ባህርይ፤ መልክ፤ ቁመና፤ ሙያ እና ወንድነት እንዲሁም ትወልደ-ሐረግ ማለትም የአካባቢውን የርስት አባቶች ስም መሠረት ሊያደርግ እና ሊይዝ ይችላል (አቶ ገብረወልድ ገ/ዓድቅ እና አቶ መንግሥቱ አማረ በ18/5/99)።

ከሞጋሳ ስያሜዎቹም ውስጥ አንድን ሰው ለማመስገን፤ ለማወደስ ጥቅም ላይ የሚውሉ አለባቸው። ለምሳሌ ወንድነትን (masculinity) ሥራ ወዳድነትን፤ ሐቀኝነትን፤ የሰው ንብረት፤ ሀብት እና ሴት አለመፈለግ እና አለመንካትን የሚገልጹ አሉ። በዚህም መሠረት ወንድነት አባ ናዳ፤ አባ ተምትም፤ አባ ሰይጣን፤ አባ ጠፍር፤ አባ ጐንጥ፤ አባ ኮስትር፤ አባ ሽንቁጥ፤ አባ ገስጥ፤ አባ ጋተው፤ አባ ስበር፤ አባ መርዞ ወዘተ ያሰኛል።

ሥራ ወዳድነትም አግተምትም፤ ማለዴ፤ ገስግሴ፤ አጭበድብድ ወዘተ ያስብላል። እንዲሁም ሀቀኝነት አባ ሚዛን፤ አባ ሰላም፤ አባ ክብካብ፤ አባ መሬት፤ አባ ጤና፤ አባ ማር አይልሴ ወዘተ እያሰኘ ያስማማል። በአንጻሩም እነዚህን ባህርያት የማያሟላ ሰው በአሉታ ይለበጣል ወይም ይሰደባል።

ከላይ ከተጠቀሱት ሦስት ዓይነት ዓለማዊ፤ መንፈሳዊ (የክርስትና) እና የሞጋሳ የላሎ-ማማ ሕዝብ ስሞች ሁሉ ግን በይፋ ወይም በገሃድ እና በስፋት የሚደመጠው ዓለማዊ ስም መሆኑን እናያለን።

2.6. የሥራ ባህል

የላሎ-ማማ ሕዝብ ዋነኛ የጉልበት መዋያ ወይም የጉልበት ማፍሰሻ ሥራ ግብርና ነው። ግብርናም የሕዝቡ የምጣኔ ሀብት ዋነኛው ምንጭ ነው። ስለሆነም በዓመት ከሁለት

እስከ ሦስት ጊዜ ድረስ ለምነቱ በተመናመነ መሬት ላይ ሰብል ለማልማት የላቀ ብርቱ ጥረትን ይሻል። ማሳን በሰብል ለማንገርገግ፤ ለማጠንዘል ውደማን ለማደመቅ ጉተራ እና ቡሀቃን ለመሙላት ገስግሶ ማልዶ መጥመድ፤ ማረስ፤ መጎልጎል፤ ማለስለስ፤ አለስልሶ መዝራት፤ ዘርቶ ማረም፤ የደረሰውን መሰብሰብ ታታሪነትን ይጠይቃል።

በጥረት አርሶ አዝምሮ ወቅቶ ቤተሰብን መመገብ መቻል "ራሱን ያውላል፤ ራሱን አይጥልም" ያሰኛል። ከራስ አልፎ ለሌላው መትረፍ ደግሞ "ባለፀጋ፤ የአገር አዋይ፤ የአገር አባት፤የአገር ሲሳይ" ያስብላል። በእነዚህ ደረጃዎች አለመገኘት "ድኃ፤ ራት የለሽ፤ ወትሮ እዬዬ፤ ሰነፍ፤ ማጋጣ፤ ማላጋ፤ ትርንኩስ፤ ሙያተኛ (ለማኝ)" ወዘተ የሚል ዘለፋ እና ለበጣን ያስከትላል። ስለሆነም ታታሪ ገበሬነት የሙያ ቁንጮ ተደርጐ ይወሰዳል። ግብርና ዋነኛው የላሙ-ማማ ሕዝብ መሰማሪያ ይሁን እንጂ ሌሎችም እንደ ግብርና የሚከበሩ በአንፃሩም ደግሞ የሚንቋሸሹ የሥራ ዓይነቶች አሉ። ከግብርና ቀጥሎ ወንዶችን የሚያስከብሩ ሞያዎች ተደርገው የሚታዩት ገንቢነት እና ከዳኝነት ናቸው።

ከገንቢነት እና ከከዳኝነት በመቀጠል ደግሞ ዘወትርም ባይሆን አልፎ አልፎ እንደተወሰኑ የወንዶች ችሎታ ተደርገው የሚታዩት ሞፈር፤ ቀንበር፤ ድግር፤ ዛቢያ መቁረጥ እንዲሁም እነዚህን የግብርና መሣሪያዎች መጥረብ እና ማቃናት መቻል ናቸው። እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የሥራ ዓይነቶች ወይም ሙያዎችም በተለያየ ደረጃም ቢሆን የሚያስከብሩ ናቸው ማለት ይቻላል። ከነዚህ ሌላ ግን አሁንም ከላይ ለተጠቀሰው የግብርና ሥራ እጅግ መሠረታዊ እና አስፈላጊ የሆነው ወንዶች የሚሰማሩበት የብረት ሥራ ማለትም ማረሻ፤ ወገል፤ ዶማ፤ መጥረቢያ፤ ቢላዋ፤ ወስፌ፤ ወዘተ መሥራት "ቀጥቃጭ" ያሰኛል። ይህን የሚሰሩ ሰዎች "ቀጥቃጭ" ከመሰኘታቸውም በላይ ቤተ-ሐረጋቸውም በ"ጠይብነት፤ ቡዳነት" ይታማል፤ ይፈረጃል። በጋብቻም ለመተሳሰር ብዙ አይፈቀዱም፤ አይመረጡም የሚል አስተሳሰብ አለ።

ከ"ቀጥቃጭነት" ተርታ የሚፈረጀው ሌላ ሙያ ሽክላ-ሰሪነት ነው። ሽክላ ሥራ በመጠኑ ወንዶች በብዛት ደግሞ ሴቶች የሚሰማሩበት ነው። ሽክላ ሰሪዎች ህዝቡ ቆሎ፤ ንፍሮ፤ እንጀራ፤ ዳቦ፤ ወዘተ አብስሎ፤ የሚበላበትን ረጅት፤ ምንቸት፤ ምጣድ፤ ገበር-ምጣድ እንዲሁም ውኃ ቀድቶ፤ ቡና አፍልቶ ጠላ ጠምቆ አረቄ አውጥቶ የሚጠጣበትን እንሥራ፤ ጀበና፤ ጋን፤ ወዘተ እንዲሁም የቤቱን ሞገስ ጭምር ሰርተው የሚያቀርቡ እና የሚያደምቁ ይሁኑ እንጂ የሚሰጣቸው ማኅበራዊ ክበሬታ ከ"ቀጥቃጮች" የተለዬ አይደለም። እንዲያውም የብረታ ብረት እና የሽክላ ሥራ ባለሙያዎች "ቀጥቃጭ" ከመሰኘታቸውም በተጨማሪ "ጠይብ" እና "ቡዳ" ተብለው ይፈረጃሉ። "ሰውን ይበላሉ" እየተባሉም ይፈራሉ፤ ይጠላሉም፤ ይሸሻሉም። እነርሱም ይህን በመገንዘብ ይመስላል ብዙ ጊዜ

ከንብረተሰቡ ጋር አብረው እና ተስማምረው ሰፍረው አይገኙም። በወረዳው ውስጥ ዋናው መኖሪያቸው ሽየት ቆላ፤ ደዋ እና ጋዲ ቀበሌዎች ወሰን ላይ በሁለቱም ቀበሌዎች ውስጥ በድንበርተኝነት እንዲሁም ኑሪትና ብያ ውስጥ ልዩ ስሙ ሙራ ሥላሴ በተባለ አካባቢዎች ነው። (አቶ ግርማ ይታፈር የወረዳው አፈጉባኤ 24/5/1999)።

ከነዚህ የሥራ ዓይነቶች በመቀጠል ደግሞ ሽማኔነት እና ቆዳ አልፊነት ይገኛሉ። ሽማኔዎች ከጥጥ እና ከበግ ፀጉር የሚሰሩትን የህዝቡን የቀን እና የሌሊት ልብሶች ሁሉ የሚሠሩ እና የሚያቀርቡ ቢሆኑም ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ሙያተኞች ማለትም ብረት ሰሪዎች እና ሽክላ ሰሪዎች በባሰ ሁኔታ ዝቅ ተደርገው የሚታዩ ናቸው። ሥራዎቹም ብዙውን ጊዜ እንደ ስንፍና እና እንደ ድህነት መዋያ ተደርገው ይታያሉ።

የመጨረሻው ከበሬታ-ያለሽ ሥራ የሚመስለው ደግሞ ቆዳ አልፊነት ነው። ቆዳ አልፊዎች በተለይ የበሬ ቆዳን አልፍተው ለጠፍር፤ ለመጫኛ ለቁርበት (ለመኝታ እና ለነዶ መጠቅለያ እና መጫኛ የሚያገለግል) የሚያበቁ ባለሙያዎች ናቸው።

የሴትነት ሙያን በተመለከተ የሴት አምስትያ የሚያሰኘው የተዋጣለት ነጭ መጋገር፤ የነተረ የዶሮ ዓይን የመሰለ ጠላ መጥመቅ፤ "እጅ ያስቆረጥማል" የሚያሰኝ ወጥ መሥራት፤ ውኃ የመሰለ ካቲካላ ማውጣት፤ ቀጭን መፍተል መቻል ነው። ከነዚህ ከተጠቀሱት የሴትነት ሙያ መለኪያዎች መለስ ሲልም "አንዱ ቢሳታት ሌላው አይሳታትም" የሚባሉ አሉ። እነዚህኞቹ ሴቶች ቆንጆ እንጀራ ቢጋግሩ ወይ ወጣቸው ወይ ጠላቸው ብዙም የማይደነቅላቸው ዓይነቶቹ ናቸው።

የላሎ-ማማ ሴቶች ሙያ ወይም ባለሙያነት ዘወትር የሚለካው ግን በቤት ውስጥ የባልትና ዝግጅት ችሎታ ብቻ አይደለም። የቤቱንም የዱሩንም ሥራ ቀጥ አድርገው የሚመሩም ይገኙባቸዋል። እነዚህኞቹ ዓይነቶቹ ሴቶች የቤቱንም የዱሩንም ተግባር በብቃት እየተወጡ ትዳራቸውን የሚመሩ በመሆናቸው "የሴት ወንድ፤ የሴት አውራ፤ የሴት ቁንጮ" ወዘተ ይሰኛሉ። የሴቱንም የወንዱንም ተግባር ጠንቅቀው በማወቃቸው የሚሰናቸው ነገር የለም ይባላል። ብዙዎቹን "የሴት ወንድ" የሚያሰኛቸው እንደ ወንድ በሬ ጠምደው፤ በማረሳቸው፤ በመዝራታቸው ወይም በማጨዳቸው አይደለም የሚመሰገኑት፤ የሚሞገሱት። የእርሻ፤ የአዝመራ፤ የሰብል ስብሰባ ወቅቱን ጠብቀው ባሎቻቸውን፤ ቤተሰቦቻቸውን አነቃቅተው ለሥራ እንዲተጉ በማነቃነቃቸው ሠራተኞቻቸውን በሥራ ገበታቸው ላይ ተገኝተው በመመገባቸው እና በማትጋታቸው ነው።

በአጠቃላይ እንዲህ ዓይነቶቹ ሴቶች የዱሩን ወይም የግብርናውን ሥራ ለባሎቻቸው ባልም ከሌላቸው ለገበሬያቸው የሚተው አይደሉም። ይልቁንም እንደ አንድ ትጉ ገበሬ የግብርና ሥራቸውን የሚከታተሉ እንጂ።

2.7. አሰፋፈር እና የቤት አሰራር

ላሎ-ማማ ውስጥ ቤት የሚሠራው ጠፍ (ለምነት የሌለው) መሬት ታይቶ፤ ኮረብታ ወይም ገብታ ወይም ተገንነት ያለው ጥጋት ቦታን ተንተርሶ ወይም ተጠግቶ ነው። ይኸውም የሚደረገው የእርሻ ቦታን ለመቆጠብ፤ ነፋስን ለመከላከል ዙሪያ ገባውን ለመቃኘት እና ለመቆጣጠር ነው።

በአብዛኛውም ቤቶቹ የሚሰሩት በድንጋይ ሲሆን በአመድ እና በአፈር ጭቃም ይገነባሉ፤ ከውስጥም ይመረጋሉ። በቆላ አካባቢ አልፎ አልፎ የግድግዳ ቤቶች ይገኛሉ። የቤቶቹ አገነባብ ወይም አገዳገድም ባብዛኛው ክብ አልፎ አልፎም ሞላላ ቅርፅ ይይዛል። ጣራቸው ከተቻለ በጥድ፤ ካልሆነም በባህር ዛፍ ምሰሶ ይደገፋል። የጣራው ወራጆችም እንዲሁ ጥድ ወይም የባህር ዛፍ እንዲሆኑ ይደረጋሉ። ሳጋቸው ባብዛኛው ባህርዛፍ ነው። ክዳናቸው ብርዕ፤ ሰንበሌጥ፤ ጓሳ፤ ድርፍ ይሆናል። በአብዛኛውም በየደጁ የቆርቆሮ ክዳን ያላቸው ቤቶች አሉ። የቤቶቹ አሠራር ዓይነት እና ብዛትም የባለቤቱን ማኅበራዊ ደረጃ ጭምር የሚገልጹበት ሁኔታ አለ። አዳራሽ (በዙሪያ ጓዳ ወይም ያለ ዙሪያ ጓዳ)፤ እልፍኝ (ምድር ወይም ፎቅ) በሳር ወይም በቆርቆሮ የሚከደን፤ ክብት ቤት፤ ጋጣ (የጋማ ክብት ማደሪያ)፤ እሪቅ (ጉተራ) ቤት እንዲሁም የገለባ እና የድርቆሽ ቤት ያለው ሰው የናጠጠ ሀብታም ተደርጐ ይቆጠራል። የአንድ ሰው ማኅበራዊ ደረጃ በቤት ዓይነት እና ብዛት ብቻ አይገለፅም። ሆኖም በአመዛኙ ከሀያ በላይ በጐች፤ ጥንድ ወይም ከዚያ በላይ ላሞች እና በሬዎች (ጥንድ፤ ጥንድ ከቅንጃ ሁለት ጥንድ) የጭነት እንሰሳት፤ "የጭን በቅሎ ወይም ፈረስ" የሌለት ሰው አላይ የተጠቀሱት ቤቶች አይኖሩትም። ከላይ የተዘረዘሩት ቤቶች ቁጥር እና የቤት እንሰሳት ቁጥር መቀነስ የጥራጥሬ ምርትም መቀነስ ጠቋሚ ሆኖ ይወሰዳል። በዚህም የተነሳ ሕዝቡ እርስ በርሱ ሀብታም፤ እራሱን የማይጥል (መካከለኛ ገበሬ ለማለት ነው) እና እራት የሌለው (ድኃ ለማለት ነው) በመባባል ይፈራረጃል።

በሀብታምም፤ በመካከለኛም፤ ሆነ በድህነት የሚፈረጁት አርሶ አደሮች ቤቶቻቸውን የሚሠሩት ከሌላው ሰው ቤት ነጠል፤ ራቅ፤ ፈንጠር ብለው ነው።

አልፎ አልፎ የአንድ ቤተሰብ ተወላጆች በአንድ አካባቢ በመደዳ ወይም በክብ መንደር መሥርተው የሚኖሩ ቢሆኑም ባብዛኛው ህዝቡ ተናጠላዊ አሠፋፈርን ይፈቅዳል። ይከተላልም። ተናጠላዊ አሰፋፈሩም ለክብት ሥምሪት እንደሚበጅ በዶሮ፤ በውሻ፤ በክብት አፍ፤ በልጆች ወዘተ ሊመጣ ከሚችል ነገር እና መጐነታተልም ሊያድን እንደሚችል ይታመናል።

2.8. ኢኮኖሚያዊ ገጽታ

የላሎ-ማማ ሕዝብ የሰፈረበት አካባቢው ቀደም ብሎ እንደተገለፀው ደጋ፣ ወይና ደጋ፣ እና ቆላ የሚባለውን የአየር ንብረት ያካትታል። ሜዳም፣ ተራራም፣ ገደልም፣ ሸለቆም፣ ሥርንጉጥም፣ ያካተተ በጐርፍ የታጠበ፣ ለምነቱ የተመናመነ ቢሆንም በዓመት ከሁለት እስከ ሦስት ጊዜ ማምረት ያስችላል። አፈሩ በአብዛኛው ጥቁር እና ቀይ ነው። ዓይነቱን መረፌ እና አቦልሴ ይሉታል። ዋነኞቹ የወረዳው የብርዕ ሰብሎች በቅደም ተከተል ስንዴ፣ ገብስ እና ጤፍ ሲሆኑ እንደዚሁም በብዛት የሚመረቱት የጥራጥሬ ሰብሎች አሁንም በቅደም ተከተል ባቄላ፣ አተር፣ ምሥር አብሽ ናቸው (አቶ ኃይሉ እሸቱ በ22/5/99)።

መስከረም ላይ ባለው ርጥበት እና ዝናም በደጋው እና በወይና ደጋው አካባቢ አምኜ (አምኜ ማለት ፈጣሪን አምኜ ማለት ነው መጪው ጊዜ ቀዝቃዛ፣ እና ድርቅ ስለሆነ) ይዘራል ባብዛኛው የሚዘራው ገብስ እና ስንዴ ነው።

ከታህሣሥ መጨረሻ እስከ የካቲት ባለው ጊዜ ውስጥ ብዙውን ጊዜ የበልግ ዝናም ስለሚጥል በደጋው እና በወይና ደጋው ላይ በልግ ይዘራል። በበልግ አዝመራ በከፍተኛ ደረጃ የሚዘራው በቅደም ተከተል ማለት ይቻላል ገብስ፣ ስንዴ ባቄላ አተር፣ ምሥር ነው። በቆላማው አካባቢ ጤፍ፣ ዘንጋዳ፣ ማሽላ፣ በቆሎ፣ አደንዝራ እና ሌሎችም ሰብሎች ይዘራሉ።

በሚያዚያ እና በግንቦት በሚጥለው መለስተኛ ዝናብ የደጋ እና የወይና ደጋው፣ ከሰኔ እስከ መስከረም ደግሞ የቆላው ህዝብ የመኸር ሰብል ይዘራሉ። ከፍተኛው የአዝመራ ጊዜም ይሄ ወቅት ነው። በዚህም መሠረት በአምኜነት የተዘራው በጥር እና በየካቲት፣ በበልግነት የተዘራው በሰኔ እና በሐምሌ፣ በመከርነት የተዘራው ደግሞ በጥቅምትና በህዳር ይሰበሰባል። በሁሉም አካባቢዎች በሁሉም የአዝመራ ወቅቶች በአንድ ማሳ ላይ ተመሣሣይ ሰብል በተደጋጋሚ አይዘራም። ይፈራረቃል። ይህም ለመሬቱ ለምነት መጠበቅ እና ለሚገኘውም ምርት መጨመር አስተዋፅኦ እንዳለው ይነገራል።

በአትክልት ረገድ ነጭ እና ቀይ ሽንኩርት፣ እንዲሁም ጐመን በንሮ አትክልትነት በሁሉም የአየር ንብረት ውስጥ ይለማል። በወይና ደጋው እና በቆላው አካባቢ ደግሞ መጠነኛም ቢሆን ጌሾ፣ ቡና፣ በርበሬ፣ ሙዝ፣ ሽንኩራ፣ ፓፓያ እና ኩክ ወዘተ ይበቅላል (አቶ ኃይሉ እሸቱ በ22/5/99)።

ሌላኛው የወረዳው ዋነኛ የሀብት ምንጭ እና የምግብ ፍጆታ መደገፊያ የእንስሳት እርባታ ነው። ሁሉም አርሶ አደር እና ከተሞች ተብለው በሚጠሩት ውስጥም ጭምር

የሚኖሩ ሰዎች ላም እና በጐች እንዲኖሯቸው ይጥራሉ። በተለይ አርሶ አደሮች ኑሮ ማላሚያ (ኑሮ ማልሚያ ለማለት ነው) ብለው ኑሮአቸውን የሚጀምሩት ዶሮ፣ በግ፣ ፍየል፣ ላም፣ በሬ፣ አህያ፣ ፈረስ በማርባት ነው። ብዙዎቹ በቅደም ተከተል ማለት ይቻላል በጐች፣ ዶሮዎች፣ ላሞች እና በሮች አሏቸው። ከበጐቹ እና ዶሮዎቹ የዓመት በዓል እና የአምሮት እርድ፣ እንዲሁም ከሽያጫቸው ብር ያገኛሉ።

በወረዳውም ውስጥ ሕዝቡ ምርቶቹን ለሽያጭ የሚያቀርብባቸው እንዲሁም የሚያስፈልገውን የሚገዛባቸው ቅዳሜ፣ እሁድ፣ ማክሰኞ እና ሐሙስ የሚቆሙ (ሞላሌ፣ ወገሬ፣ ይገም፣ መለያያ፣ ባሽ (ወይን በር)፣ ቆሎ ማርገፊያ፣ ሸሾ ወዘተ) ገቢያዎች አሉ።

ከላሞቹ እርባታ ጊደር፣ ወይፈን፣ ያገኛሉ። እነርሱንም ለእላቢ እና ለእርሻ ይጠቀሙባቸዋል። ቅቤው ብዙውን ጊዜ ለገበያ ይቀርባል። አልፎ አልፎም አንዳንድ አርሶ አደሮች ከሦስት እና አራት የማይበልጡ ቀፎዎች ይሰቅላሉ። ከነርሱም ለገበያ የሚሆን ማር ይቆርጣሉ። በአጠቃላይ ለገበያ ከሚውሉት እንሰሳት እና የእንሰሳት ተዋፅኦዎች ነዋሪዎቹ እንደሚሉት "መላበሻ፣ ጨው በርበሬ እና የኪስ አዋይ" ያገኛሉ። (የኪስ አዋይ ትንሽ ብር ነው)። አህዮችን ለጭነት ፈረሶችን ለእርባታ በቅሎዎችን ለግልቢያ መጠቀምም የተለመደ ነው። ፈረሶች በተለይ በደጋው አካባቢ ለእርሻ ሥራም ያገለግላሉ።

2.8.1. አመጋገብ

የላሎ-ማማ ህዝብ ከሞላለት አዘውትሮ ጥዋትም ማታም የሚመገበው የገብስ፣ የስንዴ፣ የጤፍ እንጀራ ነው። ማባያው አሁንም ሲመች ቀይ እና አልጫ ወጥ ነው። ስንዴ ለዳቦም ይሆናል። የማባያው ወጥ ሽሮ እና ክክ ከባቄላ፣ ከአተር፣ ከሽንብራ፣ ከጓያ ይገኛል። አራት አሁንም ለተመቸው ሰው ከገብስ በሚሰራ ደረቅ ቂጣ፣ ወይም ጥረሽ በጠመኝ ወይም በፍትግ ገብስ ቆሎ፣ በባቄላ ወይም፣ አተር አሹቅ ወይም ንፍሮ መደላድል ይታጀባል።

ከዓውደ-ዓመት መካከልም ዘመን መለወጫ በአንድ ወይም በጥንድ ዶሮ (በባልና ሚስት ስም)፣ በበግ መክት፣ በዳቦ፣ በጠላ እና ካቲካላ (አረቂ) ያልፋል። መስቀል በዳቦ እና በጠላ ይሸኛል። ገና በበግ መክት፣ በዳቦ፣ በጠላ፣ ካቲካላ (አረቂ) ይዋላል። ትንሳኤ ለተሳካለት በፍየል መክት፣ በጠላ፣ በካቲካላ (አረቂ) ይፈሰካል። አብዛኛውም በበግ፣ በዳቦ እና በጠላ ያሳልፈዋል። ዝቅ ያለው ከዚህ ባነሰ።

የብዙኃኑ ሕዝብ ባህላዊ መጠጥ ጠላ እና ካቲካላ (አረቂ) ነው። ኑሮ ሲያስቸግር ደግሞ በገብስ፣ በስንዴ እና በጤፍ ቦታ ዘንጋዳ፣ ባቄላም፣ አተርም፣ ሽምብራም፣ ማሽላም እንጀራ ይሆናሉ። በጠላ፣ በጠጅ፣ በአረቂ፣ ፈንታም ቅራፊ፣ ውኃ ገብ እና ውኃ የጉረሮ ማወራረጃ ይደረጋሉ።

2.8.2. አለባበስ

የላሎ-ማማ ሕዝብ ሦስት ዓይነት ልብሶች አሉት። እነሱም "የሰርክ" ማለትም የዘወትር ወይም የሥራ ልብስ፤ "የክት" ወይም "የደጅ መውጫ" ማለትም የአደባባይ ልብስ እና "የገዜ" ወይም "የርጅት" ልብስ የሚላቸው ናቸው። "የገዜ" ወይም "የርጅት" ልብስ የሚባሉትም የሴት እና የወንድ ተብለው ይከፈላሉ። የወንድ "የገዜ" ወይም "የርጅት" ልብስ የሚባሉት ነጭ ሱሪ፤ እጀ ጠባብ፤ ነጭ ሻሽ፤ ከጥጥ ፈትል የሚሠራ አፍሪካ ወይም ዝንጉርጉር ጥብቆ፤ ነጭ ዝተት፤ ጥቁር ዝተት፤ አፍሪካ ዝተት፤ ጉዳ ቡልኮ፤ ጥለታም ቡልኮ ወዘተ ሲሆኑ የሴት "የገዜ" ወይም "የርጅት" ልብስ የሚባሉት ደግሞ ጥቁር መላወሻ፤ ዝንጉርጉር መላወሻ፤ ጉፍታ፤ አንገት ልብስ፤ ከጥጥ ፈትል የሚሠራ ዝንጉርጉር ጥብቆ ጥለታም ብልኮ፤ ነጭ ሻሽ ወዘተ ናቸው (ቃለ-መጠይቅ አቶ ገብረወልድ ገ/ዓድቅ እና አቶ መንግሥቱ አማረ በ18/5/99)።

የሕዝቡ አለባበስ እንደአየሩ ሁኔታ የተለያዬ ነው። በደጋ፤ በወይና ደጋም ሆነ በቆላ የሚኖሩ ጠና ያሉ ወንዶች እጀ ሙሉ ወይም ጉርድ የአቡጀዲ ጥብቆ እንዲሁም ከአቡጀዲ፤ አቃቂ እና ካኪ የሚሰፉ እስከተረከዝ ወይም ባት ላይ የሚደርሱ ተነፋነፍ ሱሪዎችን ይታጠቃሉ። አልፎ አልፎም ኮት ይደርባሉ። ወጣቶች ጥብቆ እና ቱምጣ ይለብሳሉ። አዋቂዎችም ሆኑ ወጣቶች የጉማ ጫማ ወይም ጥልፍልፍ ይጫማሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ሸራ፤ ቦት፤ እና ቆዳ ጫማ ያደርጋሉ። እነዚህኞቹ ቦላሌ ሱሪም ይደፍራሉ። አዛውንቶችም ሆኑ ወጣቶች ከራሳቸው ላይ ሻሽ፤ የጥለት ቆብ ወይም ጥምጣም አያጡም። በተለይ ደገኞቹ ዓይናቸው ብቻ እንዲታይ አድርገው ነጠላ፤ ጋቢ፤ ብርድልብስ እንዲሁም ከያንዳንዱ ቤት የጠፍር አልጋ እና መደብ ላይ የማይጠፋውን ዝተት ወይም ባና ይከናነባሉ። ይህ ዝተት ወይም ባና እስከ ቅርብ ዓመታት (አሥር እና አሥራ አምስት ዓመታት በፊት ድረስ ማለት ይቻላል) ዋነኛው የደገኞች የላይ ወይም የጥፊያ (የሚጣፋ) ልብስ ነበር። ይህ ዝተት ወይም ባና የሚሠራው ከበግ ፀጉር ሲሆን ዓይነቱም ብዙ ነው። ጥቁር፤ ነጭ፤ አፍሪካ ወይም ዝንጉርጉር እና የሁሉም ዝንቅ ወይም ድብልቅ የሆነው ባና ይገኙበታል።

በተለይ ጥቁሩ የበግ ፀጉር በአካባቢው ከፍተኛ ከበሬታ ለሚሰጠው በርናስም ይውላል። በርናስ እጅግ ንፁህ የሆነው ጥቁር ፀጉር በእውቅ ሰላላ መላላ እንዳይኖረው ተደርጎ ተፈትሎ፤ ተሸምኖ እና ተረግጦ በባህር አረብ ተዘምዝሞ በደስታ እና በሀዘን (የውስጡ ወደ ላይ ተገልብጦ) የሚለበስ የማዕረግ ልብስ ነው።

ዝተት ወይም ባና የላሎ-ማማም ሆነ የደገኛው መንዝ ህዝብ ጠንካራ የብርድ መከላከያ ልብስ ከመሆኑም በላይ በዱላ (ድብድብ) ጊዜ እንደ ጋሻ የሚመከት ነው (አቶ ሸዋይርጋ አስፋው በ11/5/99)። በአጠቃላይ በደጋ፤ በወይና ደጋም ሆነ በቆላማው የላሎ-ማማ

ህዝብ መኝታ ላይ በሌሊት ልብስነት የማይጠፋው ዝተት ወይም ባና እንደ ደጋው ሁሉ በወይና ደጋ እና ቆላ ነዋሪዎች ዘንድ ቀን አይለበስም። የወይና ደጋ እና የቆላ ሰዎች ቀን የሚለብሱት ከጥጥ ፈትል የሚሠራውን ነጠላ ጋቢ እና ቡልኮ ነው።

ቀደም ባለው ጊዜ ጋቢ እና ቡልኮ ለደጋ ሰዎች የስመ-በዓል እና የገበያ፣ የመንገድ፣ ልብሶች የነበሩ ቢሆኑም ዛሬ ዛሬ የዘወትርም እየሆኑ መጥተዋል። የደጋ ሴቶች ቀደም ባለው ጊዜ ከላይ የተገለፀውን የቀድሞ የደገኛ ወንዶች ልብስ ማለትም ዝተት በመላዋሸነት (ከወገብ በታች የሚጠለቅ የዝተት ቀሚስ) ይታጠቁ ነበር። ለዚህ ይመረጥ የነበረውም ጥቁር ዝንጉርጉር ወይም አፍሪካ እና ነጭ ቀለም ነበር። ከውስጥ የአቡጀዲ ወይም የጥጥ ፈትል ጥብቆ ከላይ ሻሽ፣ አንገት ልብስ፣ ነጠላ እና ጋቢ ያጣፋሉ። አልፎ አልፎም ዝተት። የወይና ደጋ እና የቆላ ሴቶች ቀድሞም ሆነ ዛሬ ዝተትን ቀን አይለብሱም። የተለመደው የጥጥ ፈትል ውጤት እንዲሁም አቡጀዲ፣ አቃቂ፣ ኮሪያ ወዘተ የተሰኙ ጨርቆችን ቀሚስ ማድረግ ነው። በስመ-በዓላት በገዙ ወይም መንገድ በገበያ ቀናት ሴቶች ዙሪያ፣ ጐዳ፣ ጥልፍ ቀሚስ ይለብሳሉ። ነጠላ ወይም ኩታም ይደርባሉ። ልጆች በደጋም፣ በወይና ደጋም ሆነ በቆላ ባብዛኛው የአቡጀዲ ጥብቆ ይለብሳሉ። ልጆች ከሶስት እና አራት ዓመታት ዕድሜ በኋላ ደግሞ ከአቡጀዲ፣ ከአቃቂ ጨርቅ የሚሰፋ ቁምጣ ይታጠቃሉ።

የላሎ-ማማ ሰው ሀብታምም ይሁን ድኃ ሲሞት አስከሬኑ የሚሸፈነው በቤት ፈትል ጋቢ ወይም ቡሉኮ ነው።

የላሎ-ማማ ወንዶች በተለይ ከእጃቸው ወይም ትከሻቸው ላይ ዱላ ወይም በትር አያጡም። ዱላው ወይም በትሩም ጥዬ፣ ወይራ፣ ጥፌ፣ ክትክታ፣ መዛዝይ ወዘተ ከሚባሉ ዕፅዋት የሚቆረጥ ነው። ጐልማሶች እና ወጣቶች የሚይዙት ዱላ ወይም በትር ጭስ የጠገበ፣ ላት የጠጣ፣ በጐመድ የተጐለበ እንዲሆን ይደረጋል።

ሌላው የላሎ-ማማ ሰው በጠቅላላው ማለት እስከሚቻል ድረስ የጠመንጃ ፍቅር አለው። ጠመንጃን የወንድነት ክብር መጠበቂያ አድርገው ይቆጥራል። ይሁንና ይህን የሕዝቡን የጦር መሣሪያ የመያዝ ፍቅሩን ደርግም ኢሕአዴግም አጨናግፈውበታል። እዚህ ላይ ስለዚህ ስለ ትጥቅ ጉዳይ አንድ ጐልማሳ ያወጉኝን እጠቅሳለሁ። "ደርግም ኢሕአዴግም እግራቸው ቤተመንግስት እንደረገጠ ትጥቃችንን ምንጥር አድርገው አስፈትተውናል። ዛሬ ሰውነት የለንም በተለይ በኢህአዴግ ተገፈናል። ሌላው ቀርቶ በሬ መጥቢያ (ማረጃ ለማለት ነው) ደህና ቢላዋ አልቀረንም።"

2.9. ዓለማዊ አተያይ

የላሎ-ማማን ሕዝብ መንፈሳዊ ህይወት የሚመሩ ገናና ማለትም ይፋዊ (ገዛዳዊ) እና ተዛነቃዊ ወይም ተሰባጣሪ እና ተዳባይ ልማዳዊ እምነቶች እንዳሉት ሁሉ ዓለማዊ (worldly) አስተሳሰቡን እና ግብሩን የሚመሩ ወይም የሚገዙ እምነቶችም አሉት። ከነዚህም አንዱ ወንድነት (masculinity) ነው። ወንድነት በተለያዬ መንገድ ይገለጻል። አንደኛው መገለጫውም አለመጠቃት፣ ከተጠቁም ጥቃትን መወጣት ወይም መበቀል ነው። ስለዚህም ሕዝቡ ወንድነት በገዳይነት መገለፅ እና መረጋገጥ እንዳለበት ማመኑን ለገዳይ በሚሰጠው ከበሬታዊ አገላለጽ ያሳያል።

ጥቃት የማያስገባን፣ ከተጠቃም ጥቃቱን የሚበቀል እና የሚወጣን ሰው እኸሌ "ወንድ ነው፣ የወንዶች ባል፣ የወንዶች አውራ፣ የወንዶች ቁንጮ፣ ጀግና፣ ጎይለኛ፣ ጉበዝ፣ ቀብራራ፣ ቆፍጣና፣ደፋር፣ ሐሞተ ኩሩ" ወዘተ እያሉ ይገልፀታል። ይኸው ጀግነነትም በምሳሌያዊ ንግግርም በተረትም በሽለላም ይገለጻል።

ከምሳሌዊ ንግግሩ ልጠቃቅስ፡-

ሞት ላይቀር ፍርሃት
ዓመል ላይተው ቅጣት

ረጅም በትር ባይመቱበትም ያስፈራራል
ጀግና ባያርስም ስሙ ያሳድራል
ከውርደት ሞት ይሻላል።

ተረትም ይተረታል።

"አንበሳ ምንን ትፈራለህ ቢሉት አርጅናን፣
ጀግና ምንን ትፈራለህ ቢሉት ጥቃትን።"

ወንድነት በሽለላም ይሞገሳል።

"ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ አንዳባቱ፣
ስጠት አመልማሎ ይፍተል እንደናቱ።"
"ኧረ ጥራኝ ጫካው ኧረ ጥራኝ ዱሩ፣
ላንተም ይሻልሃል ብቻ ከማደሩ።"

ይህ ዓይነቱ የወንድነት ወኔ በወንዶች መቀንቀን የሚጀምረውም ገና በጠ፣ በፍየል እና በከብት እረኝነት ዕድሜ ላሉ ነው። ምክንያቱም በላሎ-ማማ ህዝብ ዘንድ ወንድነት በአርስ በርስ ግንኙነት ውስጥ ጣራ የነካ ወይም የደረሰ ከበሬታ እና ማዕረግ ያስገኛል።

በአንጻሩ ፈሪነትም "ቦቅቧቃ፣ ላም፣ የእግዜር በግ፣ አይመረው አይተኩሰው፣ ነሁላላ፣ ፈዛዛ፣ መትቻ፣ ከሪፎ፣ ድንዝዝ፣ ሆዳም፣ አራም፣ቅዘኖ ወዘተ" ያሰኛል። ስለሆነም ፈሪም በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ይንቋሸሻል፣ይዘለፋል።

ወንድነት በምሳሌ፣ በተረት፣ በሽለላ እንደሚሞገሰው ሁሉም ፈሪነትም ይናናቃል፣ ይራከሳል። ይህንንም አንዳንድ ምሳሌ በመውሰድ ማየት ይቻላል።

ከምሳሌው፡-

"ፈሪ ከደጅ አበደ በሬ ከፈሩ ላይ ተኝቶ ይሞታል።"

ከተረቱም :-

"ሳይገድሉ ጮፈሬ፣ ሳያረጋግጡ ወሬ።" የሚል አለ።

በሽለላውም ደግሞ እንዲህ ይናናቃል፡-

ይወለድና ጥርስ ነጫጭ፣
የጋለሞታ ከንፈር መጣጭ፣

በአጠቃላይ ሲታይ የላሎ-ማማ ሕዝብ ከወንድነት አንፃር ተማችነትን ተደባዳቢነትን፣ ተኳሸነትን እና ገዳይነትን ያከብራል፣ ያወድሳልም። በተለይም አንዳንድ የሀገር ሽማግሌዎች ሲናገሩ "እንኳን ሰው የዱር አውሬ መግደል ያስከብራል" ይላሉ። አውሬ የተባሉት ዝሆን፣ አንበሳ እና ነብር ዓይነቶች ናቸው።

ከዓለማዊ አመለካከት አኳያ ከወንድነት ቀጥሎ የሚያስከብር ሙያ ቢኖር ግብርና ነው። ማለዳ ተነስቶ የግብርና ሥራውን የሚያቀላጥፍ፣ በእጅጉ የሚያመርት፣ የእርሻ መሣሪያዎቹን የሚያሰማምር፣ በሮቹን የሚቀልብ፣ ሰጋር በቅሎ ያለው "አራሽ ነው እሳት የላስ ገበሬ ነው፣ ታታሪ ነው፣ አውድማው ሙሉ ነው፣ ቡሃቃው የጠገበ ነው" ያሰኛል። ከወንድነት፣ ከታታሪ ገበሬነት ቀጥሎ የሚያስመሰግን ተግባር ቢኖር ቸርነት ነው። ቸር መሆን "አባ ባህር፣ አባ መስጠት፣ አባ ንዛው" ያስብላልና።

በዚህ ምዕራፍ ከተነሱት ነጥቦች መካከልም ብዙዎቹ የግጭት ሰበብ ወይም መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው። ለምሳሌም በመልክዓ- ምድር የተገለጸው የመሬቱ ለምነት መንጠፍ የለም መሬት ድንበር ግፊያን ሊያስከትል ይችላል። በሕዝቡ ማንነት እና የኋላ አመጣጥ እንደታየውም የትውልድ ሐረግን መምዘዝ እና አለመምዘዝ መዘላለፍን እና መጋጨትን ያስከትላል። የእምነት ልዩነትም ቢሆን ግንኙነትን ያሻክራል። ጋብቻም ወግ እና ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ ካልተፈፀመ የሚያስከትለው ግጭት ይኖራል። ዓለማዊ ስምም ቢሆን በባለስሙ ህሊና ላይ የሚያሳድረው ሥነ-ልቦናዊ ተፅዕኖ አይጠፋም። የሥራ፣ የሙያ፣ የሀብት፣ የአመጋገብ፣ አለባበስ እና አሰፋፈር ልዩነትም ቢሆኑ እዚህ ተዘርዝሮ የማያልቅ ዓይነት ግጭትን ሊቀሩ ይችላሉ። ይኸውም ደግሞ በቀጣዩ የግጭት ንድፈ ሀሳብ (theory) ዳሰሳ ውስጥም ሊታይ የሚችል ነው። በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሱት ነጥቦች ለግጭት መፈጠር እና መቀስቀስ ፍንጭ ሊሰጡ እና አስተዋፅኦ ሊኖራቸው እንደሚችል ልብ ማለት ተገቢነት ይኖረዋል።

3. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ የግጭት ምንነት፣ መንስኤዎች፣ ዓይነቶች፣ ደረጃዎች እና የአፈታት ሥልቶች ይጤናሉ። የኢትዮጵያ ህጎች የግጭት አፈታት ተሞክሮዎችም ይቃኛሉ። በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ ግጭት ምንነት ላይም ተግባራዊ ብያኔ (operational definition) ይሰጣል። በመጨረሻም በባህላዊ የግጭት አፈታት እና በላሎ-ማማ ሕዝብ ህይወት ዙሪያ የተሰሩ እና በአቀረብ የተገኙ ጥናቶች ይከለሳሉ።

3.1. የግጭት ምንነት

የግጭትን ምንነት በሰፊው ለማየት ከመሞከር በፊት ቃሉ በአማርኛ የሚወክለውን እሳቤ እንዲሁም የሐሳብ ውሰት እና ንፅፅር የሚደረግበትን የእንግሊዝኛ አቻ ቃሉን ይዘት እና ገለፃ ማየት የተገባ ነው።

አማርኛ መዝገበ-ቃላት (1993:510) ግጭትን "ጥል፣ ጠብ" በማለት ይፈታዋል። ጥል፣ ጠብ ደግሞ የእንግሊዝኛ አቻው ወይም ወደረኛው "conflict" የሚለው ቃል መሆኑን Leslau (1973:236) ያሳያሉ። ስለዚህም እንግሊዝኛው ዓለማቀፋዊ ቋንቋ እንደመሆኑ ግጭት "conflict" እንደምን እንደተበየነ ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል።

Oxford Advanced Learner's Dcitionary (2000:239) "conflict" ለሚለው ቃል ሦስት ተቀራራቢ ፍቺዎችን ይሰጣል። ፍቺዎቹም ሲጠቃለሉ ግጭት የቡድን፣ የሕዝብ ወይም የአገሮች ተቃራኒ ሐሳቦች፣ አስተያየቶች፣ ፍላጐቶች ወይም ምኞቶች አለመጣጣሞች የሚያስከትሉት አለመግባባት፣ ትግል ወይም አመፅ ነው የሚል መልዕክት ይሰጣሉ።

The New Encyclopedia Birtanica (1997:370) ደግሞ የቡድን ግጭት ብዙውን ጊዜ ዋነኛ የማኅበራዊ ለውጥ ማነቃቂያ ወይም ማምጫ እና መከሰቻ ዘዴ ተደርጐ እንደሚወሰድ ይገልፃል። ማርክሳውያንም ግጭትን በገዢዎች እና በተገዢዎች መካከል የሚደረግ የመደብ ትግል አድርገው እንደሚወስዱ ያወሳል። በማያያዝም የግጭት ምንነት ከማርክሳውያኑ ገለፃ እጅጉን የሰፋ መሆን እንዳለበት በዚህም መሠረት በቡድኖች መካከል የሚደረግ ፉክክር ሁሉ ግጭት እንደሆነ ያትታል። እስካሁን መዝገበ-ቃላቱ እና ዐውደ-ጥበቡ ለግጭት የሰጡትን ፍቺ ተመልክተናል። ቀጥሎ ደግሞ የግጭት ምርምር ሊቃውንት የሰጡትን ብያኔ ወይም ምንነት ገለጻ እንመልከት።

Boulding (1962:5) ግጭትን የበየኑት "ግጭት የተለያዩ ወገኖች ወይም ፖርቲዎች መጻኢ ምኞታቸውን እና እድላቸውን አውቀው ለአንድ ቦታ ወይም ሥልጣን እና ሀብት

መያዝ ወይም መቆጣጠር የሚያደርጉት የማይታረቅ ቅራኔ የሚያስከትለው ፋክክር ወይም ውድድር ነው።" በማለት ነው።

Fisher ደግሞ (1982:567) የግጭትን ምንነት ሲገልጹ "ግጭት ብዙውን ጊዜ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ወገኖች የሚፈጥሩት እና የሚይዙት ተቃራኒ ስሜት የሚያስከትለው የተግባር፣ የዓላማ አለመጣጣም እና አንዱ ሌላውን ለመቆጣጠርም የሚያደርጉት ማኅበራዊ ተቃርኖ ነው ተብሎ ሊበይን ይችላል" ይላሉ። Fisher ግጭትን የበየኑት ካለመግባባት ሳቢያ የሚከሰት ትግል እና ተቃርኖ አድርገው ነው።

እንደ Fisher (1982) ሁሉ የግጭትን ማኅበራዊ ተቃርኖነት ያስመሩበት እና ጠቀሜታም እንዳለው የገለፁት Seymour (1986) ናቸው። Seymour (1986:51) ግጭትን የሚፈቱት "ግጭት ቀዳማይ የማኅበራዊ ለውጥ መንስኤ ማነቃቂያ ነው" በማለት ነው። በዚህ ተርታ ሊጠቀሱ ከሚገባቸው ተማራማሪዎች አንዱ Augsbeger (1992) ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት "ግጭት የሰው ልጅ ኃይል ግልፅ መታያ (ምልክት) ነው። የሰው ልጅ ተጣዳፊነት ወይም ተቸኳይነት ማስረጃም ነው። ይኸውም ለአንድ ዓላማ ወይም ግብ፣ መብት እና የሀብት ምንጭ ማግኘት ወይም መቆጣጠር የሚደረግ ትግል ውጤት ነው።" (1992:18)።

እርግጥ ነው ከዓለም ነባራዊ ሁኔታ እንደምንረዳውም ግጭት የሰው ልጆች ሁሉ የሚጋሩት ኩለንታዊ ክስተት ነው። ምክንያቱም በህይወት ውስጥ ማጋጠሙ አይቀርም። ምንም እንኳን እንደየባህሉ እና እንደየግለሰቡ ተሞክሮ ልዩነት የሚታይበት ቢሆንም።

Augsberger (1992:5) እንዳሉትም የባህል ልዩነት መከሰት የጀመረው ጥንታዊው ሰው በድንጋይ መሣሪያዎች እንሰሳትን እየገደለ መብላት ከጀመረበት ዘመን አንስቶ እያዳበረው ከመጣው አዕምሮአዊ እና ተግባራዊ ዕድገት ጋር ተያይዞ መሆኑ ይታወቃል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም የሰው ልጅ ባህልን እየፈጠረ፣ ባህልም በተራው የሰውን ልጅ እየቀረፀ፣ ሰውም እየተሻሻለ የተሻሻለውም ሰው እንደገና ባህሉን እየለወጠ መምጣቱን እና መቀጠሉን እንረዳለን። በዚህ ሂደት የሰው ልጅ ሥራት የሆነው ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈም እየተሻሻለም እውቀት፣ እምነት፣ ጥበብ፣ ሞራል፣ ህግ፣ ልማድ እና ልዩ ልዩ ተሰጥኦዎች እና ተሞክሮዎች ሆኖ ኅብረተሰብን ከኅብረተሰብ የሚለያይ ሥራት ሆኗል። Avruch (2004:6)። ይህ ደግሞ የግጭት ልዩነት መታያ፣ መከሰቻ ወይም መገለጫም እየሆነ መጥቷል። ግጭት ኅብረተሰብ የተገነባበትን ባህላዊ እውነታ በጥልቀት ያሳያልና። (Augsberger 1992:16)።

እዚህ ላይ የባህል ልዩነት እንደምን የግጭት ምንጭ መግለጫ ሊሆን ይችላል የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል። በመሠረቱ Haviland(1988:29) እንደገለጹት "ባህሎች የሕዝብ ረቂቅ እሴቶች፣ እምነቶች እና የዓለም አገነዛዘቦች (አረዳዶች) ተዋህደው የሚቀረጹባቸው ባህሪያት ናቸው"።

እነ Anderson (1999:146) የሳሞቫርን አጭር እና ግልፅ የሆነ ሐሳብ ጠቅሰው እንዳሰፈሩትም "ባህል አንድን የሕዝብ ክፍል ከሌላው የሚለይ አጠቃላይ የአዕምሮ ወይም የህሊና ኘሮግራም ነው።" በሌላ በኩል እነ Anderson፣ ግጭትን ከሰው ልጅ ውስጣዊ ስሜት አኳያ አይተውታል። "ግጭት የስሜት መወጠር ነው። የውስጥ መረበሽ፣ መነሳሳት፣ መጋጋል፣ ወይም የስሜት ሚዛንን ማጣት፣ የሥነ-አእምሮ ጫና ወይም መጨነቅ ብዙውንም ጊዜ በጠንቅ መወጠር ወይም ሌላ ሥነ-አእምሯዊ ስሜታዊነት ምልክት የሚገለፅ" (1996:10) በማለት። ይህ የአእምሮ መወጠር ወይም መጨነቅ የሚገለፅበትን ወይም የሚለቀቅበትን ሁኔታ በሚገባ ያብራሩት የሚመስሉት Rummel ናቸው። Rummel ግጭት ብዙውን ጊዜ በአጠቃላይ እንደነጐድጓድ፣ ርዕደ-ምድር፣ ፍንዳታ፣ ብጥብጥ (ትርምስምስ) የታመቀ ጥንካሬ መገለጫ፣ መታያ ወይም መከሰቻ ሆኖ እንደሚወሰድ ይገልፃሉ። በተለይም በሰዎች መካከል በጉልበት፣ በአመፅ የሚካሄደው ትግል፣ ድብድብ፣ መጠቃቃት፣ ውጊያ፣ ግድያ እና መበቃቀል ካስከተለ ማኅበራዊ ፋይዳ የሌለው መተላለቅ እንደሆነም ያወሳሉ። /http://www.hawaii edu/powerkills/።

በግለሰቦች መካከል የሚፈጠር ቅራኔን መነሻ እና መድረሻ ከማኅበራዊ ሥነ-ልቦና አኳያ የተመለከቱት Lulofs እና Cahn (2000:124፣149) በበኩላቸው ተግባቦት (communication) በግለሰቦች መካከል ለሚፈጠር ቅራኔ መንስኤ እና ውጤት ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማሉ።

Pearce እና Little John (1997:29-30) እንደገለጹትም ግጭት በዚህ መልኩ የሰው ልጅ ሕይወት ክፍል ወይም ገፅታ መሆን የጀመረው አዳምና ሔዋን በገነት ሳሉ የተከለከለውን ፍሬ በልተው ከተባረሩ እና ጥፋቱ የማን ነው ብለው ርስ በርስ ከተወነጋገቡበት ጊዜ ጀምሮ ነው።

ግጭት ከሰው ልጆች ህልውና ጋር የበቀለ እና ተያይዞም የመጣ መሆኑን በመተንተኑ ሂደት የሚታወቁት Pearce እና Little John ብቻ አይደሉም። በዚህ ረገድ ከሚጠቀሱት መካከል Bartos እና Wher (2000)ም ይገኛሉ። በነርሱ ምልከታ እና ግንዛቤ መሠረት "ግጭት ከሰው ልጅ ፍጥረት እና ዕድገት ጋር የተያያዘ ክስተት ነው። እንዲያ በመሆኑም

የሰው ልጆች ሁሉ የተለማመዱት ነገር ነው" ይላሉ::(2002:1):: ይህም ገለጻቸው ግጭትን ሰዋዊ ባህርይ ያደርገዋል::

ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን የግጭትን ምንነት፤ እና ከሰው ልጅ ጋር ያለውን ትስስር አሳይተዋል:: Eitzin እና Zinn (1998:45-46) ደግሞ ግጭት (conflict) ማለት ይህ ወይም ያ ነው እያሉ ከመበየን ይልቅ የኅብረተሰብን ገፅታ መፈተሽ እንደሚገባ ያወሳሉ:: እነርሱ እንደሚሉት አንድን አለመግባባት፤ ተቃርኖ፤ ትግል ወይም አመፅ ግጭት ነው ብሎ ለመወሰን የሚያጋጥሙ የአተያይ ችግሮች ያጋጥማሉ:: በአብነትም የዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካን የግጭት አፈታት ተሞክሮ ይጠቅሳሉ:: እንዳመለከቱትም በአሜሪካኖቹ ዘንድ ግጭት (conflict) የሚለው ቃል የሚታየው የሥልጣን መዋቅርን አደጋ ላይ የሚጥል ተግባር ተደርጐ ሲሆን በአንፃሩም ሥርዓት (order) የሚለው ቃል የሚታየው በተቋማዊ አሠራር እና አፈፃፀም ሥርዓትን የሚመሩ ወገኖችን ደህንነት መጠበቅ እና ማስከበር ተደርጐ ነው የሚል ግንዛቤ እና ውዝግብ አለ:: በመሆኑም Eitzin እና Zinn (1998፤45-54) እንደሚያወሱት ጥንድ የኅብረተሰብ ህይወት ሥርዓተ-ሞዴሎች ማለትም ሥርዓት (order) እና ግጭት (conflict) አሉ:: እነዚህ ጥንድ የኅብረተሰብ ህይወት ሞዴሎች በተናጠል ሳይሆን በውህድ ነባራዊ የአንድ ህብረተሰብ እውነታነት ከታዩም ምሉዕ የሆነ የኅብረተሰብ ገፅታን ሊሰጡ እንደሚችሉ ያመላክታሉ::

ከዚህ በላይ ያየናቸው ስለ ግጭት ምንነት የተሰጡ ፍቺዎች፤ ትርጓሜዎች ብያኔዎች እና ዓይነቶች በሙሉ ግጭት በተለያዩ መንገድ ሊገለፅ እና ሊበየን እንደሚችል ይጠቁሙናል: ይህም እውነታ ለግጭት የሚሰጠው ፍቺ፤ እና ብያኔ ሰፊ እና አወዛጋቢም መሆኑን ያመላክተናል:: የዚህም ብያኔ ልዩነት መንስኤው እያንዳንዱ የግጭት ብያኔ ሰጪ ልሂቅ ግጭትን የበየነው እንደየተነሳበት ማተኮሪያ ጉዳዩ ለራሱ የሚበጀውን እና የሚሆነውን የሥራ ወይም የተግባር ብያኔ (working definition) በመስጠቱ እንዲሁም ግጭቱን አምንታዊ እና አሉታዊ እያለ በመፈረጁ ይመስላል::

3.2. የግጭት መንስኤዎች

ቀደም ሲል በ3.1 ሥር ስለ ግጭት ምንነት ብያኔ የሰጡትም ሆኑ ሌሎች ተመራማሪዎች ምንነቱን ሲገልጹ መንስኤዎቹንም ገልጸዋል:: ይህም የሆነው ምንነቱ ከመንስኤው፤ መንስኤው ከምንነቱ ተለያይቶ ሊገለፅ የማይቻል በመሆኑ ይመስላል:: ምክንያቱም ባህርዩውን ሲያነሱ የባህርዩውን ዓይነት እና መንስኤ፤ መንስኤውን ሲያነሱ ባህርዩን ማለትም ምንነቱን እንደዚሁም ዓይነቱን ሁሉ መንካታቸው አልቀረም:: ስለሆነም እዚህ የሚጠቀሱት የግጭት መንስኤዎች ከምንነቱ ተፈልቅቀው የወጡ እና ለአፅንኦት ያህል ተለይተው እንዲታዩ የተደረጉ ናቸው ማለት ይቻላል:: ስለዚህ ቀደም ሲል ግጭት

ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ ፍቺ እና ብያኔ ያገኘንባቸው ምንጮች መንስኤውን እንደምን እንደገለጹ እንይ::

በBoulding (1962:5) አገላለፅ መሠረት ግጭት የሚቀሰቀሰው ለሀብት እና ለሥልጣን በሚደረግ ፉክክር ምክንያት ነው:: Fisher (1982:567) ግጭት የሚቀሰቀው ፖርቲዎች የተወሰነ ጥቅምን ለመቆጣጠር ሲሉ ከሚፈጥሩት ቅራኔ መሆኑን ጠቁመዋል:: ከነዚህም አባባሎች የግጭት መንስኤው የሀብት እና የሥልጣን ሽኩቻ ነው የሚል ሐሳብ ነቅሰን ማውጣት ይቻለናል::

Coser (1968:232) "ግጭቶች የሚቀሰቀሱት በእሴቶች፣ በማኅበራዊ ደረጃ፣ በምጣኔ ሀብት ውሱንነት (እጥረት) በሚነሳ ጥያቄ እና በሚደረግ ትግል ሳቢያ ነው::" ይላሉ:: ይህም አባባል የግጭት መንስኤው የሀብት ወይም የእሴት፣ የክብር ጥያቄ የሚያስከትለው ውዝግብ እና ቀውስ መሆኑን ያመለክተናል::

የGray (1984:483-486) የግጭት መንስኤ ዝርዝራ እንደሚያሳየው ደግሞ የምጣኔ ሀብት ምንጭ እጥረት መኖር፣ በእጥረት ላይ ያለውንም የምጣኔ ሀብት ምንጭ በጋራ እና በእኩልነት ለመጠቀም አለመቻል፣ ግልፅ የሆነ የሥልጣን እና የኃላፊነት ክልል አለመኖር፣ የተግባር ማለትም የሥራ ወይም የሙያ ልዩነት መኖር፣ በአንጻሩም የሙያ ልዩነት ድምበር ሲጠፋ እና መከባበርም ሲታጣ፣ የመግባባት (communication) ችግር ሲፈጠር፣ የተግባቦት አለመኖሩም የሚያስከትለው የመረዳዳት ወይም የመገነዛዘብ ልዩነት (perception difference) መከሰት፣ እንዲሁም ስለ አንድ ጉዳይ ቀድሞ የተያዘ አስተሳሰብ፣ አመለካከት ከአዲስ አስተሳሰብና እና አመለካከት ጋር አልስማማ እና አልታረቅ ሲል ግጭት ሊቀሰቀስ እንደሚችል ያወሳሉ:: ይህም አባባል ምንም ማፍታታት ሳያስፈልገው በርካታ የግጭት መንስኤዎችን ማካተቱን እና መጠቆሙን እንገነዘባለን::

ሌላው ዋነኛ የግጭት መንስኤ ተደርጐ ሊቆጠር የሚገባው እና እዚህም በድጋሚ በአፅንኦት መነሳት ያለበት ቀደም ሲል የግጭትን ምንነት ለማሳየት የተጠቀሰው የEitzin እና Zinn (1998) ዐቢይ የግጭት እና ግጭት አፈታት ፅንሰ ሐሳብ ነው:: እነዚህ ሰዎች ሥርዓት (order) እና ግጭት (conflict) መንታ የጎበረተሰብ ሕይወት ገፅታዎች መሆናቸውን ሲገልፁ ህብረተሰብ የክፍፍሎሽ ድምር መሆኑን፤ ክፍፍሎሹም በዕድሜ፣ በዘር (race)፣ በያታ፣ በአካላዊ ብቃት፣ በሙያ ብቃት ወይም ችሎታ፣ በጥበብ፣ በቤተሰብ፣ በቤተሰብ አመጣጥ ወይም ዳራ፣ በሀብት፣ በድርጅት አባልነት፣ በሥራ ዓይነት ወዘተ እንደሆነም የዚህ ድምሩም በሥርዓት እና በግጭት ሞዴሎች ሊተነተን እንደሚችል ገልፀዋል:: (1998:46-47)::

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በአጠቃላይ ሲታይ እስካሁን የቀረቡት ሐሳቦች ግጭት የሰው ልጅ ባህርይነቱን መንስኤውም አንዳየነው የትየለሌ መሆኑን ያረጋግጡልናል።

3.3. የግጭት ዓይነቶች እና ደረጃዎች

ግጭቶችን በዓይነት እና በደረጃ እየለዩ እና እያመለከቱ መግለፅ የተለመደ ነው። ብዙውን ጊዜም የግጭቶቹ ዓይነቶች እና ደረጃዎች የሚገለፁት ግጭቶቹ የተቀሰቀሰበትን ምክንያት፣ በግጭቶቹ ውስጥ የገቡትን ወይም ተሳታፊ የሆኑትን ሰዎች ቡድኖች ተቋማት ወዘተ ማንነት እንዲሁም ግጭቱ የተዳረሰበትን ወይም የተዛመተበትን አካባቢ ስፋት በማየት ይመስላል። ምክንያቱም ግጭቱ የተቀሰቀሰበትን ምክንያት መሠረት በማድረግ የግጦሽ፣ የመሬት፣ የውኃ፣ የኃይማኖት፣ የፖለቲካ፣ የቅኝ ግዛት ወዘተ ግጭት ነው እንላለን። እንዲሁም በግጭቱ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑትን ወገኖች መሠረት በማድረግ የቤተሰብ፣ የግለሰቦች፣ የቡድኖች የተቋሞች፣ የነገዶች፣ የጐሳዎች፣ የብሄሮች፣ የመንግሥታት ግጭት ነው እንላለን። ግጭቱ የተዳረሰበትን አካባቢም ግምት ውስጥ አስገብተን ጐጣዊ፣ አካባቢያዊ፣ ወረዳዊ፣ አውራጃዊ፣ ክፍለ አገራዊ፣ ክልላዊ፣ አገራዊ፣ ክፍለ-አህጉራዊ፣ አለማቀፋዊ እያልን ዓይነት እና ደረጃውን እናስቀምጣለን።

በግጭት ዙሪያ ጥናትና ምርምር ያደረጉ እና በማድረግ ላይ ያሉ ምሁራን ደግሞ የግጭቶችን ዓይነቶች እና ደረጃዎች መለያ ወይም መለኪያ ሥርዓት አበጅተዋል።

Augsberger (1992:247-248) ግጭቶችን ተጨባጭ እና ኢ-ተጨባጭ ወይም ጭብጣዊ እና ጭብጥ የለሽ በማለት በዓይነት እና በደረጃ መለየት እንደሚቻል ይገልጻሉ። በእሳቸው እይታ መሠረት ተጨባጭ የግጭት ዓይነት የሚባሉት በግል ሀብት፣ ንብረት፣ በሥራ ዓይነት እና ደረጃ፣ በተፈጥሮ ሀብት ምክንያት ወዘተ የሚቀሰቀሱት ሲሆኑ ከነዚህ ውጭ ያሉት ጭብጥ የለሾች ናቸው።

Lulofs እና Cahn (2000 57-73) ደግሞ አራት የግጭት ዓይነቶች እንዳሉ ይገልፃሉ።

የመጀመሪያው እውነተኛ እና ተጨባጭ ግጭት (real and substantive conflict) ይሰኛል። ይኸውም በጥቅም ተካፋይነት ወይም ይገባኛል ባይነት ማለትም በሀብት፣ በድንበር፣ በእምነት ወዘተ እሴቶች ተጋርቶ እና ሽሚያ ሣቢያ የሚቀሰቀስ ነው።

ሁለተኛውን የግጭት ዓይነት ጭብጠ-ቢስ ወይም ጭብጥ የለሽ ግጭት (non substantive conflict) ይሉታል። ይህም የግጭት ዓይነት ተቀናቃኞቹን ወገኖች የሚያገናኝ እና የሚያሻማ በቂ እና ተጨባጭ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ፀብ፣ መዘላለፍ እና መደባደብ የሚያስከትል መሆኑ ተወስቷል።

በሃሰተኛነት የፈረጁት እውን የለሽ ወይም እውነ-ቢስ ግጭት (unrealistic conflict) ያሉትን ነው። ይህ ደግሞ ተቀናቃኞቹ ወገኖች በመካከላቸው ፀብ መኖሩን በእኩል ደረጃ ያልተገነዘቡት የግጭት ዓይነት ነው። ይህም ማለት አንዱ ወገን ብቻ የተገነዘበው ወይም የተረዳው በሌላ ወገን በተቀናቃኝነት የተፈረጀው ወገን ወይም አካል ያልተረዳው ወይም ያላወቀው እና በገሃድም ያልተከሰተ የግጭት ዓይነት ነው።

የመጨረሻው በሀሳብ አለመስማማት ክስተት ብቻ የሚገለጽ ግጭት /mere disagreement conflict/ የተባለው ነው። ይሄም በተቀናቃኞቹ መካከል የሀሳብ አለመስማማት እና አለመጣጣም ብቻ በመኖሩ በአስተሳሰብ እና አመለካከት ልዩነት መከሰት ብቻ የሚገለፅ ከዚያ ያለፈ ውዝግብ የማያመጣ ወይም የማያስከትል ግጭት ነው።

ከዚህም ሌላ የግጭቶቹን ዓይነቶች በስበበ-መንስኤያቸው ግንዛቤያዊ (cognitive) እና ቁሣዊ (materialistic) ብሎ መመደብ፤ ደረጃቸውንም ደግሞ ንዑስ (micro level) እና ዐቢይ (macro level) ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል።

ንዑሱ የግጭት ደረጃም በግለሰቦች፣ በአነስተኛ ቡድኖች መካከል የሚታየው ዐቢዩ ደግሞ ከዚህ በላቀ ሁኔታ የሚገለፀው ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል።

3.4. የግጭት አፈታት ሥልቶች

በጥቅሉ ሲታይ ግጭት እንደ ሰው ልጅ የሕይወት ክፍል ተደርጐ ቢቆጠርም በንዑስ ደረጃም ሆነ በዐቢይ ደረጃ የሚከሰት ግጭት ምንጩ፣ ምክንያቱ እና ሂደቱ ተመርምሮ መፍትሔ ካልተሰጠው ፍልሚያ ወይም ጦርነት ሊያስከትል ይችላል። ፍልሚያ ወይም ጦርነት ደግሞ ሰብአዊ እና ቁሳዊ ኪሣራን ማስከተሉ አይቀሬ ነው። ይህም ደግሞ የሰውን ልጅ የሰከነ ህይወት ማደፍረሱ፣ ማጐሳቆሉ እና ማውደሙ ሳይታለም የተፈታ ነው።

ምንም እንኳን ግጭቶች ከሰው ልጅ ዕድገት ጋር ተያይዘው የመጡ ሰብአዊ ባህርያት ተደርገው የሚቆጠሩ ቢሆኑም በንዑስ ደረጃ ማለትም በግለሰቦች በአነስተኛ ቡድኖች፣ በተቋሞች፣ በፖርቲዎች በጐሳዎች መካከል ወዘተ እና በዓቢይ ደረጃ በመደብ፣ በአመለካከት ልዩነት፣ በብሔረሰብ፣ በብሔሮች፣ በአገሮች፣ በክፍለ አህጉሮች መካከል ተከስተው እና ተካረው ከሄዱ አደገኛነታቸው የትየለሌ ይሆናል።

ስለዚህም ግጭቶች ከቁጥጥር ውጪ ሆነው ሕይወትን እና ንብረትን ከመብላታቸው በፊት ማርገብ፣ መግታት፣ መቆጣጠር፣ ማቆም እና ዘላቂ ሰላምን በሚያሰፍን ሁኔታ መፍታት ተገቢ መሆኑ አያጠራጥርም። በተለይ ደግሞ ዘላቂ ሰላምን በሚያስከትል እና በሚያረጋግጥ መልኩ መፍታት መቻል የላቀ የግጭት አፈታት ዘዴ እና ሥልትንም የሚጠይቅ ተግባር መሆኑ ግልፅ ነው። በዚህም መሠረት ግጭቶች በተለያዩ ዘዴዎች እና

ሥልቶች ሲገቱ፤ የሚችሉባቸውን ንድፈ ሐሳባዊ ሁኔታዎች ዘርዝር አድርጉ ማመልከት እና ማስቀመጥ ተገቢ ይሆናል።

Gulliver (1979) ግጭቶች በተለይ ከጦርነት እና ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጪ ሲገቱ፤ ወይም ሲቆሙ (conflict settlement) እና ሲፈቱ (conflict resolution) የሚችሉባቸውን መንገዶች ማብራራታቸው እና ማመላከታቸው በብዙ የግጭት አፈታት ጥናቶች ላይ ተጠቋቁሟል ወይም ተነስቷል። በዮሐንስ (ኢ.አ.አ 1998:14) ላይ ደግሞ በስፋት ተጠቅሷል። በ Gulliver እይታ መሠረት ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጪ ግጭቶች ሲፈቱ የሚችሉባቸው መንገዶችም ድርድር (negotiation) የግልግል ዳኝነት (arbitration) እና ሽምግልና(mediation) የሚሉት ሦስት ዕንሰ-ሐሳቦች ናቸው።

ከላይ የተገለጹት ድርድር፤ የግልግል ዳኝነት መሻት፤ እና ሽምጋይነት ሦስቱም ዕንሰ-ሐሳቦች ግጭትን ለመቆጣጠር ወይም ለማቆም፤ ለዘለቂታውም ለመፍታት እና እርቅን ለማውረድ ሰላምንም ለማስፈን የሚረዱ ዘዴዎች ከመሆናቸው በተጨማሪ የሦስተኛ ወገኖችን ጣልቃ ገብነት ደረጃ፤ አስፈላጊነት እና ተግባር ወይም ሚና ጠቋሚዎች ናቸው።

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ዕንሰ-ሐሳቦችም በእኛም ባህል የግጭት አፈታት እና እርቅ ማውረድ ሂደት ውስጥ በደምሳሳው ድርድር፤ የግልግል ዳኝነት፤ ሽምግልና እያልን የምናውቃቸውን እና የምንሰይማቸውን አሠራሮች ገላጮች ናቸው።

ግጭትን ዘላቂ ሰላም፤ መግባባት፤ የጎበረተሰብ ህይወት መረጋጋት እና መሻሻልን በሚያመጣ መልኩ መፍታት እንደሚገባ ዘርዝር አድርገው የሚያወሱት Avruch (2004፤23-27) በዓለም ላይ እየተሠራባቸው ያሉትን የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ወይም ሥልቶች በሁለት ከፍለዋቸዋል።

Avruch (2004፤26-27) ቀዳማይ የግጭት መፍቻ ሥልት ባሉት ውስጥ ያነሱትም ማናቸውንም ዘዴ እና ሥልት ተጠቅሞ ግጭትን ማስቆም ወይም እንዲያበቃ፤ ማድረግ የሚለውን ነው። ይህም እሣቸው እንደሚሉት መመቻመችን (compromise)፤ ግጭትን መግታት ወይም ማቆምን (conflict settlement)፤ የግጭት መንስኤን አስቀድሞ ማምከን ወይም ማውደምን (conflict prevention)፤ ግጭትን መቆጣጠር፤ (conflict regulation) እና ግጭትን በሥርዓት መያዝ (conflict management) ወዘተ ያካትታል። ይሁንና እንደሳቸው አገላለፅ እነዚህ በሙሉ ጦርነት የሌለበት ሰላም (negative peace) መፍጠሪያዎች ናቸው። ስለሆነም ውሎ አድሮ ግጭቱ ሊያገረሽ እና ችግርም ሊያስከትል ይችላል።

Avruch በካልአይ የግጭት አፈታት ሥልትነት ያስቀመጡት ደግሞ አዲሱ እውነተኛ የግጭት መፍቻ ሥልት (the new genuine conflict resolution) ያሉትን ነው። ይህ

የግጭት አፈታት ሥልት የበላይነት፣ ጭቆና፣ እንዲሁም የታመቀ ወይም የሚብላላ ቦርነት የማይኖርበት የተሟላ ሰላም (positive peace) ማምጫ እና ማግኛ ነው። የግጭት አፈታት ሥልቱም ግጭቱ የተገለፀበትን፣ የታየበትን ሁኔታ በመጠገን እና በማከም ላይ ብቻ የሚያተኩር አይደለም። ይልቁንም የግጭቱን ሥረ-መሰረት አውቆ ከፀጥታ ወይም ደህንነት ስትራቴጂ ፍላጐት በዘለለ እና ባለፈ መልኩ እውነተኛ የሆነ ሰላም ማስፈንን እና የጎበረተሰብ ህይወት ለውጥን ዓላማው ያደርጋል።

ስለዚህም አዲሱ እውነተኛ የግጭት አፈታት ሥልት (the new genuine conflict resolution) ባህልን፣ ማኅበራዊ ሕይወትን ብሔራዊ እና ዓለማቀፋዊ ፖለቲካዊ ግንኙነትን (diplomacy) መሠረት ያደርጋል። ያካትታልም። ይህም ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን የሚያስችል ስለሆነ ጥቅሙ የጐላ እና የትየለሌም ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ የሚከሰቱ ከተራ እስከ ከባድ ወይም ከጥቃቅን እስከ ከፍተኛ ደረጃ ያሉ ግጭቶችን ለመቆጣጠር ለመግታት እና ለመፍታት ሰዎች ሁሉ በየአካባቢያቸው ልዩ ልዩ ባህላዊ ዘዴዎችን እና ሥልቶችን በመጠቀም ላይ መሆናቸው የሚታይ እውነታ ነው። ስለሆነም በግጭት አፈታት ጥረት እና ሂደት ውስጥ ባህልን መረዳት እና ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችንም ከግምት ውስጥ ማስገባት እና መጠቀም ተገቢ ይሆናል።

3.4.1. ሽምግልና፣ ይቅርታ እና እርቅ

እነዚህን ሽምግልና፣ይቅርታ እና እርቅ የሚሉ ቃላት የአማርኛ ፍቺ ስንመለከትም አማርኛ መዝገበ ቃላት (1993:143) ለሽምግልና ሁለት ፍቺ ይሰጠዋል። "እርጅና" እና "የማስታረቅ"፣ የማስማማት፣ የማማለድ ተግባር" የሚል። ሁለተኛው ፍቺም ለያዝነው ጉዳይ የሚስማማ ነው። ይቅርታ የሚለውን ደግሞ "ቂም ወይም ቅሬታ እንዳይኖር በዳይ ተበዳይን ምህረት የሚጠይቅበት የልመና ቃል፤ በደልን፣ ቂምን መተው ይቅር ማለት ምህረት ማድረግ"። (167) እርቅን ደግሞ "ቀድሞ የነበረን ጥል፣ ወይም ቅሬታ በማስወገድ የሚደረግ ስምምነት ፍቅር፣ ሰላም" (310) ይለዋል።

እነዚህ ሽምግልና፣ ይቅርታ እና እርቅ ጎበረተሰብን ለማስማማት፣ ለማረቅ እና ለመምራት ያላቸው ፋይዳ የትየለሌ መሆኑንም ምሁራን ማመላከታቸው ይታወሳል። ለምሳሌም በዮሐንስ (እ.አ.አ 1998:14 የተጠቀሱት) Gulliver (1979) የሰላም ድርድር እና ሽምግልና (mediation) ተጋጪዎቹ ወገኖች የተስማሙበትን እና የተቀበሉትን ውሳኔ ያለማመንታት ለማክበር የሚያስችሉ ዘዴዎች መሆናቸውን አውስተዋል።

Haviland ም (1988:310-323,369) ጎበረተሰብ በውስጣዊ እና ውጫዊ የቁጥጥር ሥርዓት ውስጥ እንደሚኖር ውስጣዊ ቁጥጥርም አብሮ በቀል በመሆኑ ከውጪ እንደሚጣል

ገደብ እንደማይቆጠር፤ በዚህም ረገድ ሽማግሌዎች (elders)፤ የልቅና ሥርዓት (chiefdoms) እና ኃይማኖት ህብረተሰብን ለመቆጠጣር ለመምራት ለማረጋጋት እና የሰከነ ህይወት እንዲመራ ለማድረግ የላቀ ድርሻ እንዳላቸው ያስረዳሉ::

በተለይ የይቅርታ እና የእርቅን ዓይነት ከሰው ልጅ ባህርይ አኳያ ሰፋ አድርገው የተነተኑት Augsberger (1992:262) ናቸው:: እሣቸው ይቅርታ እና እርቅ ለሰው ልጆች ሁሉ የሚከብዱ፤ በተለያዩ ህብረተሰብ ባህል ውስጥም የተለያዩ ቅርፅ እና አሴትነት ያላቸው መሆናቸውን እርቅም የብዙ ዓይነት ይቅርታዎች ውጤት እንደሆነ ያብራራሉ:: በመሆኑም "እርቅ ምንም እንኳን የብዙ ዓይነት ይቅርታዎች ውጤት ቢሆንም በሁሉም ህብረተሰቦች ዘንድ የተከበረ ጉባኤ እና የጋራ ተፈጥቅዶአዊ ግንኙነት ወይም የጋራ ፍቱረ-ግንኙነት ተደርጐ ይታያል:: " (Augsberger 1992:282-283):: የእርቅ አፈፃፀም ሥርዓቶቹ ወይም ከበራዎቹም (reconciliation rituals) እርቁን ዘላቂ እና ፅኑ አድርጐ ለመደምደም የሚበጁ፤ እንደየባህሉም ቀላልም ውስብስብም የሚሆኑ ናቸው::Augsberger (1992:275)::

Lulofs እና Cahnን (2000:326) እንደገለጹትም ግጭትን በይቅርታ እና እርቅ መንፈስ መፍታት የሚበጀው የግጭትን ተደጋግሞሽ እና ሽክርክሪትነት ለመግታት ነው:: ይቅርታ እና እርቅም ቁርኝትም ልዩነትም ያላቸው የጠብ እና የቂም በቀል መግቻዎች ናቸው:: እነርሱ እንደሚሉት የይቅርታ ዓላማ የበቀል ፍላጐት እና ስሜትን መግታት እና ማስወገድ ሲሆን የእርቅ ዓላማ ደግሞ መተማመንን መልሶ የመገንባት እና በረኸቦም ጊዜም ግንኙነትን ወደነበረበት ቦታ መመለስ እና ዘላቂ የመግባባት ባህርይን መገንባት ነው::

Lulofs እና Cahn (2000:326) አያይዘው እንዳመለከቱት በስሜት እና በተግባር አለመጣጣም ተራርቀው በቆዩ ሰዎች መካከል ይቅርታ እና እርቅ መፈፀም እንደሚገባ ማስተማር የተጀመረውም ቢያንስ ሥልጣኔ መመዝገብ ከጀመረበት ዘመን አንስቶ ነው:: በመሆኑም ይቅርታ እና እርቅ የአይሁድ ክርስትና እና የሌሎቹም ታላላቅ ኃይማኖቶች አስተምህሮ ባህላዊ እና ማዕከላዊ ፅንሰ ሐሳብ ነው::

ይህንኑ ከላይ የቀረበውን መሠረታዊ ሃሳብ ተመርኩዘን መጽሐፍ ቅዱስን ስንመለከትም የይቅርታን እና የእርቅን አስፈላጊነት ያነሳው ደጋግሞ መሆኑን እናያለን:: ለምሳሌም የይቅርታ አስፈላጊነት እና ጠቀሜታ በሉቃስ ወንጌል (17:3-4) እንዲሁም በጳውሎስ መልዕክቶች በገላትያ (6:1-5) በቆላስያስ (3:13) የተገለፀ ሲሆን የፍቅር አስፈላጊነትም እንዲሁ በጳውሎስ መልዕክቶች በኤፌሶን (4:32) እንዲሁም የሰላም፤ የፍቅር ፅናት እና አስፈላጊነት በማቴዎስ ወንጌል(18:15-21) እንዲሁም በሉቃስ ወንጌል (5:24-25) ተገልጿል::

ፈቃደም ለማስተማሪያ የመረጡት እና የጠረዙት ጽሁፍ (2004:1) አፍሪካውያን በአሳውንቶች እና ልማዳዊ መሪዎች አማካይነት ግጭትን በወንድማዊነት መንፈስ ለመፍታት የአርቅ ሥርዓትን ወይም ከበራዎችን የማካሄድ ልዩ ባህል እንዳላቸው ያወሳል።

3.4.2. ሽምግልና፣ ይቅርታ እና እርቅ በቀልን ከማስቀረት አኳያ

ደስታ (1962:249) በቀልን "የክፉ ብድራት ዕዳ፣ ፍዳ፣ ቂም፣ ደም" ብለው ፈተውታል። የአማርኛው መዝገበ ቃላትም (1993:226) በቀል የሚለውን ቃል "ቂም፣ የክፉ ድርጊት፣ ክፉ ምላሽ" ይለዋል። Oxford Advancd Learner's Dictionay' 2000ም የብቀላ አቻ የሆነውን "vengeance"ን መጥፎን በመጥፎ በአምሳያው መመለስ በሚል ይፈታዋል።

ብቀላ በመሠረቱ ዓይነትን በዓይነት መመለስ፣ ቀዳሚ ድርጊትን በተመሳሳይ ድርጊት መድገም እንደገናም ማስታወስ እንደገናም መድገም ሲሆን በተለይ ደምን በደም መመለስ ወይም የመበቀል ሂደት እና አዙሪትም ነው።

በተለይ በአረቦች ባህል ውስጥ ደምን በደም መበቀል ወይም መበቃቀል ልማድ ስላለ መግቻ፣ ማገጃ ወይም መፍትሔ ካልተፈለገለት ብዙውን ጊዜ እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ እያቋጠረ ሊያፋጅ እና ሊያበቃቅል እንደሚችል ተዕፏል። (Augsberger 1992:267)። በ"አማራ" ሕዝብ አኗኗር ውስጥም ይኸው ሁኔታ ይታይ ዘንድ ታሪካዊ ተዛምዶ እና ትስስር ያለ ይመስላል። በመሆኑም በቀልን ለመግታት፣ ሰላምን ለማስፈን ሽምግልናን፣ ይቅርታን እና እርቅን መጠቀም ተገቢ ልማድ ሆኗል።

3.5. የኢትዮጵያ ሕጎች የግጭት አፈታት ተሞክሮ

ኢትዮጵያውያን ግጭቶችን ተራ፣ ቀላል፣ መለስተኛ እና ከባድ እያሉ የመፈረጅ ልማድ እንዳላቸው ይታያል። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚጠቁሙትም ኢትዮጵያውያን ግጭቶችን በተለያዩ መንገዶች ሲፈቱ ኖረዋል። ይፈታሉም። የግጭት መፍቻ መንገዶቹም ኃይል፣ ዳኝነት እና ልዩ ልዩ ባህላዊ ሽምግልናዎች ናቸው።

ይሁንና ኢትዮጵያ እንደ አገር ግጭቶችን ለመፍታት የምትጠቀምባቸው መንገዶች ወይም ሥልቶች አሉ ወይ? የሚለውን መመልከት የዚህ ጥናት አንዱ ዓላማ እንደመሆኑ የኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ ስለሚፈቱበት ሁኔታ ምን ይላሉ የሚለውን ማየት ተገቢ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ዘመናዊ የህግ ሰነዶች ያካተቱን ሃሳብ ስቃኝ በአብዛኛው ግጭቶች ሊፈቱ የሚችሉባቸውን ሥልቶች (ዘዴዎች) ወይም አግባቦች ከማመልከት ይልቅ የግጭት

ዓይነቶችን እና ደረጃዎችን በማስቀመጥ ረገድ ብዙ አዕንኦት የሰጡ ይመስለኛል። ለምሳሌ ፍትሐ-ነገሥት (1958:544) ከባድ ግጭት እና ጥፋት የሚያደርገው የጦር ሜዳ ክዳትን እና ሰውን ከጦር ሜዳ ውጭ መግደልን ነው። "ሰው የገደለ ሰው በሥጋና በመንፈስ ይቀጣል" በማለት። ስለሆነም በፍትሐ-ነገሥቱ መሠረት በልዩ ልዩ ምክንያት ነፍስ የገደለ ሰው ቅጣት የሚጣልበት እንደ አገዳደሉ ሁኔታ ሲሆን ቅጣቶቹም ይሙት በቃ፣ የደም ካሣ እና ከአገር መሰደድ የሚሉትን ያካትታሉ።

ይሙት በቃ የተፈረደበት ነፍስ ገዳይም የሚገደለው በተለያዩ ሁኔታ ነው። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወት ልማድ እና ባህል ጋር እንዲሁም በመለወጥ ላይ ካለው ትውልድ ኑሮ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሳይንሳዊ ሁኔታ ጋር እንዲስማማ ተደርጎ ተቀረፀ (1949 :IV) የተባለው የ1949 ዓ.ም የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቁጥር 521 ስለመግደል አና አደራረጉ ሲገልፅ፡-

> *"በማናቸውም ዓይነት አስቦ ወይም በቸልተኝነት ሰውን የገደለ ማንም ሰው ነፍስ-ገዳይ ነው። አስቦ ነፍስን በመግደል ጥፋተኛ የሆነ ሰው አገዳደሉ ቀላል ወይም ከባድ እንደመሆኑ ይቀጣል።"* ይላል።

በተጠቀሰው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሰረትም የሞት ወይም የእሥራት ቅጣት መወሰኛ ድንጋጌዎች ተሰጥተዋል። ሌሎች የጎበረተሰብን ደህንነት የሚያውኩ ድርጊቶች ሲፈፀሙም በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 323 መሠረት ውሳኔ እንደሚሰጥባቸው ደንግጓል። የ1997 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ በበኩሉ አንቀፅ 538 ላይ ያሰፈረው ሐሳብ ከላይ ከተገለፀው የተቀራረበ ነው።

> *"ማንም ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት በማናቸውም ዓይነት መሣሪያ ወይም ዘዴ ሌላውን ሰው የገደለ እንደሆነ ነፍስ-ገዳይ ነው። አስቦ ወይም በቸልተኝነት ሰውን በመግደል ጥፋተኛ የሆነ ሰው ላይ የሚጣለው ቅጣት እንደ አገዳደሉ ቀላልነትና ከባድነት ይወሰናል።"* ይላል።

ከላይ ከተጠቀሱት የወንጀል ሕጐች ይልቅ የ1952 ዓ.ም የፍትሐ ብሔር ሕግ ለባህላዊ የግጭት አፈታት ሥልት ወይም ዘዴ እውቅና የሰጠ ይመስላል። ምክንያቱም አንቀጽ ሃያ ላይ ሽምግልና እና እርቅ ከሕጉ ጋር አስካልተጣረሩ ድረስ ተቀባይነት እንዳላቸው ይደነግጋል። በዚሁም መሠረት በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 676, 677 እና 692 እንደተጠቀሰው በባል እና በሚስት መካከል ግጭት ተከስቶ ለፍርድ ቤት ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ በራሱ ሥልጣን ውሳኔ ከማሳለፉ በፊት ጉዳዩን ለቤተ-ዘመድ ሽምግልና እና ዳኝነት መምራት እንዳለበት ይጠቁማል። የባል እና ሚስት አለመግባባቶችን ፍርድ ቤቶች ወደቤተ-ዘመድ ሽምግልና ጉባኤ እየመሩም የቤተ-ዘመድ ጉባኤዎቹ የማስማማያ እና የማፋቻ ሐሳቦችን እና ውሳኔዎችን ሲሰጡ እንደነበር የሚታወስ ነው።

በ1987 የወጣው የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት የግል እና የቤተሰብ ህግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በኃይማኖቶች ወይም በባህላዊ ህጐች መሠረት መዳኘት አለመከልከሉን ያወሳል። የኃይማኖት እና የባህል ፍርድ ቤቶችን ማቋቋም እንደሚቻልም በአንቀጽ 34 ቁጥር 4-5 ደንግጓል። በሌላም በኩል ይኼው ሕገ-መንግሥት የፌዴሬሽን ምክር ቤት "በክልሎች መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሄ ይፈልጋል" የሚል ድንጋጌ አለው። ይሁንና የፌዴሬሽን ምክር ቤቱ አለመግባባቶቹን ለመፍታት ሊጠቀምባቸው የሚገቡት አግባቦች አልተጠቀሱም።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግጭቶችን ለማርገብ እና ለመፍታት የሚጠቀምባቸው ባህላዊ ዘዴዎች መኖራቸው የታወቀ ቢሆንም /በተዛማጅ ሥራዎች ሥር የተከለሱትን ማየት ይቻላል። /በሕግ ደረጃ በፍትሐ-ነገሥት 1958 እና በ1952 ፍትሐ-ብሔር ሕግ ከተጠቀሱት በስተቀር ልማዳዊ እና ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥልቶች አልተካተቱም። እንዲያውም የ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 216 እና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 11 ከባድ ድብደባ፣ ግድያ፣ እምነት ማጉደል፣ አስገድዶ መድፈር፣ ጠለፋ፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ በሽምግልና እና እርቅ ማለቅ ወይም መጨረስ እንደሌለባቸው ይደነግጋል።

3.6. የላሎ-ማማ ምድር ወረዳ ግጭት ምንነት ተግባራዊ ብያኔ

በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ የማያጣላ እና የማያጋድል የፀብ ወይም የግጭት ዓይነት የለም ማለት ይቻላል። በግጭት ንድፈ-ሐሳብ ወይም ትውር ቅኝት ሥር የቀረቡት መንስኤዎች ሁሉም አለመግባባት፣ ፀብ፣ ድብደባ እና ግድያ የሚያስከትሉ ግጭቶች ናቸው።

የፀቡ ወይም የግጭቱ ዓይነት እና ደረጃም የሚሰላው ግጭቱ ባስከተለው የንብረት፣ የአካል እና የሕይወት መጥፋት መጠን እና ደረጃ ነው። ከዚህ በመነሳትም ግጭቶቹን ቀላል እና ከባድ እያሉ የመፈረጅ ልማድ አለ። ግጭትም ለላሎ-ማማ ሕዝብ የለውጥ ማነቃቂያ እና የማህበራዊ ዕድገት ግብ መምቻ መንስኤ አይደለም። ይልቁንም መደባደቢያ፣ አካል ማጉደያ፣ ንብረት ማውደሚያ እና መገዳደያ ነው። ስለሆነም አዎንታዊ ገፅታ የለውም።

ሕዝቡ ግጭቶቹን ለማብረድ ወይም ለማቀዝቀዝ እና ለመፍታት የሚጠቀምበት ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ የሽምግልና ሥርዓትም ትወልደ-ሐረጋዊ ወይም ቤተ-ዘመዳዊ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ሰላም መፍጠሪያ እና ማረጋጊያ ነው። ስለሆነም "ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ" ጥናት የአካባቢያዊ ወይም አገር በቀል የግጭት አፈታት አውቀት እና ሥርዓት ማሳያ ነው። የዘመናዊ ህግ ሥርዓት የግጭት አፈታት እና ሂደት የበላይነት ማሳያ ወይም ማረጋገጫ አይደለም።

በዚህ ምዕራፍ ስለ ግጭት ምንነት፣ መንስኤዎች፣ ዓይነቶች፣ ደረጃዎች እና የግጭት አፈታት ሥልቶች አጫጭር ገለፃ ለማቅረብ ሞክሬያለሁ። ሽምግልና፣ ይቅርታ እና እርቅም የበቀል መግቻ ስለመሆናቸው አውስቻለሁ። ለላሎ-ማማ ምድር ነዋሪዎች የሚስማማ የግጭት ብያኔም ሰጥቻለሁ። ቀጥሎ ደግሞ በላሎ-ማማ ምድር ሕዝብ ህይወት እና በባህላዊ የግጭት አፈታት ላይ የተሰሩ ጥናቶችን አክልሳለሁ።

3.7. በላሎ-ማማ ምድር ሕዝብ ሕይወት እና በባህላዊ የግጭት አፈታት ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች ክለሳ

በዚህ ርዕስ ሥር የሚታዩት እና የሚከለሱት ሥራዎች በተለያዩ የትምህርት መስኮች እና በተለያዩ ክፍሎች እንዲሁም አካባቢዎች የተካሄዱ ጥናቶች ናቸው። እነዚህም ሥራዎች ብዙዎቹ ለዶክትሬት ዲግሪ እና ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ሲሆኑ ለአከላለስ ያመች ዘንድም በሁለት ክፍል መድቤያቸዋለሁ።

የመጀመሪያው ክፍል በ"ሶሻል አንትሮፖሎጂ" የትምህርት መስክ በላሎ-ማማ ሕዝብ ሕይወት እንዲሁም ግጭትን እና የግጭት አፈታትን አስመልክቶ በተካሄዱ ጥናቶች ክለሳ፤ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር የትምህርት መስክ በግጭት እና ግጭት አፈታት ዙሪያ በተሰሩ ጥናቶች ክለሳ ላይ ያተኩራሉ።

3.7.1. በ"ሶሻል አንትሮፖሎጂ" የትምህርት መስክ የተደረጉ ጥናቶች ክለሳ

በ"ሶሻል አንትሮፖሎጂ" የትምህርት መስክ በመንዝ አካባቢ ከተደረጉ ጥናቶች መካከል Reminick (እ.ኤ.አ. 1965) "The Manze Amhara of Ethiopia: a Study of Authority, Masculinity and Sociality" በሚል ርዕስ የሰሩት ጥናት አለ።

ጥናቱ መሠረት ያደረገው እና የተካሄደው በወረዳው ርዕሰ ከተማ ሞላሌ ሦስት ኪሎ ሜትር ዙሪያ ከባቢ ውስጥ ነው። የዳሰሰውም በጊዜው ይታይ የነበረውን አጠቃላይ የሕዝቡን ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ነው።

የReminick ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ሲነፃፀር በስፋቱም፣ በደረጃውም ላቅ ያለ ቢሆንም የርዕሰ-ጉዳይ እና የይዘት ተዛምዶ ግን የለንም። ምክንያቱም የእኔ ትኩረት የወረዳውን ባህላዊ የደም ማድረቅ ዕርቅ ሥርዓት ለማሳየት ነው። የእሳቸው ደግሞ የህዝቡን አኗኗር፣ አደረጃጀት፣ መስተጋብር፣ ዝንባሌ እና ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ገፅታ በመዳሰስ ላይ ያተኮረ ነው። በጥናቶቻችን መካከል የተወሰነ መቀራረብ ወይም መመሳሰል የሚታየው በአካባቢ ዳራ ገለፃዎቻችን ላይ ነው። ይኸውም ሊሆን የቻለው እሳቸው በዳራ ገለጻቸው ያነሷቸው አንዳንድ ተፈጥሮአዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ገፅታዎች አንዳንዶቹ

ቋሚ በመሆናቸው አንዳንዶቹም በአርባ ሁለት ዓመታት ውስጥ ብዙም ያልተለወጡ ከመሆናቸው የተነሳ በእኔም ጥናት ዳራ ውስጥ ሊጠቀሱ በመቻላቸው ይመስለኛል::

Reminick በሁለንተናዊው የሞላሌ ከተማ አካባቢ ህዝብ አኗኗር ጥናታቸው ከተመለከቷቸው ጉዳዮች ውስጥ ወንድነት (masculinity) የሚለው ገለጻቸው ይገኛል:: እሳቸው እንደተገነዘቡትም የመንዜ ሥነ ልቦና እና ባህላዊ እሴት ፀበኝነትን ያደፋፍራል:: በመሆኑም ልጅም ሆነ ጉልማሳ፣ ሴትም ሆነች ወንድ፣ ለፀብ እና ለድብድብ የሚያነሳሱት በወኔ ነው:: (Reminick 1973: 157)::

በተመሳሳይ ሁኔታ በዚሁ በ"ሶሻል አንትሮፖሎጂ" የትምህርት ዘርፍ በመንዝ አካባቢ ከተደረጉት ጥናቶች ሌላው Levine (እ.ኤ.አ. 1972) "Wax and Gold" በሚል ርዕስ ያካሄዱት ጥናት ነው:: ጥናቱ ያተኮረው በኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት ምሥረታ ሂደት ውስጥ የመንዘን እና የጐንደርን ሚና ወይም አስተዋፅኦ እንዲሁም የሁለቱን አካባቢ ሕዝቦች ተመሳስሎ እና ልዩነት በማሳየት ላይ ነው:: ይሁንና የመንግሥት አፈጣጠር እና የግዛት ማስፋፋት ሂደቱን ሲያነሱ የአካባቢውን ሕዝብ ማንነት፣ ቋንቋ፣ አስተዳደር፣ ባህልና እምነት ወዘተ መጠቃቀሳቸው አልቀረም:: ምንም እንኳ ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባይኖረውም በእግረ መንገድ ያነሳቸው የአካባቢው ዳራ፣ ገለፃዎች፣ በእኔም የአካባቢ ዳራ ገለፃ ውስጥ በስፋት ተነስተዋል:: ከዚህ በላይ ቀጥተኛ ተመሣሣይነት የሚያሳዩ የመሰሉኝን የLevine ገለፃዎች ደግሞ በማጣቀስ ለማመሳከት ሞክሬያለሁ::

በተጠቀሰው የትምህርት መስክ በግጭት ዙሪያ በአማራ ክልል ከተደረጉት ጥናቶች ደግሞ አንዱ የዮሐንስ ብርሃኑ (እ.ኤ.አ 1998) " Conflict and Conflict Resolution Among the Peoples of Chihera" ነው::

ጥናቱ በአማራ ክልል በሰሜን ጐንደር ዞን ጪሃራ አካባቢ በሚገኙ ስድስት ቀበሌዎች ነዋሪዎች የግጭት ሁኔታዎች እና አፈታት ተሞክሮዎች ላይ የተደረገ ነው:: በጥናቱ መሠረት የአካባቢው ህዝብ ግጭት ውስጥ የሚገባባቸው ቋሚ እና ተለዋዋጭ ምክንያቶች አሉ:: በቋሚ የግጭት ምክንያትነት የታዩትም ውርስ፣ የንብረት መጥፋት፣ ፍቺ እና በጨዋታ መሀል የሚፈጠር አለመግባባት ሲሆኑ በተለዋጭ የግጭት ሰበብነት የተጠቀሰው ደግሞ የክልሉ መንግሥት አርሶ አደሮችን "ቢሮክራት ቅሪት፣ ሀብታም፣ መካከለኛ እና ድኃ" በሚል ፈርጆ ያካሄደው የመሬት ሽግሽግ እና የይዞታ መጠን መለዋወጥ ነው::

ጥናቱ እንደጠቆመው በመሬት ሽግሽጉ ሳቢያ አባቶች እና ልጆች ባሎች እና ሚስቶች ግጭት ውስጥ ገብተዋል:: የአካባቢው ህዝብም ከላይ የተጠቀሱትን ቋሚ እና ተለዋዋጭ ግጭቶች ሁሉ ለመፍታት "የአባት ዕድር ህግ" ብሎ በሚጠራው ሽምግልና ይጠቀማል::

ILS LIBRARY

ይህም ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር በአንዳንድ ነጥቦች ተመሳስሎ ሲኖረው በብዙ ነጥቦች ደግሞ ይለያል።

የእኔ ጥናት ምንም እንኳን የተለያዩ ግጭቶችን እና የእርቅ አፈፃፀምን የሚነካካ ቢሆንም ዋነኛ ትኩረቱ ለደመኝነት የሚዳርጉ ምክንያቶችን፣ ባለደሞችን ለማስታረቅ የሚደረጉ ጥረቶችን፣ የእርቅ አፈፃፀም ቃለ-መሐላዎችን ወዘተ ማሳየት ነው። የደም እርቅን ለመፈፀም የሚደረገው ሽምግልና ማካሄጃ ቦታም የተለያየ መሆኑን ይገልፃል። በደም እርቅ ላይ ግጭት ውስጥ በገቡት ወገኖች መካከል የደም ወደር ወይም አቻ ከሌለ በስተቀር ገዳይ ለወቀሳ እና ለእርቅ አይቀርብም።

ግጭትን እና የግጭት አፈታትን አስመልክቶ ከተደረጉ ጥናቶች መካከል ሌላው የቀለመወርቅ ታፈረ (እ.ኤ.አ. 2000)" Indigenous Institutions of Conflict Resolution Among the Ab'ala Afar in North Eastern Ethiopia" ነው።

የቀለመወርቅ ጥናት ማዕከላዊ ሐሳብ የአብአላ አፋሮች እርስ በርሳቸውም ሆነ ከአጐራባቾቻቸው የትግራይ ደገኞች ጋር በእንስሳት ሀብት መዋያ፣ ግጦሽ፣ ውኃ፣ እና መሬት ምክንያት የሚፈጥሩትን ግጭት በሁለት ዓይነት አካባቢ ወይም አገር በቀል የሽምግልና ጉባኤዎች የሚፈቱ መሆናቸውን ነው የሚያሳየው። ስለሆነም የኔ ጥናት ከቀለመወርቅ በብዙ ነጥቦች ይለያል። ትኩረቱ አንድ ወረዳ ውስጥ በሚኖር አንድ ወጥ ጎበረተሰብ መካከል በሚፈጠር የርስ በርስ ግጭት አነሳስ እና አፈታት ላይ ነው። በመሆኑም ቀለመወርቅ ካደረጉት መንታ ጥናት ይለያል።

በእኔ ጥናት መሠረት የርስ በርስ ግጭት መንስኤዎች በርካታ ናቸው። ስለሆነም የግጭት መንስኤዎችን ዘርዝሮ አድርጐ በማሳየት ረገድ የኔ ጥናት አድማስ ሰፊ ነው። የቀለመወርቅ ጥናት የውስጥ ግጭቶች በጐሳ ተወላጅ አዛውንቶች ወይም መሪዎች የውጭ ቅራኔዎች ደግሞ ተጋጪዎቹ ጐሳዎች በሚሰይሙት የጋራ ጉባኤ ታይቶ እንደሚፈታ ብቻ ነው የሚገልፀው። እንዲሁም አፅንኦቱ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት በሚፈታበት ዘዴ ላይ እንደመሆኑ የእርቅ አፈፃፀም ሥርዓቶችን (rituals) አጠቅሳለሁ። አብራራለሁም። የቀለመወርቅ ጥናት የእርቅ አፈፃፀም ሥርዓቶችን (rituals) አይጠቅስም አያብራራም።

አሰፋ ቶሌራም (እ.ኤ.አ. 1995) "Ethnic Integration and Conflict: The Case of Indigenous Oromo & Amhara Settlers in Aaroo Addis Alem Kirammu area, North Eastern Wellega." በሚል ርዕስ የሠሩት ጥናት አለ።

ጥናቱ በቀደምት ሰፋሪ ኦሮሞች እና በኋለኞቹ ሰፋሪ አማሮች መካከል የሚከሰቱ ልዩ ልዩ ግጭቶች በሽምግልና እንደሚፈቱ እርቁም በመሀላ እንደሚታሰር ይገልጻል። በእርቁ

እና በመሐላው መሠረት ያልፀና ወገን ከማኅበረሰቡ እንደሚገለልም ያወሳል። ይሁንና ይህ ጥናት የደም ግጭት እና እርቅ የሚፈፀምበትን ዝርዝር ሁኔታ ስለማያነሳ ከእኔ ጥናት ጋር ተዛምዶ የለውም።

በሪሁን መብራቱ (እ.ኤ.አ.1996) "Spontaneous Settlement and Inter-Ethnic Relations in Matakal" በሚል ርዕስ በጉሙዝ እና በሰፋሪ አማሮች መካከል የተከሰቱ እና በመከሰት ላይ ያሉ ግጭቶች የተፈቱበትን እና እየተፈቱበት ያለውን ሁኔታ ተመልክተዋል።

በጥናቱ መሠረት ጉሙዞች ለእርቅ ዝግጁ ሲሆኑ የእርቅ ፍላጐት ማሳያ የሚሆኑ ምልክቶችን ማለትም ጥጥ እና ማሽላ፣ ፈቃደኞች አለመሆናቸውን ለመግለፅ ደግሞ ቃሪያ ወይም በርበሬ በምልክትነት ይልካሉ። የእርቅ ፍላጐት ኖሮ ጉመዞች ከአማሮች ጋር ሲታረቁ ለሟች ወገን ካሣ እንደሚቆረጥ እርቁን ለማፅናት ደግሞ ጠመንጃዎችን በመሬመድ እና ሌሎች ትእምርቶችን በማድረግ መሐላ እንደሚፈፀም ጥናቱ ያወሳል።

ይህ ጥናት በመሠረቱ በሁለት የተለያዩ ብሔረሰቦች መካከል ግጭቶች እንደኖት እንደሚከሰቱ እና እንደሚፈቱም የሚያሳይ በመሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር አይገናኝም። የእኔ በአንድ ቋንቋ፣ ባህል፣ እምነት ወዘተ ተናጋሪዎች መካከል የሚከሰት ግጭት እና የግጭት አፈታትን የሚመለከት ነው። በእኔ እና በበሪሁን ጥናት መካከል ያለው አንድ መመሳሰል ጠመንጃ መሬመድ የደም እርቅ መሐላ መፈፀሚያ ተደርጐ በመወሰዱ ላይ ነው።

3.7.2. በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሁፍና 'ፎክሎር' የትምህርት መስክ የተደረጉ ጥናቶች ክለሳ

በዚህ የትምህርት መስክ በግጭት አፈታት ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ስምንት ያህል ሲሆኑ እነርሱም እንደሚከተለው ተከልሰዋል።

መሉጌታ ነጋሳ (1997) "የአዳአ-ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሴረጉማ ከግጭት አፈታት አንጻር" በሚል ርዕስ የሠሩት ጥናት አለ።

ጥናቱ የሚያሳየው በወረዳው ውስጥ የሚከሰቱ ልዩ ልዩ ግጭቶችን ለማብረድ እንዲሁም ተፈጥሮንም ለመለማመን ጭምር የ"ሴረጉማ" ሥርዓትን መፈጸም የተለመደ መሆኑን ነው።

ጥናቱ ከጥናቴ ጋር የሚዛመድበትን የነፍስ ግድያ ግጭት አፈታት ብቻ አፅንኦት ሰጥቼ ሳይም ገዳይን እና የሟች ወገኖችን ወደ እርቅ ለማምጣት በአባገዳ መሪነት የሚፈፀሙ "ሰገዳ፣ ሰንጋ ዲቡ፣ ሰንጋ ቡሩክስ፣ ቢያ፣ ሐርካ፣ ባፈታ ወዘተ" የተሰኙ ልዩ ልዩ ደረጃ ያላቸው የማግባቢያ፣ የእርቅ ማውረጃ እና ማማማያ ሥርዓቶች አሉ። እርቁም

የሚፈፀመው ለሟች ወገኖች የደም ካሣ ወይም ጉማ በመቁረጥ፤ ወይም ሀብት በመስጠት፤ ወይም ሰውም ጭምር በመስጠት፤ ወይም ሁሉንም በመስጠት እንደሆነ ጥናቱ ያመለክታል። እርቁ ይፀና ዘንድም ገዳይ እና የሟች ወንድም ወይም የቅርብ ቤተሰብ ለእርቁ ሥምረት በሚታረደው እንሰሳ ደም ይታጠባሉ። እጃቸውንም በታረደው እንሰሳ አንጀት ውስጥ ከተው ይጨባበጣሉ።

የእኔ ጥናት ከሙሉጌታ ጥናት ጋር ያለው ተዛምዶም ሲታይ እጅጉን የተለየ ነው። ምክንያቱም በመንዝ የደም እርቁ የሚደረገውም በወንዝ፤ በኮረብታ ወይም በቤተክርስቲያን አካባቢ እንጂ በሟች መኖሪያ ቤት አካባቢ አይደለም። ገዳይም በእርቅ ላይ አይቀርብም። በመሆኑም ገዳይና የሟች ወንድም ወይም የቅርብ ቤተሰብ ለእርቁ ሥርዓት በሚታደረው እንሰሳ ደም አይታጠቡም። በአንጀቱም ውስጥ አይጨባበጡም። ብዙ ጊዜም የደም ካሣም አይቆረጥም። ስለዚህ ግኝቶቻችን የተለያዩ ናቸው።

ሰለሞን ሣህሌም (1998) "የግጭት አፈታት በሲቡ ሴራ ኦሮሞዎች" በሚል ርዕስ ያካሄዱት ጥናት አለ።

ጥናቱ እንደሚያሳየው በአካባቢው በልዩ ልዩ ምክንያት ማለትም በድንበር፤ በሴት ጠለፋ፤ በሰው ሚስት መድፈር፤ በስካር፤ በባልና ሚስት አለመግባባት ወዘተ የሚከሰቱ ግጭቶችን በሽምግልና መፍታት የተለመደ ነው።

በተለይም የነፍስ ግድያ ግጭት ሲከሰት የገዳይ ወገኖች ከሟች ወገኖች እየሸሹ በመቆየት ወደ አካባቢው አባገዳ በመሄድ ሽምግልና ይጠይቃሉ። አባገዳውም የሟች ወገኖች ለእርቅ እንዲቀርቡ አካለ-ምሉዕ እና አካለ-ጉዶሎ ሰዎችን አውጣጥቶ በማለዳ እየሄዱ እግዚኦ እያሉ ለእርቁ እሺ እንዲሉ እንዲያደርጓቸው ይልካል። ተማላጆቹ እሺ ሲሉም ገዳይ እና ሟች ወገኖች የየራሳቸውን ሽማግሌዎች መርጠው ሽምግልናው ማክሰኞ፤ ረቡዕ እና አሁድ ቀናት ተካሂዶ እርቅ እንዲወርድ የሚደረግ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል።

እርቁም የሚፈጸመው በወንዝ ዳር ነው። ለደም ማድረቂያም አዳል በግ በገዳይ እና በሟች ወንድም በጋራ ይታረዳል። አርደውም እጃቸውን በበጉ አንጀት ውስጥ አስገብተው ይጨባበጣሉ። ግንባራቸውንም በበጉ ደም ይቀባሉ። ብቅልም በጋራ በአንድ ዋንጫ ይጠጣሉ። ከዚያም የታረደውን በግ ሥጋ ዘጠኝ ቦታ ቆራርጠው በያቅጣጫው ጥለው ወደየቤታቸው እንደሚሄዱ እና በየተራም ድግስ ደግሰው እንደሚገባበዙ ጥናቱ ያመለክታል።

በሰለሞን እና በእኔ ጥናት መካከልም ብዙ ልዩነቶች ይገኛሉ። በእኔ ጥናት ለነፍስ ግድያ እርቅ ማካሄጃነት የሚመረጡት ቀኖች የወንድ መላዕክት፤ ሰማዕታት፤ እና ሐዋርያት ክብረ በዓላት ናቸው። ለደም እርቅ መሐላ መፈፀሚያነት የሚታረደው እንሰሳ ሥጋም

አይጣልም። ይልቁንም ይበላል። ለእርቅ ማባባል አካሉ-ጉዶሎ ሰው ሥራዬ ተብሎ አይጨመርም። ገዳይ በሽምግልናም ሆነ በእርቅ ላይ አይገኝም። እንዲሁም በአመዛኙ የደም ካሣ አይቆረጥም። አይበላምም።

ይልማ ተፈሪም (1998) "የሽምግልናና እርቅ ሥርዓት በወላይታ" የሚል ጥናት አካሂደዋል። በጥናቱ መሠረትም የወላይታ ብሔረሰብ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀምባቸው "ጫሜታ፣ ጨቆ፣ ጨጫ ጫቻ" የሚባሉ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት አሉት።

በወላይታ ብሔረሰብ "ጨጫ ጫቻ" ማለትም የነፍስ ግድያ ግጭት መፍቻ መሠረትም ገዳይ ሰው በመግደሉ ተፀፅቶ ሽማግሌዎችን በምስጢር አነጋግሮ ወደሚች ቤተሰብ ይልካል። የሚች ወገኖች ለእርቅ ሲስማሙ ገዳይ ፊቱን ጥላሸት ተቀብቶ (ተለቅልቆ) በደረቀ የከብ ቅጠል አካሉን ሸፍኖ ወልዳ ያበቃች ላም እና ወልዳ ያበቃች በግ ጮትቶ አንገቱን አቀርቅሮ "አጥፍቻለሁ ማሩኝ" እያለ ከሽማግሌዎቹ ፊት ይቀርባል። በዚህም ወቅት ከሀገር ሽማግሌዎቹ መካከል ታላቅ የሆኑት "ገዳይ ደንቡን አሟልቶ ይቅርታ ጠይቋል እና ይቅር በሉት" በማለት የሚች ወገኖችን ይጠይቋቸዋል። እነሱም ይቅር ይላሉ። ገዳይ ለእርድ ያቀረባቸውን እንሰሳትም አንዱ ሽማግሌ ይባርኳቸዋል። ከዚያም ሽማግሌው ደማቸውን በሌባ ጣታቸው እያጠቀሱ ገዳይን እና የሚችን የቅርብ ቤተሰብ ቀጥሎም የገዳይና የሚችን ወገኖች ሁሉ እመሃል ግንባራቸው ላይ ይቀቧቸዋል።

በመጨረሻም ገዳይና የሚች የቅርብ ሰው ጐን ለጐን ተቀምጠው፣ በነጠላ ተጋርደው በአንድ ዋንጫ ተሞልቶ የቀረበ ብርዝ ወይም ጠጅ በጋራ ጨብጠው አፋቸውን አቀራርበው በአንድ ትንፋሽ አብረው እንዲጠጡ ይደረጋል። የታረዱት እንሰሳት ሥጋም እዚያው ተጠብሶ ተሰብሳቢዎች ሁሉ እንዲቃመሱት ይደረጋል።

በእኔ ጥናት መሠረት በገዳይ እና በሚች ወገኖች መካከል የደም-መከፋፈል ዕቅዱታ ከሌለ በስተቀር ገዳይ ለእርቅ አይቀርብም። ስለሆነም በይልማ ጥናት ውስጥ እንደታየው ገዳይ ቀርቦ የሚፈፅማቸው ተግባራት ሁሉ በእኔ ጥናት ውስጥ አይታዩም።

"ሀገረሰባዊ የግጭት መፍትሔ ሥርዓት በዶኮ-ጋሞ" በሚል ርዕስ ተመስገን ምንዋጋው (1998) የሠሩት ጥናትም ሌላው ተከላሽ ነው።

በጥናቱ መሠረት ዶኮ-ጋሞ ውስጥ የሚያጋጥሙት ዋና ዋናዎቹ ግጭቶች የሚመነጩት በዘመዳሞች መካከል በሚፈፀም የግብረ-ሥጋ ግንኙነት፣ የሰው ሚስት በመድፈር፣ በድንበር፣ በጎሳ እና በነፍስ ግድያ ምክንያት ነው።

ከላይ የተጠቀሱት የግጭት ዓይነቶች ሁሉ ደግሞ መለኮታዊ ኃይል አድሮባቸዋል ተብለው በሚመለኩ "የግጭት መፍትሄ ሹማምንት የግጭት መፍትሄ አደባዮች" አማካኝነት በእርቅ ይፈታሉ። ግጭቶቹን ሁሉ በእርቅ ለመፍታት የሚያገለግሉ ስምንት ያህል ሀገረሰባዊ የግጭት መፍትሔ ተቋማት እንደሚገኙም ጥናቱ ያወሳል። ከተጠቀሱት የግጭቶች መፍቻ ተቋማት መካከልም ማካ /የዘመዳሞች ወሲባዊ ግንኙነት መፈፀም እና የሰው ሚስት መድፈርን/፣ ጊቃ ኢቃ/ የድንበር ይገባኛል ጥያቄና አለመግባባትን/፣ ካሬ /ከሌላ ማኅበረሰብ ጋር የሚከሰቱ አለመግባባቶችን/፣ በላና ደና /የነፍስ ግድያ ግጭትን እንዲሁም ልዩ ልዩ ወይም ማናቸውም ዓይነት ግጭትን/፣ ዎጋ ኤራሶ (ሥርዓት አዋቂ) ደግሞ ከላይ በተጠቀሱት ተቋማት መፍትሔ ያላገኙ ወይም ለአካባቢው እንግዳ የሆኑ ግጭቶችን/ የሚፈቱ ተቋማት ናቸው።

በእኔ ጥናት መሠረት የዘመዳሞች የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ለአደባባይ አይበቃም። ጥናቴ ያተኮረው በርስ በርስ ግጭት በተለይም በዐብይነት በደም እርቅ ላይ ስለሆነ ከሌሎች ማኅበረሰቦች ጋር ያሉ ግጭቶችን ሁኔታ አይዳስስም። እንዲሁም በእኔ ጥናት የነፍስ ግድያ እርቅ የሚፈፅምባቸው ቀኖች ብዙ ናቸው። በእጣቸው ጥናት መሠረት የግድያ እርቅ የሚፈፀመው በዕለተ ዓርብ ብቻ ነው።

ወንድወሰን አውላቸው (1998) "የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ አስተዳደርና የግጭት አፈታት" በሚል ርዕስ ያካሄዱት ጥናትም አለ።

ይህ ጥናት ያተኮረው የግጭት ሰበቦችን፣ የግጭት ዓይነቶችን እና መፍትሔዎችን ማመላከት ላይ ነው። በመሆኑም በአካባቢው ድንበር መጋፋት፣ ስርቆት ድብደባ፣ ክህደት፣ ስድብ፣ ቤት ማቃጠል፣ ንብረት ማጥፋት የግጭት መነሻ ምክንያት ወይም ሰበብ ሆነው ተገኝተዋል። የግጭት ዓይነቶች ሆነው የተገኙት እና የሰፈሩት ደግሞ የቤተሰብ፣ የልጆች፣ የመሬት፣ የጐሳ የሚሉት ሲሆኑ ለተጠቀሱት የግጭት ዓይነቶች መፍትሄ መስጫዎቹ ደግሞ የመኖሪያ አካባቢን እና ጐሳን መሠረት አድርገው የተዋቀሩ ሁለት ዓይነት ተቋማት ናቸው። እነዚህም ተቋማት ስምንት ዓይነት የአስተዳደር መዋቅር አላቸው። እነሱም ቤተሰብ፣ ቤተዘመድ፣ ጐሣ፣ አካባቢ፣ "ጀፎጊ" እና "ቃየ" እንዲሁም ክፍለ-ጉራጌ እና "የጅካ" የተሰኙ ናቸው። ተቋማቱ ግጭቶቹን የሚፈቱትም በሽምግልና እና እርቅ እንዲሁም ዳኝነት በማየት ነው።

በጥናቱ መሠረት የደም ግጭት በማንአለብኝነት፣ እና በጥንቃቄ ጉድለት ይከሰታል። የደም ግጭት በሚከሰት ጊዜም ግጭቱ በሰባት ቤት ጉራጌ "ቂጫ" መሠረት ክርክር ተካሂዶ፣ የገንዘብ ቅጣት ተጥሎ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ እስከ አሥራ ሁለት ትውልድ

ድረስ የሚቋጠሩ የገዳይ እና የሟች ወገኖች ከአንድ ወንዝ ውኃ አይቀዱም። አብረው ከአንድ ገበያ ላይ አይውሉም። በሰርግና በለቅሶ በዕድር አይገናኙም ።

ጥናቱ በደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት ላይ ያተኮረ እና ውሱን ስለሆነ፤ እንዲሁም የደም እርቅም በሽማግሌዎች ፊት በሚደረግ ክርክር ሣይሆን በሽምግልና የሚፈፀም፤ የገንዘብ ቅጣትም የማይጣልበት መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ፤ እንዲሁም የደም እርቅ አፈፃፀም ሂደትን (ቅድመ-እርቅ እና የእርቅ ወቅት እንዲሁም ድህረ-እርቅ ሁኔታ) አካቶ በማሳየቱ ይለያል።

በአማራ ክልል ከተደረጉ ባህላዊ የግጭት አፈታት ጥናቶች ክለሳዬ ውስጥ የማካትተው ጥናት ደግሞ "ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በባህር ዳር ነገዴ (ወይጦ) ጎበረተሰብ" በሚል ርዕስ አየለ ፍቅሬ (1998) ያቀረቡትን ነው።

ጥናቱ እንዳመለከተውም ጎበረተሰቡ በመካከሉ የሚከሰቱ ልዩ ልዩ መለስተኛ ግጭቶችን በእርስ በርስ ውይይት እና ምክክር እንዲሁም በባልና ሚስት መካከል እና በነፍስ ግድያ ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶችን ደግሞ በሽምግልና የመፍታት ልማድ አለው።

በተለይም የእርስ በርስ ግድያ ግጭትን ለመፍታት ገዳይ ወደ አበጋሩ ሰው ልኮ ሽምግልና እንደሚጠይቅ፤ አበጋሩም ዋነኛው የሽምግልና እና የሽማግሌዎች አሰባሳቢ እና ሰብሳቢ ሆኖ በማደራደር መበቃቀልን እንደሚያስቀር እና እርቅን እንደሚያወርድ ጥናቱ ይገልፃል።

ጎበረተሰቡ ከአማራ ብሔር ተወላጆች ጋር ደም ሲቃባም ከሁለቱም ወገኖች በሚውጣጡ የሀገር ሽማግሌዎች አማካኝነት ግጭቱን ለማብረድ እንደሚሞክር ሆኖም የሽምግልናው ሂደት እንደ እርስ በርሱ ቀላል እንደማይሆንም ጥናቱ ይጠቁማል። በተለይም የእርስ በርስ የደም ግጭቱ እርቅ በዋነኝነት የሚፈፀመው የደም ካሣ በመቁረጥ መሆኑን፤ እርቁም ሲፈፀም ዓመድ በገል ቀርቦ የገዳይ እና የሟች ወገኖች ሁለት ጠመንጃዎችን ተራምደው እና በግ ወይም ፍየልም አርደው ላለመከዳዳት እና እርቁን ላለማፍረስ መሐላ እንደሚፈጽሙ ሲያመለክት አልፎ አልፎ ግን ገዳይ አካባቢውን እንዲለቅ የሚደረግ መሆኑንም ያመለክታል።

ከላይ ከቀረበው ጭምቅ ሃሳብ በመነሳትም በእኔ እና በአየለ ጥናቶች መካከል ያሉ ልዩነቶችን እጠቁማለሁ። የጥናቴ መሠረት የሆነው ህዝብ እምነት ከአየለ የጥናት መሠረት ህዝብ እምነት የተለየ ስለሆነ፤ እንዲሁም ለነፍስ መጠፋፋት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮችን ስለሚዘረዝር፤ በድብደባም ሆነ በደም እርቅ ወቅት ባመዛኙ የደም ካሣ የማይቆረጥና የማይበላ ስለሆነ፤ በደመኞች መካከል የደም ወደር ከሌለ በስተቀርም ገዳይ በእርቅ ላይ

ስለማይገኝ፣ ደመኞችን ለማስታረቅ ተነሳሽነቱን የሚወስደውና የሚጥረውም አንድ የታወቀ አካል (ተቋም) ብቻ ስላልሆነ (በአየለ ጥናት ዋናው አበጋሩ ነው።) ጥናቱ ይለያል።

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር ባሉ አካባቢዎች ከተደረጉ የግጭት አፈታት ጥናቶች መካከል ሌላው "አበጋር ባህላዊ የግጭት አፈታት በተሁለደሬ ወረዳ" በሚል ርዕስ ነግነት መኮንን (1998) ያቀረቡት ነው።

ይህ ጥናት ተጠቃሎ ሲታይ ያተኮረው በአበጋር ምንነት፣ አወቃቀር፣ በአበጋር አማካኝነት የሚፈቱ የግጭት ዓይነቶችን በመዘርዘር እና በእርቅ አፈፃፀሙም ላይ የሚፈፀሙ አድራጎቶችን በመግለፅ ላይ ነው። በጥናቱም መሠረት አበጋር ማለት፡- "የጠብን ገዳና የማይፈልግ ከዱአ በስተቀር ሌላ የማያውቅ አስታራቂ" ነው። በማስታረቅ ሚናውም በህዝቡ ዘንድ የተፈራ፣ የተከበረና የታመነ ሲሆን በአወቃቀርም ሁለት ዓይነት ማለትም "የዘር" እና "የመንደር" አበጋር የሚሰኙ አሉ። አበጋሮችም እርቅን ለማስፈፀምም መቁጠሪያ፣ ዘንግ፣ ድቤ፣ ጭራ፣ አንካሴን" ይጠቀማሉ።

ጥናቱ አበጋር የእስልምናን ኃይማኖት የሚከተሉ ሰዎች የግጭት መፍቻ ስልት መሆኑን፣ በአበጋር አማካኝነትም ከቀላል ፀብ እና ግጭት እስከ ግድያ ያሉት ግጭቶች እንደሚፈቱ ያሳያል። በተለይም የግድያ እርቅ የሚደረገው (ምንም እንኳን በደጋና በቆላ መጠኑ የሚለያይ ቢሆንም) የጉማ ገንዘብ ተከፍሎ መሆኑን ያወሳል። ገዳይ ለእርቅ ሲቀርብም ቀሚስ ያጠልቃል። ገዳይ እና የሟች ወገኖች እርቅ ሲፈፅሙም የቀይ በሬ ደም ይፈሳል። ጥናቱ በተጨማሪም ገዳይ እና ወገኖቹ እንዲሁም የሟች ወገኖች ጥርሳቸውን ግንባራቸውን እና አገጫቸውን በተጠበሰ ወይም በጥሬ ሥጋ እንደሚፈገፍጉ፣ የጥርስ መፈግፈግም ለገዳይ እና ለሟች ወገኖች የወደፊት መፈቃቀድ አስተዋፅኦ አለው ተብሎ እንደሚታመን፣ አጠቃላይ የእርቅ ሥርዓት ሂደቱም ጫት በመቃም ፀሎት በማድረስ፣ በምርቃት እና በእርግማን (ለመጥፎ ነገር) እየታጀበ እንደሚፈፀም ያመለክታል።

የእኔ ጥናት ከነዓነት ጥናት የሚለይባቸው ነጥቦች አሉ። ይኸውም ጥናቱ የእስልምናን እምነት እና እውቀት እንዲሁም አድራጎት በሚከተል ህብረተሰብ ውስጥ የተደረገ ስላልሆነ፤ ላሎ-ማማ ውስጥ የሀገር ሽማግሌ ለመሆን የዝርያ አመጣጥ ግዴዊ መስፈርት ስላልሆነ፤ ላሎ-ማማ ውስጥ በድብደባም ይሁን በደም እርቅ ባመዛኙ የደም ካሣ የማይበላ ስለሆነ፤ በደም እርቅ ላይ የደም ወደር ወይም አቻ ከሌለ በስተቀር ገዳይ ለእርቅ የማይቀርብ ስለሆነ ይለያል። እንዲሁም ለእርቅ ማሳረጊያ የሚቀርበውን የእርድ እንስሳ ሽንጥ ሥጋ የገዳይ እና የሟች ወገኖች ከተቋረጡት በኋላ በሽምግልናው ላይ የተገኙ ሁሉ እንዲቃመሱት ከመደረጉ ውጪ ለሌላ ተምሳሌታዊ አገልግሎት አያገለግልም ወይም አይውልም።

አሁንም በአማራ ክልል ከተካሄዱት ባህላዊ የእርቅ ሥርዓት ጥናቶች መካከል ሌላው "ባህላዊ እርቅ በምሥራቅ ጐጃም መስተዳድር ዞን በደባይ ጥላትግን ወረዳ" በሚል ርዕስ ዮሴፍ ጌትነት (1998) ያቀረቡት ነው።

ጥናቱ ያተኰረው የግጭት መነሻ ምክንያቶችን፣ የግጭት ዓይነቶችን እና የግጭት መፍቻ ተቋማትን በመግለፅ እና የእርቅ አደማደም ሥርዓት መሐላዎችን በማመላከት ላይ ነው። ስለዚህም በጥናቱ መሠረት ዋነኛ የግጭት ምክንያቶች ሆነው የተገኙት የእርሻ እና የግጦሽ መሬት እጥረት ሲሆኑ፤ የፀብ ወይም የግጭት ዓይነቶቹ ደግሞ ድንገተኛ ወይም የዕለት፣ ቂም በቀል እና ደም ምለሳ ናቸው። የግጭት መፍቻ ተቋማቱ ደግሞ ሽምግልናና "ስቅላት" ናቸው። ጥናቱ እንደሚያሳየው የደም እርቅ የሚፈፀመው "ሽምግልና" በተሰኘው ተቋም ሲሆን በእርቁም ወቅት ታራቂዎቹ እና እስከ አራት ትውልድ ድረስ የሚቋጠሩ የታራቂዎቹ ዘመዶች እና ማኅበርተኞች ጐረቤቶች እና እርቁ የሚካሄድበት ጐጥ ነዋሪዎች ይገኛሉ።

እርቁም ይሰምር እና ይፀና ዘንድ ታራቂዎቹ ውል ይፈራረማሉ። ጥይት የጐረሱ ሦስት ጠመንጃዎችን በመራመድ ያለመከዳዳት መሐላ ይፈፅማሉ። በመጨረሻም ደመኞቹ አንድ በግ በጋራ ባርከው የተጠበሰውን ሥጋ ይጐራረሳሉ። ሽማግሌዎቹ እና የታራቂዎቹ ወገኖችም ሥጋውን እና ሌላም የተገኘውን መስተንግዶ ይቃመሳሉ።

የእኔ ጥናት ቅድመ-የደም እርቅ ጥያቄ ወይም ጥሪ አደራረግ ሂደትንም ያካትታል። በእኔ ጥናት ግኝት መሠረት ለደም መቃባት የሚያበቁት ምክንያቶች የእርሻ እና የግጦሽ መሬት እጥረት ብቻ አይደሉም። በደመኞች መካከል የሚወዳደር (የሚገዳደር) ማለትም የደም ዕኩሌታ ወይም የደም አቻነት ከሌለ በስተቀርም ገዳይ ወይም ገዳዮች በሽምግልና ድርድሩም ሆነ እርቁ ላይ አይቀርቡም። እንዲሁም በእኔ ጥናት አስተውሎት እና ግኝት መሠረት ስቅላት እንደ አንድ የግጭት መፍቻ ሥልት፣ ዘዴ እና ተቋም ሊታይ የሚችል ቢሆንም ዘወትር እርቅን እና ሰላምን የሚያመጣ እና የሚያስገኝ ባለመሆኑ ይለያል።

ከዚህ በማስከተል ከርዕሰ-ጉዳዬ ጋር ተዛምዶ ያለውን የደመኞችን እርቅ የሚመለከተውን የማህተመ ሥላሴ (1960) ጥናት እቃኛለሁ። ማህተመ ሥላሴ (1960) "የኢትዮጵያ ባህል ጥናት ቡልጋ" በተሰኘው ሥራቸው የቡልጋ ሕዝብ ግጭቶችን የሚፈታው በሀገር ሽማግሌዎች የሽንጐ ሥነ-ሥርዓት መሆኑን አውስተዋል። በተለይም ግጭቱ የደም ከሆነ ደግሞ እርቁ የሚፈፀመው ገዳይን አገር በማስለቀቅ ብቻ እንደሆነ ገልፀዋል። እርቁም ይፀና ዘንድ ገዳይ እና ባለደሙ የሽንጥ ሥጋ እንደሚቋረጡ የአገር ሽማግሌዎቹ፣ የታራቂዎቹ እና የታራቂዎቹ ዋሶች ስሞችም በአካባቢው ቤተክርስቲያን ውስጥ በሚገኝ ዐቢይ መጽሐፍ ላይ እንዲሰፍር የሚደረግ መሆኑን ፅፈዋል።

ማህተመ ሥላሴ ያወሱት የደም እርቅ አደራረግ እና የመሐላ አፈጻጸም ሥርዓት ገለፃ ከሌሎቹ ጥናቶች ሁሉ ለጥናቴ ግኝት ቅርበት ያለው ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ይህም የሆነው ቡልጋ እና መንዝ ተቀራራቢዎች በመሆናቸው ይመስላል።

የኔ ጥናት ከማህተመ ሥላሴ በግልፅ የሚለየው በሁለት ነገሮች ብቻ ነው። ይኸውም በኔ ጥናት ግኝት መሠረት ገዳይ የደም ወደር እስከሌለ ድረስ በእርቅ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ከባለደሞች (ከሟች ወገኖች) ጋር አይገናኝም። ሽንጥ ሥጋም አይቋረጥም። ይህ የሚደረገው በገዳይ ወገኖች እና በሟች ወገኖች ነው። ሁለተኛው የጥናቴ ልዩነት የገዳይ እና የሟች ወገኖች የእርቅ ሥርዓት ሂደት የሚሰነደው በቤተክርስቲያን መጽሐፍ ገጽ ውስጥ አለመሆኑ ነው። በእኔ ጥናት ግኝት የደም እርቅ ፈፃሚዎች፣ የአስታራቂ ሽማግሌዎቹም ሆኑ የዋሶቹ ስሞች፣ ስምምነቶች እና ገደቦች የሚሰነዱት በተራ ወረቀት ነው። የሚያዙትም በታራቂዎቹ እና በዘመድ ዳኛው ነው።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የሌሎችን እና የራሴን ጥናት በማነፃፀር ያቀረብኩት ጥናቴ የሚያሳየው የተለየ ባህል መሆኑን ለማመላከት ነው።

4. የላሎ-ማማ ምድር ግጭት እና የግጭት አፈታት ሥርዓት

በዚህ ምዕራፍ የላሎ-ማማ ምድር ወረዳ ሕዝብ የግጭት መንስኤዎች ተፈትሽዋል። በተለይም ደግሞ ቅድመ እና ድህረ ግድያ ሁኔታዎች ተመርምረዋል። የግጭት አፈታት ሥልቶችም ታይተዋል። የደም ግጭትን በመፍታት ሂደት ውስጥ የሚታዩ ቅድመ እና ድህረ ዕርቅ ክንውኖች ተወስተዋል። የደም ግጭት እርቅ ጥያቄ አቀራረብ፣ አመላለድ፣ ድርድር እና እርቅ አፈጻጸም የሚሉትም ተዳሰዋል። በምዕራፉ መገባደጃ ላይም ድህረ-ዕርቅ የግንኙነት ሁኔታ እና ባህላዊ የደም ማድረቅ ዕርቅ ሥርዓቱ ያለበት ወቅታዊ ሁኔታ ተመላክተዋል።

4.1. የላሎ-ማማ ምድር ነዋሪዎች ግጭት መንስኤዎች

ላሎ ማማ ወረዳ ውስጥ ለሚከሰቱ ግጭቶች መንስኤዎቹ እና ምክንያቶቹ ምን? ምን? ናቸው፣ ለነፍስ ግድያ የሚያበቁትስ ምን? ምን? ግጭቶች ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለሁሉም ቁልፍ ወይም አውራ የመረጃ ተባባሪዎቼ ባነጋገርኳቸው ጊዜያት ሁሉ አንስቼባቸው ነበር። እነሱም እንደመለሱልኝ የግጭት እና የግድያ ሰበብ ምክንያቶች ብዙ እና የተለያዩ ናቸው። ለነፍስ ግድያ የሚያበቁትን ምክንያቶችም በደረጃ ለማስቀመጥ ይቸገራሉ። በአጠቃላይ ግን የላሎ ማማ ምድርን ነዋሪዎች የሚያጋጩ፣ የሚያቀያይሙ፣ የሚያኳርፉ፣ የሚያደባድቡ እና የሚያጋድሉ ያሏቸውን ነጥቦች እንደሚከተለው ዘርዝረውልኛል።

ከሁሉም የመረጃ ተባባሪዎች እንደበት እንደሰማሁት ቀደም ባለው ዘመን ማለትም በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ-መንግሥት ዋናው መጋጪያ መሬት ነበር። የመሬት ተወላጅ ነኝ የይገባኛል ጥያቄ የርስት ክርክር ወይም አለመግባባት። ከዚሁ ጋር በዚያኑ ዘመን ይታይ ወይም ይከሰት የነበረው እና አሁንም የሚታየው የግጭት መነሻ አፍ እላፊ ነው። ከአፍ እላፊም ደግሞ አጥንት ወይም "ትውልደ-ሐረግ" የሚነካው። በተለይም ከዚህ ከ"አጥንተ-ነክ "ወይም "አጥንተ ነጭነት ማጕደፍ"ጋር በተያያዘ የተከሰተ ቆየት ያለ ግድያ ትዝታቸውንም (አቶ ሽዋይር ጋ" አስፋው በ13/5/99) እንደሚከተለው አውግተውኛል።

> *"አንድ ጊዜ ይገም አጥቢያ ዳኛ ችሎት ላይ ሙግት ነበረብኝ :: እዚያ ተቀምጬ ፋይሌን ስጠባበቅ የሁለት ለምድር ሰሰማይ የከበዱ ሰዎች ክርክር ይካሄድ ነበር። ጭብጡ የመሬት ነበረ። ፋይላቸው ተቀጥሮ ወደ ኋላ መለስ ሲሉ አንደኛው ሰውዬ ሌላኛውን "አንተ ምነው አባትህን ጠርተህ እናትህን ሳትደግም እናቱ ርስት ላይ ወደቅህ? አሏቸው::" ተሰዳቢው መልስ ሳይሰጥ ስድቡን ሰው ሁሉ የሰማባቸው ይመስል በቅሏቸውን ዝፈው ሄዱ:: ሌሊቱን ያን የሰደባቸውን ሰውዬ ከነቤተሰቡ፣ ከነንብረቱ አቅልጠውት አደሩ::"*

እርሳቸው እንደነገሩኝ ገዳይ ግድያውን የፈፀሙት ይሚገታቸው የነበረው የእህታቸው ባለቤት ሰው የማያውቀውን የእናታቸውን ባይተዋርነት/ እናታቸው የጌታ ገረድ ነበሩ/ በመግለጹ ነው። ስለሆነም ሰው ዘሩን ራሱ የሚያውቀው ቢሆንም ሌላ ሰው በአደባባይ እንዲዘራበት አይፈልግም።

ሁሉም የመረጃ ተባባሪዎቼ በተመሳሳይ ሁኔታ እንደገለፀልኝም በደርግ ዘመነ-መንግሥት ደግሞ በድንበር፣ በመሬት አከፋፈል እና ድርሻም ግጭት እና ግድያ ነበር። አሁንም የመረጃ ተባባሪዎቼ እንደነገሩኝ ቂም በቀል በተለይም "ቤተ-ደመኝነት" ወይም "አበ-ደምነት" ሌላው መጋጪያ እና መገዳደያም ነው።

ብዙዎቹ እንደሚሉት የቆየ ደመኝነት ላሎ-ማማ ውስጥ አረም አይውጠውም፣ ጊዜም አይሽረውም። እነርሱ እንደሚሉት ለዚህም ምክንያቱ ባለ-ደሙ ቂሙን ቢረሳው ጐረቤቱ እና አገሩ አያስረሳውም። እዳር ያለው ያልተነካው ሰው ወገኑ በሰው እጅ ያለፈበትን ሰው በነገር እየጐነታተለ ተበዳዩ ወይም ባለደሙ የረሳውን ሌላው ያስዘክረዋል (አቶ ገብረወልድ ገ/ጻድቅ፣ መቶ አለቃ ሽቤ ጣልባቸው፣ አቶ መንግሥቴ አማረ በ18/5/99)፣ (አቶ ቀጥይበሉ አሳምነው በ17/5/99)፣ (ቄስ ማሞ ጸደቀ፣ አቶ ደጀጠና መንግስቱ አርሶ አደር በ7/5/99)፣ (አባ ዘውዴ ደምድም አርሶ አደር፣ አቶ ሽዋይርጋ አስፋው በ13/5/99) እንዳጫወቱኝ የመንዝ ሰው ደሙን ያልተወጣን ሰው ማበጃጀት ማለትም ማሳጣት ያውቅበታል። እዚህ አቶ ቀጥይበሉ አሳምነው የነገሩኝን አንድ ምሳሌ እጠቅሳለሁ።

> *"ወንድሜ ወገንህ በሰው ተገድሎብህ አንድ ገደብ ከሌለህ በስተቀር አገርህ ላይ አርሰህ፣ አምርተህ፣ ከብረህ አልበህ፣ ጋልበህ፣ አርደህ፣ አጊጠህ፣ በየድግሱ በየስመ-በዓሉ ከሰው ጋር ሸንተህ፣ ኮርተህ ለአዝማሪ ግጥም ተቀበል ብለህ፣ አትኖርም። ሰው ያሸሚጥጥሃል፣ ያማሃል፣ ይጠቃቀስብሃል። ይሄ ደግሞ አይመረው፣ አይተኩሰው፣ አይከረፋው፣ ሆድ-አደር እያለ ይሞልቄሃል። ድንገት ደግሞ ቀን ጐድሎብህ ከአንዱ ጋር በትንሽ ነገር ከተጋጨህ ደሞ ነጩን ይነግርሃል። 'እኔ ደመኛህ አይደለሁም ሂድና ደመኛህን ፈልግ ደምህ ካለበት አለ። መጀመሪያ እሱን መልሶ ብሎህ ቁጭ ይላል። በተለይ ደግሞ ጠመንጃ ናርህ ከሆነማ ይሄ ሁሉ ለበግ እና ለከብት መጠበቂያ? እያሉ ያመሃል። ደግሞ ደፈር ብለህ በየሰርግ ቤቱ፣ በየስመ-በዓሉ ከሸለልህ አፀፋው የገዳ ነው።*
> *"ሸለለው ሸለለው ምንድነው ምላሹ፣*
> *ባልቤን በምንሸር በእሞን በዲሞፍተር ደምን ታልመለሰ።*
> *እንዲያ እንዲያ እያሉ ገድለህ እንድትነቀል ይገፋፋሃል"*

በማለት አጫውተውኛል።

አሁንም ብዙዎቹ የመረጃ ተባባሪዎቼ ደጋግመው ያነሱልኝ ሌላው የግጭት እና የግድያ ምክንያት ደግሞ የሰው ውሸማ፣ ቅምጥ፣ እጮኛ እና ሚስት ማዳራት፣ ማሽኮርመም፣ ማማገጥ ወይም መድፈር ነው። በተለይ የሰው ሚስት መድፈር ምህረት

የሌለው የመረረ ፀብ ያስከትላል። ሚስቱ ተደፍራበት ዝም ያለ ሰውም እንደሰው አይቆጠርም ከሰው ተራ የወጣ ነው። ይሸለልበታልም።

ኧረ ጅል የሞተው ኧረ ጅል የሞተው፣
ሚስቱን ወሰዱለት ከገቢያ ነድተው።
ኧረ ጅል የሞተው ኧረ ጅል የሞተው፣
ሚስቱን ወሰዱለት በገመድ ጐትተው።
ኧረ ምን ያለው ነው ሐሞተ ደንዳና፣
ሚስቱን ሲያማግጧት /ሲያባልጓት/ የሚፈልግ ዳኛ።
በለው በውሸግራ በለው በወጨፎ አስኪደው በዋንዛ
ባባት አገር እና በሚስት የለም ዋዛ።

በሚል የሽለላ ቃልም ተበዳይ የባሰውን ይጐሸማል ማለትም ይሰደባል። ስለሆነም በዚህ ሁሉ ነገር ጆሮው የገማው /የመረረው ለማለት ነው/ ባያስበውም ይገድላል ይላሉ። እዚህ ላይ ሴቶች የግጭት መንስኤዎች ብቻ አለመሆናቸውንም ጠቁሞ ማለፍ ተገቢ ይሆናል። ከአንዳንድ የላሎ-ማማ ምድር ነዋሪዎች እና የአገር ሽማግሌዎች እንደተረዳሁት ሴቶች ለፀብ መክረር ወይም መብረድ ያላቸው ሚናም ከፍተኛ ነው። ምክራቸው የዋዛ አይደለም። አልጋ ላይ ሀሳብ የሰጡበት ነገርም (ለበጐም ይሁን ለክፉ) በቀላሉ አይፈታም ነው የሚባለው። በመሆኑም ሴቶች ባሎቻቸውን፣ ወዳጆቻቸውን፣ ወንድሞቻቸውን እና ልጆቻቸውን መላልሰው " ይህን ነገር ተው፣ አርፈህ ተቀመጥ፣ ኑሮህን አታበላሽ፣ ልጆችህን አሳድግ፣ ቤተሰብህን ሰብስብ፣ ግልግል ይግባህ ካሏቸው ግጭቱ ይበርዳል። በአንፃሩ "ጥቃት ገባን፣ ተደፈርን፣ ውርደት ገባን፣ የአገር መሣለቂያ ሆንን ወዘተ" እያሉ ከነሰቲቸው ማለትም ከጨቀጨቋቸው ደግሞ "ሴት የላከው ሞት አይፈራም" እንዲሉ ግጭቱ የበረታ ይሆናል። እናም ሴቶች የግጭት መንስኤ ብቻ ሳይሆኑ አርጋቢዎችም አደፋፋሪዎችም ናቸው የሚል ሥር የሰደደ አስተሳሰብ አለ።

የላሎ-ማማ ነዋሪዎች ከላይ ከተጠቀሱት የግጭት ምክንያቶች በተጨማሪም የውርስ ሀብት (ንብረት) ክፍፍል ይገባኛል ባይነት ጭቅጭቅ፣ የመሬት ጥበት እና የድንበር መጋፋት፣ እንዲሁም በመልካም አስተዳደር እጦት፣ ወይም እጥረት ማለትም በእርዳታ እህል ይገባኛል፣ ወይም አንሶኛል፣ በዳኝነት ተዛብቶብኛል ወይም ተጓድሎብኛል ምክንያት ግጭት ውስጥ እንደሚገቡ እና ግድያም እንደሚፈፀም የወረዳው ፖሊስ አዛዥ (ረዳት ኢንስፔክተር አህመድ መሐመድ በ24/5/99) ከምርመራ ማጎደሮቻቸው በመነሳት ገልጸውልኛል።

ረዳት ኢንስፔክተር አህመድ መሐመድ እና ሌሎቹ የመረጃ አቀባዮቼም በጋራ የጠቀሱት ሌላው የግጭት ምክንያት ደግሞ ስካር ወይም ሞቅታ ነው። ሁሉም እንዳሰመሩበት "ካቲካላ" ወይም አረቄ ቤቶች በየገጠሩም ስላሉ በየድግሱም ላይ ይሸው መጠጥ ስላለ "በነገር ታህለኛለህ ወይ? እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ፉክክር፣ በአለባልታውም፣

በሽሙጠም፣ በስላቁም፣ በጥርስ፣ በአገጭ ምልክት ተነጋገርክብኝ፣ አፍንጫህን ሰቀልክብኝ፣ ወዘተ" ግጭት ይከሰታል። ይህም ግጭት በልዩ ልዩ አካላዊ፣ ምልክታዊ እና አንደበታዊ ቋንቋ አጠቃቀም ምክንያት ማለትም በዓይን አገላለጥ፣ አተያይ፣ (መገርመም፣ መግረፍ፣ ማጉረጥረጥ፣ የጉሪጥ ወይም የሽወርኔ ማየት)፣ በአፍንጫ መንፋት፣ መስቀል፣ አንገት ማጣመም፣ ማዋቃት፣ ማዙር፣ ጀርባ መስጠት፣ በአረማመድ ወይም አካሄድ፣ (አታሜ መምታት፣ ማደሽደሽ፣ መመናጨር)፣ "የከብት እግር" ጋልቦ አስተላለፍ (ደንጋላሳ መምታት፣ አቧራ ማስነሳት)፣ በንግግር (አሽሙር፣ ሽሙጥ፣ ስላቅ፣ አግቦ፣ ጉንተላ)፣ በአለባልታ፣ (አልሺ-ባልሺ) ምክንያት ሊቀሰቀስ እና ግድያ ሊከተል እንደሚችል ይጠቁመናል።

በተለይ (ቁስ ማሞ ፀደቀ በ6/5/99) እንደነገሩኝም "አንድ መለኪያ አረቂዬን ደፍተሃል" በሚል ሳይቀር የሰው ነፍስ ጠፍቷል። ከዚህ በተጨማሪም ልብሱ ተቆረጠ፣ ውድማዬ፣ በረቴ፣ ግቢዬ፣ "መድኃኒት ተረጨበት"፣ ምርቴ፣ ሀብቴ፣ (ንብረቴ)፣ ተሰለበ በሚል ጥርጣሬ እንዲሁም በሥራ ወይም በሙያ ልዩነት (ጠይብ፣ ቀጥቃጭ፣ ባለእጅ፣ ፋቂ፣ ቡዳ፣ ወዘተ) ብሎ በመፈረጅ፣ በማንቋሸሽ፣ "አጥንት የሚነካ" ስድብ በመሳደብ፣ ማለትም የሰውን ትውልድ ሐረግ የሚነካ ቃል በመሰንዘር፣ ማህበራዊ ደረጃን በመንካት እና በማዋረድ፣ በዋለ ባደረ ቂም ወዘተ ሳቢያ መቀያየም እና መጋጨት ብሎም መግደል መገዳደል ይከሰታል።

የላሎ-ማማ ሰው የሚጋጨው ነፍስ የሚጠፋፋው በእነዚህ ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች ብቻም አይደለም። ብዙዎቹ የመረጃ ተባባሪዎቼ በተለያየ አገላለፅ ነገር ግን ተመሳሳይ ይዘት ባለው ሁኔታ እንዳወሱልኝ በሰው ውኃ መቅኛ፣ በከብት ውኃ ማጠጫ፣ በመስኖ ውኃ ሽሚያ፣ በከብት ማሰማሪያ ማሳውም "በዓሣ ቁርር" ማለትም የይዞታ ማስከበሪያ ምልክት አለማክበር እና ማስገር /በተለይ በጀማ ወንዝ አካባቢ/፣ በአውድማውም፣ በከብት እበት መጠፍጠፊያውም መጣበብ እና መሻማት በከብት አፍም፣ ሰብሌን፣ ሳሬን አስበላህ፣ በሚል በዶሮውም (ስጤን ጫረ፣ በላ በሚል) በልጆች እና በሴቶች አለመግባባትም እንዲሁም በእጅ አመል ምክንያት ማለትም በባልትና (እንጀራ፣ ሹሮ፣ በርበሬ፣ ቅመም፣ ወተት፣ ቅቤ፣ ዱቄት፣ ጥራጥሬ) ሥርቆት ጥርጣሬ ወይም መሰረቅ፣ እንዲሁም በንብረት ስርቆት፣ ማቃጠል፣ እምነት ማጉደል ግጭት ይቀሰቀሳል።

ከተጠቀሱት በተጨማሪም እከሌ ላሜን፣ በሬዬን፣ ልጄን፣ ባሌን ወይም ሚስቴን "በዓይነ-ወግ ነብዙብኛል"፣ በሚል ጥርጣሬ ሁሉ መቀያየም እና መጋጨት እንዳለ እና እንደሚኖር የመረጃ ተባባሪዎቼ ሁሉ አውግተውኛል።

4.2. ቅድመ ግድያ

ግለሰቦች በልዩ ልዩ ምክንያቶች ለግጭት ይዳረጋሉ። ፀብ ውስጥ ይገባሉ። እነዚህን በግለሰቦች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችም የተለያዩ ሰላማዊ ዘዴዎች ተጠቅሞ ለመፍታት ይሞክራል። ይሁን እንጂ ሁሉንም ዓይነት ግጭቶች የሰው ሕይወት እና ንብረት መጥፋትን ሳያስከትሉ ለመቅጨት እንዳልተቻለ እና እንደማይቻልም የነባራዊው ዓለም እውነታ ያሳየናል። ግጭቶች እየተካረሩ ግድያም እየተከተለ ነውና።

ግጭት መኖሩ ሳይታወቅ እና ሳይታይ ባልታሰበ እና በድንገተኛ አጋጣሚ ሁሉ ግድያ ይከሰታል። ነገር ግን ግጭት መኖሩ እየታወቀ በሰላም ለመፍታትም እየተሞከረም ሳለ ግድያ ያጋጥማል። ይህ ዓይነቱ ሁኔታም ላሉ-ማማ ምድር ውስጥ ይስተዋላል። ከዚህ በመነሳትም ምናልባት በግለሰቦች መካከል ግጭት መኖሩ በሚስተዋልበት ሁኔታ ግድያ ለመፈፀም ያለመ ሰው የሚያሳያቸው አንዳንድ ቅድመ-ግድያ ምልክቶች ስለመኖር አለመኖራቸው የመረጃ ተባባሪዎቼን ጠይቄያቸዋለሁ።

የጭማ ገረገራው (ደንገዜ) የመረጃ ተባባሪዬ አቶ ደጀጠና መንግሥቱ በ6/5/99 እንደሚሉት በተለይ በቆላማው አካባቢያቸው ነገሬ ብሎ ላስተዋለ እና ላጤነ ሰው በልቡ ሰው ለመግደል የቋጠረ እና የከጀለ ማለትም ያሰበ ሰው የሚያሳያቸው አንዳንድ ምልክቶች መኖራቸውን መረዳት ይቻለዋል። እሣቸው እንዳስተዋሉት አንዳንድ ሰዎች ጠላታቸውን ለመግደል ሲያስቡ፡-

> *"በወንዝ፣ በበረሃ፣ በጫካ /በዱር/ ሲያልፉ፣ሲያገድሙ ወይም በተሰማሩበት ሥፍራ ሆነው መሸለል ያዘወትራሉ። ክራር እና ማሲንቆ መምታት የሚችሉ ከሆነ ደግሞ ማታ ማታ የቁረጥልኝ ሆዴ የአባት አገር ስንብት ዜማ ያንጐራጉራሉ።"* ይላሉ

ከግጥሙ የሚያስታውሱትን ንገሩኝ ብያቸውም፡-

> *"እንዲህ ጨሸ ጨሸ የነደድኩ እንደሆን፣*
> *የአመዱ ማፍሰሻ ሥፍራው ወዴት ይሆን።*
> *ኧረ አገሬ ማማ ኧረ አገሬ ላሎ፣*
> *ጥቃት ይከብዳል ወይ እንደ ወንዝ ገሎ።*
> *ከቶስ ይኖራል ወይ እንዲህ ተጣጥሎ።*
> *ኧረ አገሬ ማማ ኧረ አገሬ ላሎ ወንዜ ሆይ ደንገዜ፣*
> *ማን ያስገድደኛል እምቢ ባልኩ ጊዜ።*
> *በሮቼን ልብላቸው ላሞቼ ይሸጡ፣*
> *ባገር መኖር የለም ከተጐናነጡ።*
> *..... ዓመት የደለበው በሬ፣*
> *ቀንበሩ ተበሳ ሊጠመድ ነው ዛሬ"* ወዘተ

የሚሉ እንዳሉ አጫውተኛል። እሣቸው እንዳወጉኝ አንዳንዶች ደግሞ ድንገት ተነስተው የእርሻ በሬያቸውን፤ ጥገት ላማቸውን "የጭን" በቅሎአቸውን የተሞከተ በግ እና ፍየላቸውን

በአዘቦት ቀን አርደው ይበላሉ። እናም ይህን ሁሉ የሚያዩ ሰዎች" እከሌ ሊነቀል ነው፣ እዬ መካሪ ማጣት " እያሉ መነጋገሪያ ያደርጓቸዋል። ስለሆነም እነዚህ ሁኔታዎች የቅድመ-ግድያ ምልክቶች ሆነው ይቆጠራሉ ይላሉ።

በቆላ አካባቢ የሚታየው ከላይ የተገለጸው ዓይነት የግድያ ቅድመ-ምልክት በወይና ደጋ እና በደጋስ ይታያል ወይ? ያልኳቸው የወገሬው አቶ ቀጥይበሉ አሳምነው በ17/5/99 የዳሳው አቶ ገብረወልድ ገብረፃድቅ በ18/5/99 የአንገዋው አቶ እንግዳ አልታዬ በ13/5/99 እና የወምሶው አቶ ሺፈራው ደምሴ የመንግሥት ጠረተኛ እና አርሶ አደር በ9/5/99 ደግሞ ዘወትርም ባይሆን አልፎ አልፎ አንዳንድ ነባር ቂም ያላቸው ሰዎች ጠላታቸውን ለመበቀል ሲያልሙ መሸለል፣ ማስሸለል፣ መፎከር፣ ማስፎከር እና ጓዝ ማለትም ንብረት ማቃለል ማለትም ምርት እና ከብትን ወደ ገበያ እያወጡ ማድፋፋት /ባልረባ ዋጋ መቸብቸብ/ በአጠቃላይም ኑሮን የማናናቅ አዝማሚያ ሊያሳዩ እንደሚችሉ ያወሳሉ። ሆኖም ግን እንደነዚህ ዓይነቶቹን ምልክቶች ለሚያሳዩ ሰዎች ብዙውን ጊዜ መካር ዘመድ፣ ወዳጅ አይታጣም። በመሆኑም የቅድመ-ግድያ ምልክቶቹ ቢታዩም ሁልጊዜ ግድያን ላያስከትሉ ይችላሉ ይላሉ።

እነ አቶ ቀጥይበሉ እንደሚሉት ይልቁንም ብዙውን ጊዜ ግድያ የሚፈፀመው ምንም ዓይነት ቅድመ-ግድያ ሁኔታ ወይም ምልክት ሳይታይ ነው። ምክንያቱም ቅድመ ግድያ ምልክት መስጠት የልብ አለመቁረጥ፣ የተው ባይ ገላጋይ፣ ጠንክሮ እንዲገባ መፈለግ፣ ጠላትም እንዲሰጋ እና ለግልግል እንዲምበረክክ ማድረጊያ ዘዴ ሆኖ ሊያገለግል ስለሚችል ነው ይላሉ። በተለይ አቶ እንግዳ አልታዬ እንደሚሉትም "እገድላለሁ ያለ አይገድልም። እንዲያውም ብዙ ጊዜ ይገደላል። ልቡ የቆረጠ ሰው መሄዴ ነው በየት ነው መንገዱ አይልም። ገድሎ ውልቅ ይላል።"

4.3. ድህረ ግድያ

በዕለት ድንገተኛ ፀብም ይሁን በቂም በቀል ምክንያት በተፈጠረ ግጭት የሰው ሕይወት ከጠፋ ብዙውን ጊዜ የሟች ወገኖች ደማቸውን ለመመለስ ይሯሯጣሉ። ስለዚህም ገዳይ እራሱ እየሸሸ እና እየተሸሸገ (እየተደበቀ) ወዲያወም የቅርብ ቤተሰቦቹን ሁሉ እንዲሸሹ ማድረግ እንዳለበት ይህም የተለመደ እንደሆነ የመረጃ ተባባሪዎቹ ገልፀውልኛል።

በተለይም አቶ ሽዋይርጋ አስፋው በ11/5/99 እንዳጫወቱኝ "ገዳይ በእጁ የሰው ነፍስ እንዳለፈበት ወዲያውኑ ለቅርብ ዘመዶቹ እና ቤተሰቦቹ አሳውቆ የነበሩበትን አካባቢ ለቀው ገለል እንዲሉ ማድረግ አለበት አለዚያ የሚከተለው መከራ የበዛ ይሆናል" ይላሉ።

ገዳይ እራሱ ከሸሸ በቂ አይሆንም ወይ? ቤተሰቦቹ እና የቅርብ ዘመዶቹ ለምን ይሸሻሉ? ያልኳቸው አቶ ሸዋይርጋ አስፋው "እረ-ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈቅ ቅዱስ! ይሄማ ጉድ ነው። ለጆሮ የሚቀፍ። ሰው የገደለ ሰው የገደለውን ሰው ወገን ካልናቀ በስተቀር ቶሎ ብሎ ቤተሰቡን ማንቃት እና እንዲሸሹ ማድረግ አለበት አለዚያማ ጉድ ይፈላል። " በማለት በአንድ ወቅት የሆነውን አጋጣሚ አስታውሰው አጫውተውኛል።

ጊዜው ደርግ እንደወደቀ አካባቢ ነው። እናም አንድ ወጣት ቂም የቋጠረበት ጠላቱ የሄደበትን ገበያ ሰልሎ ይደፍጣል። ሰውዬው ከገበያ ሲመለስ ለመግደልም ይጠብቃል። እንደተጠበቀውም የተደቀነለትን ወጥመድ ያላወቀው ገበያተኛ ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ ወደ ቤቱ እየገሰገሰ ሳለ ደፋጭ በጥይት ነጥሎ ይጥለዋል። በሁኔታው የተደናገጡት የሟች ጓደኞችም መሬት እየያዙ ግራ እና ቀኝ እሩምታ ይተኩሱለ። በዚያም ወቅት ገዳይ የታዩ ይመስለውና የደፈጠበትን ቦታ ለቆ ሲሸሽ የሟች ጓደኞች ማንነቱን ይለዩታል። ከዚያም እሬሳቸውን አንስተው ከቤቱ እንደደረሱ የሟችን ታናሽ ወንድም አስከትለው ወደ ገዳይ ቤተሰቦች ቤት ይከንፋሉ። እንደደረሱም የገዳይ አባት ከዋሉበት ሲገቡ፣ የገዳይ እናት ደግሞ "የምን ተኩስ ነው የሰማሁት" እያሉ በሰፈር የነበሩ ሰዎችን ሰያጠያይቁ አግኝተው በጥይት ይረፈርፏቸዋል።

አቶ ሸዋይርጋ እንደነገሩኝም በድንገቱ አምስት ቤተሰብ፤ በርካታ እንሰሳት እና በጐተራ የነበረ እህል ሁሉ ጠፍቷል። ይህም አደጋ ከገዳይ ጥንቃቄ ጉድለት የመጣ እና በስህተት ላይ ስህተት የተደረበበት እንደነበር ያስታውሳሉ። እሳቸው እንደሚሉት በእጁ የሰው ነፍስ ያለፈበት ሰው እራሱን ብቻ ሣይሆን ለደም መወጫነት ሊዳረጉ የሚችሉ ቤተሰቦቹን እና ዘመዶቹን ማንቃት እና ማስገለል ወይም ገለል እንዲሉ ማድረግ አለበት። ይህም ከጥንት የነበረ አሁንም ያለ ልማድ፣ ደንብ ስለሆነ ገዳይ ይህን ከማድረግ መቦዘን እንደሌለበት ይናገራሉ። ሌሎቹም ይህንኑ ያሰምሩበታል።

4.4. የላሎ-ማማ ምድር ነዋሪዎች ግጭት አፈታት

ቀደም ሲል በቀረበው የላሎ-ማማ የግጭት መንስኤ ሥር እንደታየው በርካታ ሰበቦች ለግጭት ይዳርጋሉ። የግጭት መነሻዎቹ እንደመብዛታቸው ለደም መቃባት የማያበቃ የግጭት ዓይነት እንዳለመኖሩም ግን ሕዝቡ አልተላለቀም፣ አልተፋጀም። ስለሆነም ግጭቶች እንደምን እየተፈቱ ሕይወት፣ ሰላም፣ መረጋጋት ቀጠለ ማለኘቱ አይቀርም። እኔም ይህን ሁኔታ ለማወቅ ሞክሬያለሁ። በመሆኑም የላሎ-ማማ ሕዝብ ግጭቶቹን ለመፍታት የሚጠቀምባቸውን ተቋማት እና ሥልቶች እንዲያብራሩልኝ አውራ የመረጃ ተባባሪዎቼን እንደዚሁም ሌሎችን ጠይቂያለሁ፣ የተወሰነ ምልከታም አድርጌያለሁ። በአባሪ አንድ ላይ

በቁልፍ ወይም አውራ የመረጃ ተባባሪነት የተዘረዘሩት በሙሉ እንዲሁም ሌሎች ለዚህ የሰጠኝ ምላሽ አገላለፁ ከመለያየቱ በስተቀር ይዘቱ ወጥ ነው።

እንደዋነኛ የመረጃ ተባባሪዎቼ አገላለፅ የላሎ-ማማ ወረዳ ሕዝብ የሚያጋጥመውን ቀላል እና ከባድ ግጭቶች የሚፈታው በተለያዬ መንገድ ነው። ግጭቶች በቤተሰብ አባወራ፣ በአባት እና እናት፣ በአጐት፣ በአክስት፣ በንሰሐ-አባት፣ በቡና ማኅበርተኞች፣ (ለሌቶች)፣ በጠንቋይ፣ በሰንበቴ (ፅዋ) ማኅበርተኞች፣ በሰፈር አካባቢ ሽማግሌዎች ወይም እድርተኞች በአገር ሽማግሌዎች በአካባቢ ፍርድ ሸንጐ፣ በፖሊስ እና በመደበኛ ፍርድ ቤት፣ (መግት) አማካኝነት ይፈታሉ።

የአገር ሽማግሌዎቹ እንደሚሉት በቤተሰብ አባወራ አማካኝነት መፍትሄ የሚያገኙት ጥቃቅን የቤተሰብ ፀቦች ወይም ግጭቶች ናቸው። ለምሳሌም በዚህ ሊፈቱ የሚችሉት አንዱ የቤተሰብ አባል የሌላውን ጉልማ /የግል ሀብት ንብረት/ ማለትም በግ፣ ፍየል፣ በሬ፣ ላም፣ ሳር፣ ገለባ፣ ነፈገ፣ ከለከለ፣ መትቶ ሰበረ፣ ዓይን አጠፋ፣ ወዘተ ምክንያት የሚፈጠሩ መቀያየሞች መዘላለፎች መደባደቦች ዓይነቶቹ ናቸው።

በእናት እና አባት አማካኝነት የሚፈቱትም እንደላይኛው ሁሉ ጥቃቅን ግጭቶች ናቸው። የመረጃ ተባባሪዎቼ በምሳሌ አስደግፈው እንደገለጹልኝም ልጆች እርስ በርሳቸው መግባባት ሲሳናቸው ወላጆች በልጆቻቸው መካከል መኳረፍ፣ መዘላለፍ፣ መሰዳደብ ዓይነት ነገር ሲያዩ ጣልቃ በመግባት የፀቡን ምክንያት ጠይቀው ያግባባሉ፣ ያስማማሉ።

እንደ አገር ሽማግሌዎቹ ገለጻ አጐት ወይም አክስት ወይም ሁለቱም በጋራ ለመፍታት የሚሞክሯቸው ግጭቶችም አሉ። በነርሱም ይቃለሉ ዘንድ የሚሞክሩት መለስተኛ ግጭቶች እንደ ልጆች ከወላጆቻቸው ጋር አለመግባባት፣ ወላጆቻቸው የሞቱባቸው ልጆች በውርስ ንብረት ክፍፍል ሳቢያ የሚፈጥሯቸው ቅራኔዎች ወዘተ ዓይነቶች ናቸው።

በንሰሐ-አባት ብቻም ሊፈቱ የሚችሉ ወይም የሚሞክሩ አለመግባባቶችም እንዳሉ ከመረጃ አቀባዮቼ ገለጻ ተረድቻለሁ። የንሰሐ-አባቶች ብቻቸውን ጣልቃ የሚገቡባቸው የግጭት ዓይነቶችም "የባልና ሚስት አልጋ መለያየት፣ በትዳር ላይ ዲቃላ መውለድ፣ የተደበቀ ዲቃላ ተቀባይነት እንዲያገኝ የማድረግ ጥያቄ ወዘተ" ናቸው (አባ ዘውዴ ደምድም በ13/5/99፣ ቄስ ማሞ ጸደቀ በ7/5/99)።

ይሁንና የንሰሐ አባቶች እነዚህን ዓይነቶቹን አለመግባባቶች ብቻቸውን መፍታት ሲሳናቸው ለሽማግሌም የሚተላለፉበት ሁኔታ እንዳለ እንዲሁም የንሰሐ-አባቶች ሌሎች ግጭቶችንም ለመሸምገል በሚደረግ ጥረት ውስጥ እንደሚገቡ የአገር ሽማግሌዎቹ ይጠቁማሉ።

የአገር ሽማግሌዎቹን በቡና ማኅበርተኞች ሊፈቱ የሚችሉት ግጭቶችስ ምን ምን ዓይነቶቹ ናቸው? ብያቸውም ነበር። ለዚህ ጥያቄዬ አንዳንዶቹ የመለሱልኝ "ይሄ ትርኪ-ምርኪው ነዋ" በማለት ነው። ትርኪ-ምርኪ የተባለውም አልሺ-ባልሺ ወይም ሐሜት፣ ሽሙጥ፣ ለበጣ፣ የጐሪጥ ማየት፣ አፍንጫ መንፋት፣ አገጭ መስቀል፣ አታሚ መምታት፣ ማለትም ሰላምታ መንፈግ፣ እና ተራምዶ ማለፍ ወዘተ ዓይነቱ ነገር የሚፈጠር ቅራኔ ነው (አቶ ሽዋይርጋ አስፋው በ11/5/99 አቶ ቀጥይበሉ አሳምነው በ17/5/99)።

አንዳንዶቹ ደግሞ በቡና ማኅበርተኞች የሚፈታው ግጭት ብዙም "ውኃ የማያነሳው" ማለትም ብዙም ለሽንገጮ የማይበቃው ነው ይላሉ (አቶ ገብረወልድ ገብረጻድቅ፣ አቶ መንግሥቱ አማረ፣ መቶ አለቃ ሸቤ ጣልባቸው፣ አቶ ደምሴ ወልደጻድቅ የመንግሥት ጠረተኛ በ18/5/99)።

እንደመረጃ ተባባሪዎቼ ገለፃ ለ"አዋቂ" ማለትም ለጠንቋይ የሚቀርቡት ግጭቶች ደግሞ "የሴቶች የባልትና ውጤቶች ስርቆቶች" ማለትም የስጥ መታፈስ ወይም መሳሳት የሹሮ፣ የበርበሬ፣ የወተት፣ የቅቤ፣ የጥራጥሬ ሥርቆት፣ እንዲሁም በ"መተት" ወይም መድኃኒት ተደርገውብኛል ወይም ተጥሎብኛል። ለምሳሌም በልጆች ጤና ማጣት፣ በእንስሳት ህመም፣ በእላቢ መድረቅ፣ በ"ሰለባ" ወይም ንብረት በ"መፀ-ሰውር" ማለትም በጥበብ በዘዴ ተወስዷል በሚል፤ በልብስ መጥፋት፣ በአዲስ ልብስ መቦጨቅ፣ ወዘተ ምክንያት በጐረቤታሞች መካከል መጠራጠር ሲኖር ነው። በአብዛኛውም ወደጠንቋይ የሚሄዱት ሴቶች ናቸው። ይሁንና በአገር ሽማግሌዎቹ እምነት እነዚህ "አዋቂ" ወይም ጠንቋይ የሚባሉት ግን ጥርጣሬ እና ግጭቱን ከማርገብ ይልቅ እጅጉን ያሰፋሉ። ወደ ጠንቋይ የሚሄዱትም ሰዎች የሽንገጮም ሆነ የቤተክርስቲያን አደባባይን የማያዘወትሩ እና የማያውቁ "መንፈሰ ልሎች" ተደርገው ይቆጠራሉ።

በሰንበቴ (ዕዋ) ማኅበርተኞች ሊፈቱ የሚችሉት ደግሞ በክብት አፍ፣ (ሣር፣ ሰብል ማስበላት) በአውድማ፣ በክብት እበት መጠፍጠፊያ፣ በመንገድ ጠበበኝ፣ በክብት "ስረጌ" ማለትም ማሰማሪያ፣ በውኃ ማጠጫ እና መቅጃ ተሸምቶ፣ በልጆች ድብድብ፣ በሴቶች መዘላለፍ፣ መዛዛት፣ በሳር፣ ገለባ፣ ነዶ፣ እንሰሳት ስርቆት፣ ወዘተ ምክንያት የሚፈጠሩ አለመግባባቶች መሆናቸውን የአገር ሽማግሌዎቹም ሌሎቹም ያወሳሉ፣ ያፀድቃሉም።

በሰፈር (አካባቢ) ሽማግሌዎች ሽምግልናም የሚቃለሉ ያለመግባባት ችግሮች አሉ። በሰፈር ሽማግሌዎች ሊፈቱ ከሚሞክሩት እና ከሚችሉት መካከል የባልና ሚስት አለመግባባት፣ የሰው ውሽማ፣ ቅምጥ፣ ማማገጥ(መስረቅ)፣ ድብድብ እንደዚሁም ከላይ የሰንበቴ ማኅበርተኞችም ሊፈቷቸው እንደሚችሉ የተጠቀሱት አለመግባባቶች ናቸው።

ይህም የሚሆነው እንደ መረጃ ተባባሪዎቹ ገለጻ ጉረቤታሞች የሰንበቱ ማኅበር አባል ላይሆኑ በዕድር ሽማግሌዎችም ሽምግልና ላይረግቡ ወይም ላይመለሱ ማለት ላይስማሙ ይችላሉና ነው።

ከላይ በተገለጹት የግጭት ማርገቢያ፣ መቆጣጠሪያ እና እርቀ ሰላም ማውረጃ ዘዴዎች ሊፈቱ ያልቻሉ ቅያሜዎች አለመግባባቶች ወይም ቅራኔዎች ከአንዱ ወደሌላው ወይም ወደሚቀጥሉት ተቋማት ማለትም የአካባቢ ፍርድ ሸንጎ፣ የአገር ሽማግሌ ሽምግልና፣ ፖሊስ እና መደበኛ ፍርድ ቤት፣ ሊተላለፉ ወይም ሊሸጋገሩ እና እልባት ሊያገኙ እንደሚችሉ የመረጃ ተባባሪዎቹ ያረጋግጣሉ። የመረጃ ተባባሪዎቹ ከዚሁ ጋር አያይዘው እንዳወሱልኝም ብዙውን ጊዜ ለኋለኞቹ ተቋማት ማለትም ለአገር ሽማግሌ ፣ ለፖሊስ እና ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርቡት ግጭቶች እንደ ከፍተኛ የውርስ (ንብረት) ክፍፍል፣ ጭቅጭቅ የንብረት እና የቤት ቃጠሎ ከባድ ድብደባ እና አካል ማጉደል፣ የሰው ሚስት መጥለፍ፣ መቀማት፣ ከፍተኛ የባልና ሚስት ቅራኔ፣ የአደራ ገንዘብ፣ መሣሪያ፣ ንብረት መብላት፣ ማጥፋት፣ ማለትም እምነት ማጉደል፣ አጥንት የሚነካ ወይም "የሚያጉድፍ" ስድብ፣ እንዲሁም የ"እጅ እላፊ" ማለትም የነፍስ ግድያ የመሳሰሉት ናቸው።

ይሁን እንጂ አውራ የመረጃ ተባባሪዎቹ በተመሳሳይ ሁኔታ እንደገለጹት በልዩ ልዩ ምክንያት የተፈፀመ የነፍስ ግድያ የሚያስከትለውን መበቃቀልን የሚከላው ወይም የሚገታው ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት ነው። እነርሱ እንደሚሉት በፖሊስ እና መደበኛ ፍርድ ቤት የሚደረገው የነፍሰ-ገዳይን ተከታትሎ በዘመናዊ የወንጀል ህግ መሠረት ቅጣት መጣል ወይም ማሳለፍ ህግ እና ሥነ-ሥርዓትን ያስከብራል እንጂ የደም ምለሳ ብቀላን አያስቀረውም። ሽማግሌ የሚያደርቀውን ደምም ዳኛ አያደርቀውም። ዳኝነት የየዕለቱን ሽምግልና የዘለቄታውን ማለትም የዘላለሙን የማየት ችሎታም አላቸው ብሎ ሕዝቡ እንደሚያምን በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ላይ ሲናገር ይሰማል። በማስከተል የአገር ሽማግሌዎችን ማንነት ለማሳየት እሞክራለሁ።

4.4.1. የአገር ሽማግሌነት እና ሽምግልና

ቀደም ሲል በቀረበው ገለጻ የተለያዩ ግጭቶች ሊፈቱ የሚችሉባቸውን ተቋማት ለማመላከት ተሞክሯል። በተለይም ከባድ ግጭቶች ከሚፈቱባቸው ተቋማት መካከል አንዱ የአገር ሽማግሌዎች ሽምግልና መሆኑም ተጠቁሟል። ይሁን እንጂ የአገር ሽማግሌዎች ምን ዓይነት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ያላቸው ሰዎች ናቸው ማለኘቱ አይቀርም። ስለሆነም የአገር ሽማግሌዎች የአገር ሽማግሌ ለመባል የሚችሉበትን ወይም የሚበቁበትን መስፈርት ማመላከት ይገባል።

የአገር ሽማሌዎች ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው? የሚለውን ጥያቄ ለራሳቸው ለአገር ሽማግሌዎቹም ለሌሎች ሰዎችም ስንዝሬ ያገኘሁትን ምላሽ /ገለጻ/ እንደሚከተለው አጠቃልየዋለሁ::

የአገር ሽማግሌዎች የሚባሉት በአመዛኙ ዕድሜያቸው ከ50 ዓመት ይዘላል:: ስማቸው በሚኖሩበት ቀበሌ ብቻ ሣይሆን በአጐራባች ቀበሌዎች እንዲሁም በወረዳ ደረጃ እና ከዚያም ዘልቆ ይጠራል:: በአኗኗራቸው ባለፀጋ ወይም "ሀብታም" ይሰኛሉ:: የግብርና ሥራቸውንም በልጆቻቸው ወይም በቅጥር "ገበሬ" ወይም በዘመድ አዝማድ እና በሚያውቃቸው ሁሉ ያሰራሉ:: ስለከበሬታቸውም ሰዎች ምን እንርዳ ብለው በራሳቸው ፈቃድ ያግዟቸዋል:: በትዳራቸው፤ በጠባያቸው፤ በግብራቸው (ሥራቸው) በአነጋገር ሥልት አዋቂነታቸው፤ በማግባባት ችሎታቸው ይደነቃሉ:: እንዲሁም የአባት አገር ዕድር/ይላላል/ ማለትም አስተዳደር ወይም "አዳ" ማለትም ልማድ፤ ወግ፤ የአባት ወንዝ ወይም የአባት አደር ማለትም ደንብ ህግ ጠንቀቅው የሚያውቁ፤ እና በሽምግልና ተቀምጠው ነገር "የማይሳድርባቸው" ማለትም የማይፋለስባቸው ናቸው:: ሕዝቡም "ሽማግሌ አዬ እግዜር አዬ ነው" ብሎ ቃላቸውን እንደፈጣሪ ቃል ያከብርላቸዋል:: በተለይም ደመኞችን በማስታረቅ ተሞክሯቸው እውቅና እና ዝና ያላቸው "ሰማይ ተቀደደ ቢባል እንኳን ታዲያ ሰፊ ሽማግሌ መቼ ገደደ?" ለምድር ለሰማይ የከበዱ ቃላቸው የማይሰተሃቀርባቸው (የማይዛነፍ ለማለት) እነ እከሌ አሉ አይደለም ወይ? እያለ ሕዝቡ የሚመሰክርላቸው ወንዶች ናቸው:: እራሳቸውን የአገር ሽማግሌዎቹንም ስለ ችሎታቸው እና አኗኗራቸው እንዲያወጉኝ አንስቼባቸው "ምን ችሎታ አለን እንዲያው ሕዝቡ ፈርዶበት እየመጣ ይወድቅብናል እንጂ:: ምንስ ኑሮ አለ ብለህ ነው" እያሉ እራሳቸውን ዝቅ እያደረጉ ነው የነገሩኝ (አቶ ገብረወልድ ገ/ዓድቅ እና አቶ መንግሥቱ አማረ በ18/5/99)::

ይሁንና አንዳንዶቹ ልምዱን ከአባቶቻቸው እንዳገኙት ህዝቡም ያንኑ ተከትሎ "ቤተ-ጨዋ ቤተ-ሽማግሌ" እያለ አመኔታ እንደጣለባቸው፤ በዚህም የተነሳ "የሰው ቀዳዳ ሲሰፉ" ማለትም ሲሸመግሉ "የቤታቸውን እንጀራ እንኳ በወጉ እና በቅጡ አጣጥመው እንደማያውቁ" ሰውም "እከሌ እከሌ ቤቱን አያውቀውም" እያለ እንደሚገልፃቸው ተረድቻለሁ (ቄስ ማሞ ጸደቀ በ6/5/99፤ አቶ ሸዋይርጋ አስፋው በ11/5/99፤ አቶ ቀጥይበሉ አሳምነው በ17/5/99)::

አንዳንዶቹ ደግሞ በሕይወት ተሞክሯቸው በየትም አደባባይ ቆመው "ዝንጋቸው የማይሰበር" ማለትም የያዙትን ነገር ከዳር የሚያደርሱ ጥቃትን የማይወዱ "በፍትህ ከሄደች ሲናር በቅሎዬ ያለፍትህ የሄደች ጥርኝ ቆሎዬ ትከነክነኛለች" እንዲሉ ጠንክረው ለሐቅ ለፍትህ የቆሙ በመሆናቸው ሕዝቡ "እከሌ በነገሬ ይግባበት" እያለ ለሽምግልና

እንደሚያጫቸው እና እንደሚያስገባቸው ይናገራሉ(አቶ ሺፈራው ደምሴ በ9/5/99፤ አቶ መንግሥቱ አማረ፣ መቶ አለቃ ሽቤ ጣልባቸው በ18/5/99)።

በሽማግሌዎች እና በአገር ሽማግሌዎች መካከል ያለውን ልዩነት እና ደረጃም ለማወቅ ጠይቂያለሁ። ሽማግሌዎች የሚባሉትም እንደ አገር ሽማግሌዎቹ ሁሉ ዕድሜያቸው ከሃምሳ ይዘልቃል። ትዳር እና ቤተሰብ ያላቸው እንዲሁም "ደህና" ያድራሉ ማለት መካከለኛ ህይወት ይመራሉ የሚባሉ ምግባረ-መልካም የሚሰኙ ሰዎች ናቸው። ስለሆነም የሰፈርተኞቻቸውን አንዳንድ ችግሮችም ለመፍታት የምክር ሐሳብ ያመነጫሉ። ቀላል የባልና ሚስት እንዲሁም የጐረቤታሞች ቅራኔዎችንም ለመፍታት ይሽመግላሉ። የአገር ሽማግሌዎች የሚባሉት ግን፤ ለከባድ ግጭት አብራጅነት፣ አስማሚነት፣ አስታራቂነት፣ በተለያዩ ቀበሌዎች ነዋሪዎች የሚታጩ እና የሚሰየሙም መሆናቸውን ከተለያዩ አቅጣጫ ተረድቻለሁ።

እንደመረጃ ተባባሪዎቼ አገላለፅም በሽማግሌዎች እና በአገር ሽማግሌዎች መካከል ያለው ዋና ልዩነት የሽማግሌዎች በየሠፈሩ መገኘት እና የአገር ሽማግሌዎች ግን እንኳንስ በሰፈር በቀበሌ ደረጃም ብዙ ጊዜ የማይገኙ መሆኑ ነው (ቄስ ማሞ ጸደቀ በ6/5/99፤ አቶ ደጀጠና መንግሥቱ በ6/5/99፤ አቶ ሽዋይር ጋ አስፋው በ11/5/99፤ እና ሌሎችም)።

4.5. ቅድመ-እርቅ

4.5.1. የደም ግጭት እርቅ ጥያቄ አቀራረብ

ደመኞችን ለእርቅ ማብቃት የሚቻለው በቅድሚያ የሰመረ የእርቅ ጥያቄ አቀራረብ እና አቃራቢ ወይም አባባይ ሲኖር ነው። የመረጃ ተባባሪዎቼ እንደነገሩኝ የደም እርቅ ጥያቄ የሚደረገው እና የሚካሄደው በተለያዩ ሰዎች እና መንገዶች ነው። ይህም የሚመሰነው በተጋፊዎች ማኅበራዊ ደረጃ ማለትም እውቅና፤ ተደማጭነት፤ ከበሬታ፤ የወገን ብዛት እንዲሁም የሀብት ደረጃ እንደሚሆን ሁሉም የመረጃ ተባባሪዎቼ ገልጸውልኛል።

እንደመረጃ አቀባዮቼ እውቀት የደም እርቅ በገዳይ፤ በገዳይ ወገኖች በሚች ወይም በተጐጂ ወገኖች፤ በአገር ሽማግሌዎች፤ በኃይማኖት አባቶች፤ በተናጠል ወይም በተጠቀሱት ወገኖች ጥምረት ወይም ቅንጅት አባባይነት ወይም ቀስቃሽነት ሊደረግ ይችላል። የእነዚህ የግልግል እና የእርቅ ጥሪዎች አደራረግም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የየራሱ መነሻ ምክንያት አለው። ምክንያቱን ጠይቂያለሁ። ስለሆነም በዝርዝር አሳያለሁ።

ብዙ ጊዜ በገዳይ አማካኝነት የእርቅ ጥያቄ የሚቀርበው የሚች ወገን ኃይል አይሎ እና ደርጅቶ ሲገኝ፤ የገዳይም ወገኖች "ታስፈጀናለህ፤ ጥፋልን፤ ዓይንህን ላፈር፤ አትድረስብን" ብለው ሲገስፁት እና ጥላ ከለላ መከታ ላይሆኑት ሲቀሩ ነው። ይህ ዓይነት

ሁኔታ ሲከሰትም ገዳይ ራሱ ሌሊት በድብቅ እየተንቀሳቀሰ የአገር ሽማግሌዎችን ይማፀናል። ከተሳካለትም "አስምሩኝ ዘመዶቼን አትርፉልኝ በአገሩ አዳ (ልማድ እንደማለት ነው) መሠረት ይወሰንብኝ" በማለት ሽምግልና እንዲጀመርለት እና እንዲያዝለት ይጠይቃል። በዚህም ከተሳካለት ሽምግልናው ይቀጥላል (አባ ዘውዴ ደምድም በ13/5/99 አቶ ደጀጠና መንግሥቱ በ7/5/99)።

ገዳይ ከላይ የተጠቀሰው ዓይነት የእርቅ ጥሪ ተቀባይነት ካላገኘለት ደግሞ ወደ አንድ የታወቀ፣ የተከበረ፣ ገዳም ወይም ደብር ገብቶ በመደወል፦

"ውቃቢ ርቆኝ፣
ሰይጣን አሳስቶኝ፣
በጀ የሰው ህይወት አለፈብኝ፣
እነሆም ዛሬ እግሬ ቁጠማ፣
ዓይኔም ጨለማ፣
ሁሉ ግራ ስለሆነብኝ
ለአገር ሽማግሌ አብቁኝ"

በማለት የእግዚአታ ጥያቄ ያቀርባል። ይህን ከተናገረ በኋላም እጁን ለገዳሙ አለቃ ይሰጣል። ከዚያ በኋላ እርቁን የሚያስተናብሩት ወይም የሚያባብሉት የገዳሙ ቀሳውስት ወይም መነኮሳት ወይም ሁለቱም ይሆናሉ (አባ ዘውዴ ደምድም በ13/5/99፣ አቶ ደጀጠና መንግሥቱ በ7/5/99 አቶ ገብረሕይወት አሳምነው የመንግሥት ጡረተኛ በ9/5/99)።

የአገር ሽማግሌዎቹ እንደሚሉትም ገዳም ገብቶ የደወለ ነፍሰ ገዳይን የሚች ወገኖችም አይከታተሉትም። ሽምግልናውም እንደሌላው አያስቸግርም። ምክንያቱም ገዳይ በመግደሉ ሳይኩራራ ወደ ቤተ-እግዚአብሄር እና "ሥልጣነ-ክህነት ወዳላቸው ወይም ይህ ዓለም ወደበቃቸው መነኮሳት" በመሄዱ ድርድሩ አያስቸግርም። ይሸማገላሉ። ዋናው ነገር የሚች ወገኖች ሊያዩት ስለማይፈልጉ ብቻ አገሩን ለቆ ተሰዶ መኖር ይችላል። የሚች ወገኖች "ዓይናችን እንዳያይብን ገለል ይበልልን ዓይን ደም ይጠላልና ነው የሚሉት"። ገደለ ተነቀለ ነውና።

የቤተክርስቲያን ደወልም ልዩ ልዩ ተምሳሌታዊነት እንዳለው ከነዚህም መካከል ማንቃት፣ ማካፈል እና ማሳረግ የሚሉትን መንፈሳዊ ሐሳቦች እንደሚይዝ ይነገራል። በሌላ በኩል ፍትሐ-ነገሥት (1958:548) ላይም ስለዚህ የመደወል ጉዳይ የተጻፈ አለ። ይኸውም አንድ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ እገድለዋለሁ ያላለውን ሰው መትቶ ከገደለ ስለፀፀቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ ገብቶ መደወል እና መማፀን እንዳለበት ይህንንም ከፈፀመ በኋላ ጥቃት ሊደርስበት እንደማይገባ የሚያወሳ ነው። ይህም አባባል አስቦ እና አቅዶ የገደለውን የሚመለከት አይደለም። ምናልባትም ይህ ዛሬ ላሉ-ማማ ውስጥ በእርቅ መጠየቂያነት አገልግሎት እየሰጠ ያለው በቤተክርስቲያን ውስጥ እየገቡ የመደወል እና እርቅ የመጠየቅ ባህል የመጣው ከፍትሐ-ነገሥቱ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል።

ሁለተኛው የእርቅ ጥሪ የሚቀርበው በገዳይ ወገኖች ነው። ይህ ዓይነቱ ጥሪ የሚደረገው የገዳይ ወገኖች ወገናቸው ሟችን የገደለው በበቂ ምክንያት እና ጥቃት ወይም በዕለት ድንገተኛ ያልታሰበ ግጭት መሆኑን አምነው ሲቀበሉ እና "አንድዬ ሆኗል የፈሰሰ ውኃ አይታፈስም እንግዲህ ለሀገር ሽማግሌ ይጭነቀው አንተ ራስህን መጠበቅ ነው።" ብለው ሲያምኑ ነው። ስለሆነም የሟች አርባ እስከሚያልፍ ገዳይን ሸሽገው እንዲሁም የገዳይ እና የሟች መኖሪያ ቅርብ ከሆነ የገዳዩን ቤተሰብ አሸሽተው በውኃ መቅጃ፣ በክብት ውኃ ማጠጫ፣ በክብት ስምሪት ወይም ማዋያ፣ በደቦ፣ በዕድር፣ በሰርግ፣ በለቅሶ በገቢያም ጭምር ላለመገናኘት ራሳቸውን አቅበው እና ተጠንቅቀው ወደ ሀገር ሽማግሌ በመሄድ ይህም ካልተሳካ ወደ ቤተክርስቲያን አባቶች በማምራት የአስታርቁን ጥያቄ እና ተማፅኖ ያቀርባሉ።

ሦስተኛው የእርቅ ጥያቄ ወይም ጥሪ አቀራረብ በሟች ወይም በተጐጂ ወገኖች የሚደረግ ነው። የአገር ሽማግሌዎቹም ሌሎቹም እንዳጫወቱኝ ይህ ዓይነቱ የደም እርቅ ጥያቄ እና ማባባል የሚፈፀመውም በሁለት ዐበይት ምክንያቶች ነው።

አንደኛው ምክንያት ሟች በገዳይ ላይ የአካባቢ ሰው ያወቀው፣ የታወቀ ጥቃት፣ በደል "አስነዋሪ ተግባር" ማለትም ሚስት ማባለግ፣ ሀብት መቀማት፣ በአደባባይ ማዋረድ፣ ወዘተ ዓይነቱን ተግባር አድርሶበት ወይም ፈጽሞበት ከሆነ እና ገዳይ "ደሙ ፈልቶበት" ከገደለው እና በዚህም ሳይገታ ከግጭቱ ጋር ንክኪ ያላቸውን የሟች ወገኖች በተጨማሪ ያጠቃል ይገድላል ተብሎ ሲሰጋ ወይም ራሱ ገዳይም "እከሌንም እደግማለሁ" እያለ መልዕክት ሲልክ እራሱንም ሽፍታ አድርጐ ሲቆጥር ወገኑም አይሎ እና ልቆ ሲገኝ ነው።

ሁለተኛው ምክንያት የሟች ወገኖች ከገዳይ የተሻለ ማኅበራዊ ደረጃ /በሀብት በንብረት/ ኖሯቸው ሳለ ገዳይ እና የገዳይ ወገኖች በአንጻራዊ ሁኔታ ዝቅ ያሉ ወይም ያነሱ ሲሆኑ እንዲሁም ገዳይ በቀዳሚ ባህርይው ጦሰኛ፣ ነገረኛ፣ ብትንኩስ የሚባል ዓይነት ሆኖ ሳለ ሟች ከእንዲህ ዓይነቱ አቻው፣ እና እኩያው ካልሆነ "ጋጠወጥ ወይም ወመኔ" ሰው ጋር ግጭት ውስጥ ገብቶ ያመጣው "መዘዝ" ነው ብለው ሲያምኑ የሚያቀርቡት የእርቅ ጥያቄ ነው። መጀመሪያውንም "አተሬ አትጣላ ከመተሬ" ማለትም "ሀብታም ከመናጢ ድኃ አትጣላ ነውና" ይላሉ የአገር ሽማግሌዎቹ።

የአገር ሽማግሌዎቹ እንደሚገልፁት የሟች እና የገዳይ ወገኖች በቀጥታ "ባረጁ እና ባፈጁ" ሽማግሌ ዘመዶቻቸው አማካኝነት ራሳቸው አንዳቸው ለአንደኛቸው ወገን የእርቅ ጥያቄና እንገላገል ሐሳብ የሚያቀርቡበት አጋጣሚም አለ። ይህ በሟች ወይም በገዳይ ወገኖች በኩል በቀጥታ የሚደረገው የእንሽማገል ወይም እንስማማ ጥያቄ የሚደረገውም

የአካባቢው ሽማግሌዎች የሀገር ሽማግሌዎች እና የኃይማኖት አባቶች ለተፈጠረው ግጭት በጣም ያልተገበት እና አክብሮትም ያልሰጡት ሆኖ ሲገኝ ነው።

የአካባቢው ሽማግሌዎች፣ የአገር ሽማግሌዎች እና የኃይማኖት አባቶችም ለዚህ ለአራተኛው ዓይነት የእርቅ ጥሪ አቀራረብ አንዳንድ ጊዜ ትኩረት የማይሰጡበት ምክንያት ተጋጪዎች ወገኖች ብዙም በመልካም ሥራቸው የማይታወቁ በማኅበራዊ ደረጃቸውም ዝቅ ያሉ ሆነው ሲገኙ ነው (አቶ ሽዋይርጋ አስፋው በ12/5/99 ፣ አቶ ደጀጠና መንግሥቱ በ7/5/99)።

አምስተኛው የእርቅ ጥሪ የሚደረገው በአገር ሽማግሌዎች አማካኝነት ነው። ይህ ዓይነቱ የእርቅ ጥሪ የሚደረገው ገዳይ እና ሟች እንዲሁም ወገኖቻቸው በአካባቢያቸው በትውልድ፣ በግብርና፣ በንግድ፣ በክህነት ወዘተ የተከበሩ እና የአገር ስም የሚያስጠሩ የተመሰገኑ ሆነው ሲገኙ እና ያላቸውንም ማኅበራዊ ክበራታ ለማስጠበቅ ሲሉ በማያባራ መገዳደል እና መተላለቅ ውስጥ እንዳይገቡ ለማድረግ ነው። የሀገር ሽማግሌዎቹም ተግተው የሚነሱት ብጤዎቻቸው ወይም አቻዎቻቸው በመሆናቸው መሆኑን የመረጃ ተባባሪዎቼ ገልፀውልኛል (አቶ ገብረወልድ ገብረፃድቅ፣ አቶ መንግሥቱ አማረ፣ መቶ አለቃ ሽቤ ጣልባቸው በ18/5/99)።

ይህን ከላይ የተገለፀውን የእርቅ ጥሪ የታወቁ የአገር ሽማግሌዎች እና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ኃይማኖት መሪዎች የሚያደርጉበት ምክንያትም ከተከሰተው ከባድ ግጭት በኋላ በሚቀጥለው የመበቃቀል ወይም ደም የመመላለስ ሂደት የሁለቱም ተጋጪዎች ወገኖች እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ እየቆጠሩ እንዳይተላለቁ እና አገር ባዶ እንዳይሆን በመስጋት የአዋሳኝ ቀበሌዎች ነዋሪዎችም "አገሩ ሰው የለበትም ወይ? ባዶ ነው ወይ?" እያሉ እንዳይሳለቁ ለማድረግ በማሰብና በማቀድ ነው።

የመጨረሻው የእርቅ አቀራረብ ጥሪ ደግሞ ከላይ የተጠቀሱትን የእርቅ አቀራረብ መንገዶች በማጣመር ወይም በማቀናጀት የሚደረግ ነው። ይህም የሚደረገው ሽምግልናው "ሊሳድር" ማለትም ላይሳካ ይችላል የሚል ሥጋት ሲኖር ርብርቦሽ አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት ነው።

የመረጃ ተባባሪዎቼ በተመሳሳይ ሁኔታ እንደገለጹልኝም ከላይ የተገለጹት የእርቅ ጥያቄዎች ወይም ጥሪዎች የሚቀርቡት በሁለት ዓይነት መንገዶች ነው። በምስጢር እና በገሐድ። ምስጢራዊ የእርቅ ጥሪ የሚደረገው ጉዳዩን ለተወሰኑ እና ለታመኑ የአገር ሽማግሌዎች ወይም የኃይማኖት አባቶች ብቻ በማካፈል የግልግል ወይም የድርድር ሂደቱንም እንደዚሁ በህቡዕ እንዲፈጽሙ ለማድረግ ነው። በገሃድ የሚደረገው የእርቅ ጥሪ በአደባባይ የሚቀርብ ነው። ጥሪው የቤተክርስቲያን ደወል በመደወል እና የህዝቡን ስሜት

ወይም ቀልብ በመሳብ እከሌና እከሌን እንድታስማሙልን በታቦተ-ህጉ ስም እና በራሳችንም ስም እንለምናለን የሚል ዓይነት ነው።

4.5.2. የደም ግጭት እርቅ አመላለድ

ቀደም ሲል በቀረበው "የደም እርቅ ጥሪ አቀራረብ" ርዕስ እንደተጠቆመው የደም እ ርቅ ጥሪ በገዳይ፣ በገዳይ ወገኖች፣ በሟች ወገኖች፣ በአገር ሽማግሌዎች፣ በኃይማኖት አባቶች ወይም በነዚህ ተነሳሾች የሁለትዮሽ ወይም ሦስትዮሽ ቅንጅት ሊደረግ እንደሚችል የመረጃ ተባባሪዎቼ ገልፀውልኛል።

የመረጃ አቀባዮቼን የጠየቅኋቸው የእርቅ ጥሪ እንዴት ይቀርባል? የሚለውን ብቻ አልነበረም። የእርቅ ጥሪ ምልጃ አደራረግስ? የሚለውንም አክዬ ነበር። እነርሱ እንደሚሉትም በተለይ ገዳይ ራሱ በሀገር ሽማግሌ በኩልም ይሁን በቤተክርስቲያን በኩል ከሚያቀርበው የአስታርቁኝ፣ አስምሩኝ፣ ፍረዱብኝ ወዘተ የእርቅ ጥሪ ውጪ ያሉት ጠንከር ያለ ምልጃን ይጠይቃሉ።

ስለሆነም የሚማለዱትን ወገኖች ለማግባባት የሚያከብሩትን የሚያፈቅሩትን ዘመዳቸውን ወይም የንስሐ አባታቸውን ወይም በአካባቢው በጣም የተከበረውን የአገር ሽማግሌ፣ ወይም ቄስ እና መነኩሴ፣ አሊያም ከነዚህ የተውጣጣ አማላጅ ይላካል። የሚላኩት አማላጆችም ለነገሩ አያያዝ በሚያመቻቸው መንገድ በገሃድ ወይም በምስጢር በመሄድ እርቅ እንዲያወርዱ የሚጠየቁትን ወገኖች/ ብዙ ጊዜ የሟች ወገኖች ናቸው/ "ተማማሩ ያለፈው ይብቃ፣ የሰው ደም እሸት አያበቅልም፣ የሰው አጥንት አጥር አይሆንም ወዘተ" በማለት በልቦናቸው ያደረውን የበቀል መንፈስ ለማቀዝቀዝ ይጥራሉ።

ይሁንና የመረጃ ተባባሪዎቼ በተለያየ አገላለፅ ነገር ግን በተመሳሳይ ይዘት እንደነገሩኝ ምልጃው በአንድ እግሬታ ማለትም ጉዞ አይሳካም። ምክንያቱም ተጠያቂዎቹ ወገኖች እርቁን ቢፈልጉት እንኳን ከአንጀት ዘመዶቻቸው ጋር የመምከሪያ ጊዜ ስለሚያስፈልጋቸው "እስቲ ተውን" ሊሉ ይችላሉ። ስለዚህም የእርቅ ምልጃ ሁለት ሦስት ጊዜ ወደ ተማላጆች ዘንድ መመላለስን ይጠይቃል። በዚህም ካልተሳካ ደግሞ ተማላጆቹ በጣም ያከብሩታል የሚባለውን ታቦት በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ አደባባይ የሚወጣ መስቀል በማስያዝ ይማለድባቸዋል። ይሄ ከሆነ በኋላ እሺ ይላሉ። እሺ የሚሉትም መስቀሉን ስለሚፈሩ እንደዚሁም "ሰው አዬ እግዚአብሔር አዬ ነው" ብለው ስለሚያምኑ ነው። ሁሉም ያነጋገርኳቸው ሰዎች እንደገለፁትም የደም እርቅ ምልጃም የሚፈፀመው በዚህ መልኩ ነው።

የደም እርቅ ምልጃው ከሰመረ በኋላ ተማላጆቹ ብዙውን ጊዜም የሟች ወገኖች የራሳቸውን ሽማግሌዎች፣ ተደራዳሪዎች፣ የድርድር ሁኔታ ማለትም በገሃድ ወይም በህቡዕ

ይቀጥል? የሚለውን ከዘመድ አዝማዶቻቸው ጋር መክረው እንዲያሳውቁ ጊዜ ይሰጣቸዋል። በተቆረጠው ቀነ-ቀጠሮም ተማላጆቹ /የሚች ወገኖች/ በበኩላቸው በሀገር ሽማግሌነት የመረጧቸውን ከሦስት-አምስት የሀገር ሽማግሌዎች እና በሽምግልናውም ሂደት የሚደራደሩላቸውን ከሦስት እስከ ሰባት ተወካዮቻቸውን በድርድሩም ለመቀጠል እና ለመደራደር መፍቀዳቸውን የሚያረጋግጡላቸውን ሁለት ተያዥ ዋሶች ስም ዝርዝር ያሳውቃሉ። የመረጧቸውንም የሀገር ሽማግሌዎች፣ ተደራዳሪዎች እና ዋሶች ለማቅረብ የስምምነት ቃል ይሰጣሉ። በደመኛቸው በኩል የተመረጡ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ ተደራዳሪዎችን እና ዋሶችን ማንነት እንዲሁም ብዛት ጠይቀው ይረዳሉ ወይም አማላጆቹ ይገልፀላቸዋል። እዚህ ደረጃ ላይ ከተደረሰ በኋላ በደመኞቹ ወገኖች በኩል የሀገር ሽማግሌዎች፣ የተዋቃሽ ወይም ተደራዳሪ እና የዋሶች ተቃውሞ እና ቅሬታ ካልቀረበ የሽማግሌዎች ቁጥር ይወሰናል። ቅሬታ ከቀረበም ቅሬታ የቀረበባቸው እንዲለወጡ ይደረጋሉ። የሽማግሌዎቹም ቁጥር ከ3-9 ሊደርስ ይችላል።

የመረጃ ተባባሪዎቹ እንደሚሉት በቆላ አካባቢ 3 ወይም 5 ወይም 7 በደጋ ደግሞ 5 ወይም 7 ወይም 9 የሀገር ሽማግሌዎች ይሰየማሉ። ቁጥራቸው ምንጊዜም ጐደሎ ነው። የአገር ሽማግሌዎቹ ቁጥር 3, 5, 7 ወይም 9 የሚደረግበትን ምክንያት እንዲነግሩኝ የአገር ሽማግሌዎቹን ጠይቄ ነበር። ያገኙሁት ምላሽ የተለያዬ ነው።

አንዳንዶቹ /አቶ ቀጥይበሉ አሳምነው በ17/5/99፣ አቶ ሺፈራው ደምሴ በ9/5/99 ፣ አቶ ደጀጠና መንግሥቱ በ7/5/99፣ / የሽማግሌ እና የዳኛ ቁጥር ጐደሎ መሆን ስላለበት ነው ሲሉ ብዙዎቹ ደግሞ ለሽማግሌዎቹ ቁጥር መነሻው የመንፈሳዊው ህይወት እምነት መሆኑን ይገልፃሉ። የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና እምነት እውቀት ቀመሶች የሆኑት ቄስ ማሞ፣ አቶ ሽዋይርጋ፣ አቶ ገብረወልድ፣ አቶ መንግስቱ፣ አቶ ገብረህይወት ገለጻ መሠረት የሽማግሌዎቹ 3, 5, 7, 9, መሆን የተለያዬ ተምሳሌትነት ወይም ትዕምርትነት ይሰጠዋል።

የአገር ሽማግሌዎቹ ቁጥር ሦስት መሆን ምክንያቱ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን (ሥላሴዎችን) ስለሚወክሉ ነው። " Insight on the scriptures Vol- 2 1998፣ 511" ም በህግ ረገድ የሦስት ምሥክርነት ይበልጥ ጠንካራ መሆኑን ያወሳል።

የአገር ሽማግሌዎቹ ቁጥር አምስት መሆን ደግሞ በኢትዮጵያ "ኃጢአተኞችን ለማስተማር" የላቀ ግብረ-ሐዋርያነት ተምሳሌት ፊዕመዋል የሚባልላቸውን አቡነ-ገብረ-መንፈስ ቅዱስ ዕለተ-ክብር እንደሚወክልም የአገር ሽማግሌዎቹ ይተርካሉ።

የአገር ሽማግሌዎቹ ቁጥር ሰባት የሚሆነው ደግሞ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከፈጠረ በኋላ ዕረፍት ያደረገበትን ዕለተ-ሰንበት እንዲሁም የሥላሴን ዕለተ-ክብር መዋያ ስለሚወክል ነው ይባላል።

ዘጠኝ ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነት "የዚህ ዓለም ህይወት በቃኝ" ወይም "መነኮሰ-ህይወት" ልማድ በኢትዮጵያ አብራሂዎች (አስተማሪዎች) የሚባሉትን እና በዘጠነኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ወደ ኢትዮጵያ የገቡትን ዘጠኙን ቅዱሳን ይወክላል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው።

በእርቅ ምልጃው ወቅት የአገር ሽማግሌዎቹ፣ የተደራዳሪዎቹ እና የዋሶቹ ማንነት እና ቁጥር በደመኞቹ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ ደግሞ ድርድሩ፣ ምልጃው በተጀመረበት ሁኔታ /በገሀድ ወይም በህቡዕ/ የሚካሄድበት ቀን ይወሰናል።

ለደመኞቹ እርቅ ድርድር ማካሄጃነት ብዙ ጊዜ የሚመረጡትም ወንድ በዓላት፣ ቀናት፣ ማለትም አቦ፣ ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ጊዮርጊስ፣ ተክለኃይማኖት፣ በአለወልድ ናቸው። እነዚህ የወንድ በዓላት ቀናት የሚመረጡትም የእርቅ መሐላ የሚሰጥባቸው በመሆናቸው መሆኑን አውራ የመረጃ ተባባሪዎቼ ገልፀውልኛል።

የደም እርቅ ሽምግልና ማካሄጃ ሰዓት ወይም ጊዜ /በቀን ወይም በጨረቃ/ እንዲሁም ሥፍራው /በወንዝ፣ወይም በበረሃ በቤተክርስቲያን/ እንዲሆን የሚወሰነው በተሸማጋዮቹ (በተደራዳሪዎቹ) እና በሀገር ሽማግሌዎቹም የጋራ ስምምነት ነው። የድርድር ቦታው ተለዋዋጭ የሚሆንበት አጋጣሚም አለ። ተለዋዋጭ ሲሆንም በየድርድሩ ማብቂያ ዕለት በሦስትዮሽ ማለትም በተደራዳሪዎቹ ወገኖች እና በሀገር ሽማግሌዎቹ ይወሰናል። በዚህም መሠረት ድርድሩ በቀን ወይም በጨረቃ፣ በገሃድ ወይም በድብቅ፣ በወንዝ፣ በጫካ በኮረብታ ወይም በቤተክርስቲያን አካባቢ፣ ሊደረግ ይችላል። የድርድሩ ሁኔታም እንደተጋጪዎቹ ማንነት እና ሁኔታ በገሀድ ወይም በህቡዕ፣ በቀን ወይም በጨረቃ፣ የሚደረግ ቢሆንም ዛሬ ዛሬ የሌሊት ድርድር እየቀረ መሆኑንም የመረጃ ተባባሪዎቹ ገልፀውልኛል። ብዙ ጊዜም በቆላማው አካባቢ ድርድሩ የሚደረገው በወንዝ ዳር ሲሆን በደጋ አካባቢ ደግሞ በበረሃ፣ በኮረብታ እና በቤተክርስቲያን አካባቢ ነው።

የደም እርቁ ወንዝ ላይ የሚደረገው በአብዛኛው በወይና ደጋ እና በቆላ አካባቢዎች ነው። ይህም የሚደረገው አንድም ለተገላጋዮቹ አቀማመጥ አመቺ በመሆኑ ነው። ሁለተኛም ደግሞ ቂመኝነት እና በቀለኝነትን እንደ ወንዙ ውኃ ያፍስስልን፣ ያውርድልን፣ ይውሰድልን ለማለት መሆኑን አቶ ደጀጠና፣ ቄስ ማሞ፣ አቶ ቀጥይበሉ እና አቶ ሺፈራው ገልፀውልኛ ል። ሌሎችም እንደሚያወጉት ወራጅ ውኃ ብዙውን ነገር ጠራርጐ ይዞ የሚሄድ በመሆኑ

ቂም እና በቀልም እንደዚያ ይጠራረጉ እና ይሂዱ በሚል እምነት ነው። ግልግል እና እርቁ በበረሃ የሚካሄደውም የደም እርቅ ከባድ ጉዳይ እንደመሆኑ በሰዋራ ሥፍራ ከመንደር እና ከሰው እይታ ውጪ እንዲሆን ተገላጋይ ደመኞችንም እንዳይተያዩ በየጉድባቸው (ደባቃ) ሥፍራ ለያይቶ ለማስቀመጥ መሆኑ ይገለፃል።

በተራራ ላይ እርቁ የሚደረገውም ተራራ የእግዚአብሔር ጥሪ መንፈስ ድምፅ እና በረከት ለሙሴ የቀረበበት ስለሆነ ነው ይባላል። ይህም ሁኔታ በኦሪት ዘፍጥረት ም17 ቁ 9-11፤ ም18 ቁ5-7 እንዲሁም ም19 ቁ11-25 ከተገለፀው የወረደ እና የተወሰደ ይመስላል።

የደም እርቅ ድርድሩ እንዲጀመርበት በተቆረጠው ቀን እና ሥፍራ ሲጀመርም የመጀመሪያው የአገር ሽማግሌዎች ተግባር መሪ የሀገር ሽማግሌ መምረጥ፣ ተዋቃሾች ያቀረቧቸውን ሁለት፣ ሁለት ተያዥ ዋሶች ማለትም በየበኩላቸው አንድ የደህንነት እና የህግ ጥበቃ እንዲሁም አንድ የህግ፣ የካሣ እና የዝምድና ዋሶችን ገደብ በማስገባት ነው። ምክንያቱም ተገላጋዮቹ በገደብ ታስረው በመረጧቸው የአገር ሽማግሌዎች አማካኝነት ለመታረቅ መስማማታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

የደህንነት ጥበቃ እና የህግ ዋሶቹ ተግባር ተደራዳሪዎቹ በድርድሩ ሂደት አንዳች መተናኮል እንዳይፈጥሩ እንዲሁም ከእርቅ በኋላ ውል እንዳያፈርሱ ዋስትና መሆን ነው። በተለይ ከእርቅ በፊት ሌላ የማጥቃት ሙከራ ወይም ጥቃት ቢደረግ የሚጠየቁ ወገኖችም ናቸው።

የአገር ሽማግሌዎቹ እንደሚሉትም ለደህንነት ዋስትና የሚመረጥ ሰው በመረጡት ሰዎች ላይ ከፍተኛ አመኔታ ያለው "አንጉቴን ለሰይፍ አሰጥላቸዋለሁ" የሚል ዓይነት መሆን አለበት። ምክንያቱም በድርድሩ ላይ አንዳች የኃይል ጥቃት ተያዥ ከሆነላቸው ወገኖች በኩል በሌላው ተደራዳሪ ወገን ላይ ቢደርስ በህግም በኃይልም ተጠያቂ ነው የሚሆነው ይላሉ የአገር ሽማግሌዎቹ። ስለሆነም ብዙ ጊዜ ቁሶች ለዚህ ተግባር ተያዥ አይሆኑም። አይደረጉምም። ተያዥ የሚደረገው በሀብቱ፣ በጉልበቱ፣ በወገኑ "አንቱ" የተሰኘ ተያዥ ያደረገለት ሰዎች ክህደት ቢፈፅሙ እንኳ ራሱም ተመልሶ ባለጋራ ሆኖ ሊቆምባቸው የሚችል ሰው ነው።

ሁለተኛው የህግ እና የዝምድና ዋስ ኃላፊነት እርቁ ከሰመረ በኋላ ባሉ አፈፃፀሞች ላይ ነው። ተግባሩም የእርቁ ውሳኔ እንዲፈፀም ማድረግ ነው። የተዋሳቸው ወገኖች ተስማምተው እርቅ በተፈፀመበት ሁኔታ መሠረት ባይፈጽሙ ግን የማስፈፀም ኃላፊነት እና ተጠያቂነት አለበት።

4.5.3. የደም እርቅ ድርድር ሂደት

ሁሉም ቁልፍ ወይም አውራ የመረጃ ተባባሪዎቹ እንደገለፁልኝ የእርቅ ጥያቄ ቀርቦ፤ የተሸማገሉ ምልጃ ተካሂዶ፤ የአገር ሽማግሌዎች ተሰይመው፤ የሟች እና የገዳይ ወገኖች ተደራዳሪዎች በሰላም ለመደራደር ተያዥ ወይም ዋስትና ከሰጡ በኋላ በተመረጠው ቀን፤ ሰዓት፣ እና ቦታ ድርድሩ ፀሎት በማድረስ ይጀመራል፤ ይዘጋልም።

ድርድሩ በቁስ ፀሎት የሚጀመረው እና የሚፈፀመውም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና እምነት አስተምህሮ ህግን ለመፈፀም መሆኑን አባ ዘውዴ ደምድም በ13/5/99፤ ቁስ ማሞ ጻደቀ በ6/5/99 ይገልፃሉ። እነርሱ እንደሚሉት የሰው ልጅ ሲወለድ፤ ክርስትና ሲነሳ፤ ፀሎት ይደረግለታል። "ነፍስ ሲያውቅ" ማለትም ክፉ እና ደጉን ሲለይም ጠዋት ሲነሳ "በሰላም አውለኝ" ምግቡን ከመብላቱ በፊት እና ከበላም በኋላ "የተባረከ ገበታ አድርግልኝ"፤ አንድን ሥራ ሲጀምር "በሰላም አስጀምረህ በሰላም አስጨርሰኝ"፤ ሲጨርስ "በሰላም እንዳስጀመርከኝ እና እንዳዋልከኝ ፍፃሜውንም የሰላም አድርግልኝ"፤ እቤቱ ሲገባና ሲተኛም "በሰላም አሳድረኝ" በማለት ይዘታቸው የተለያዩ ፀሎቶችን ያደርግ ዘንድ የተገባ ስለሆነ ነው። በመሆኑም በድርድሩ መጀመሪያ እና መጨረሻም ላይ ፀሎት የሚደረገው የተቃና እና የሰመረ የፀና ይሆን ዘንድ ከፈጣሪ በረከተ- ረድኤት ለማግኘት ነው።

የሟች እና የገዳይ ወገን ተደራዳሪዎች ሆነው የሚቀርቡትም ብዙ ጊዜ የሟች እና የገዳይ የቅርብ ቤተሰቦች እና ዘመዶች ማለትም አባት፤ ልጅ፤ ወንድም፤ አጐት፤ አክስት ወዘተ ናቸው። በሟች እና በገዳይ ወገኖች መካከል "የሚገዳደር" ማለትም የሚወዳደር የነፍስ መጠፋፋት ከሌለ በስተቀር ገዳይ በግልግሉ ድርድርም ሆነ በእርቁ ላይ አይገኝም። ገዳይ በሥነ-ሥርዓቱ ላይ የሚገኘው የደም መከፋፈል እኩሌታ ሲኖር ብቻ መሆኑን ከደጋም፤ ከወይና ደጋም፤ ከቆላም ያነጋገርኳቸው የመረጃ ተባባሪዎቹ ሁሉ አረጋግጠውልኛል።

በወይና ደጋ እና በቆላ አካባቢዎች ድርድሩ ሲጀመርም ብዙ ጊዜ የገዳይ ወገኖች የሽማግሌ ምሳ በሚል አርባ ብር ለሽማግሌዎቹ መሪ ወይም ሰብሳቢ ያስይዛሉ። በደጋ አካባቢ የተጠቀሰው ገንዘብ አይያዝም። ከዚህ ውጭ በሁሉም አካባቢዎች የሟች እና የገዳይ ወገን ተዋቃሾች ወይም ተደራዳሪዎች የሚቀመጡበት ወይም የሚጋለሉበት ሥፍራም ተለይቶ ይመደብላቸዋል። ይኸውም በዋስትና ተያዦቻቸው ይገለፅላቸዋል። በእነዚሁ የዋስትና ተያዦቻቸው አመላካችነት እና ቃፊርነትም በየተመደበላቸው ሥፍራ ይቀመጣሉ። ለተደራዳሪዎቹ የሚመደብላቸው ሥፍራ ከአገር ሽማግሌዎቹ ጋርም ሆነ እርስ በርስ ሊተያዩ የማይችሉበት "ሰዋራ" ወይም ደባቃ ቦታ ነው። ተደራዳሪዎች በየቦታቸው መገኘታቸውን የሰላማዊ ድርድር ዋስትና ተያዦቻቸው ለአገር ሽማግሌዎች ካሳወቁ በኋላም በቅድሚያ

የሚች ወገን ተዋቃሾች ወቀሳቸውን እንዲያሰሙ፤ በመቀጠልም የገዳይ ወገኖች ምላሽ እንዲሰጡ በልጅ እግሩ የአገር ሽማግሌ አማካኝነት ይጠራሉ። ብዙ ጊዜም የዋስትና ተያገሯቸው ከተያዟቸው ተዋቃሾች እና የአገር ሽማግሌ መሸንገያ (መቀመጫ) ሥፍራ መሀል ላይ ሆነው መልዕክት እንዲያስተላለፉ ይደረጋል።

ተዋቃሾች ወይም ተደራዳሪዎች ወደ ሽምግልናው ሥፍራ ሲሄዱም ሆነ ወደ አገር ሽማግሌዎች ሲቀርቡ የጦር መሣሪያ እንዲይዙ አይፈቀድላቸውም። በትርም እንኳን ቢሆን ይዘው ከአገር ሽማግሌዎቹ ፊት አይቀርቡም። በዚህ ሂደት የሚዘልቀው የደም እርቅ ድርድርም እጅግ ሰመረ ወይም ተሳካ ሲባል እስከ ሦስት ወራት እጅግ "ሳደረ" ወይም ዘገየ ሲባልም እስከ ሦስት ዓመት "ሊፈጅ" ማለትም ሊወስድ እንደሚችል የአገር ሽማግሌዎቹ ይገልፃሉ። እንደአገር ሽማግሌዎቹ አገላለጽ የደም እርቅ ድርድር ረጅም ጊዜ የሚወስደውም ተደራዳሪዎቹ ከተለመደው የደም እርቅ መስማሚያ እና መፈፀሚያ ልማድ ውጪ የሆነ አንዳንድ "አሰናካይ፣ አዋኪ ወይም አንቃፊ ነገር ሲያቀርቡ ነው።" ደመኞቹ ለእርቅ እስቲበቁ ድረስም ድርድሩ በዚሁ መልኩ ይቀጥላል።

4.5.4. የደም እርቅ ሥርዓተ አፈጻጸም

የደም እርቅ ሥርዓት የሚፈጸመው የሚች እና የገዳይ ወገኖች ተዋቅሰው የአገር ሽማግሌዎቹ ከቀረቡላቸው የወቀሳ ጭብጦች ተነስተው ለተደራዳሪዎቹ በሚያቀርቡት የመስማሚያ ሐሳብ ላይ ተዋቃሾቹ መስማማት ሲችሉ ነው። የአገር ሽማግሌዎቹ ደጋግመው እንደገለፀልኝ የማስማሚያ ሐሳቡን የሚያመነጨት የግድያውን መንስኤ፤ የነገሩን ክብደት እና ቅለት፤ የአገዳደሉን ዓይነት ወይም ሁኔታ ማለትም ሴራ ያለበት፣ የታሰበበት፣ የታቀደ፣ የተቀነባበረ ወይም የቆየ ቂም በቀል፣ ወይም አበ-ደምነት፣ ምክንያት የተከሰተ የ"ዓይን ደም ይጠላል" ውጤት እንዲሁም ያልታሰበ ድንገተኛ ወይም የዕለት ጠብ፣ ምክንያት መሆኑን እንደገናም የገዳይን እና የሚችን ሰብዕና ማለትም ጠባይ፣ ባህርይ፣ ኑሮ፣ የቤተሰብ ሁኔታ፣ የመኖሪያ ቦታ መቀራረብ፣ ወዘተ ግምት ውስጥ በማስገባት ወይም ታሳቢ በማድረግ ነው።

ከደጋ አቶ ሽዋይርጋ አስፋው በ12/5/99፣ አቶ ገብረወልድ ገብረዓድት በ18/5/99 ከወይና ደጋም አቶ ሺፈራው ደምሴ በ9/5/99፣ አቶ ቀጥይበሉ አሳምነው በ17/5/99 ከቆላም አቶ ደጀጠና መንግሥቱ በ7/5/99፣ ቁስ ማሞ ፀደቀ በ6/5/99 ወዘተ ያነጋገርኳቸው፣ የአገር ሽማግሌዎች እንዳረጋገጡልኝም የደም እርቅ ማስማሚያ ሐሳቡ ገዳይ የሚኖርበትን ጉጡን ወይም ቀበሌውን ለቆ ወንዝ ተሻግሮ ጋራ ዞሮ በአካባቢው ባሉ ወረዳዎች ውስጥ መኖር እንዲችል ከመፍቀድ እስከ መንዝን /መንዝ የሚባለው ላሎ ምድርን፣ ማማ ምድርን፣ ጌራ ምድርን፣ ቀያን፣ ግሼን፣ አንያኪያን፣ መዘዞን፣ ያካትታል/ ማስለቀቅ እና እንዲሰደድ

እስከማድረግ ይደርሳል። ሁሉም የአገር ሽማግሌዎች በተመሳሳይ ሁኔታ እንደገለፁትም አልፎ አልፎ በልዩ ልዩ ምክንያት ገዳይ አገር የማይለቅባቸው አጋጣሚዎች ቢኖሩም ዋነኛው የደም እርቅ ማስማሚያ መንገዝን ማስለቀቅ ነው።

ገዳይ መንገዝን ሳይለቅ እንዲኖር ሊፈቀድለት የሚችልበት አነስተኛ አጋጣሚ አለ ያሉበትን ሁኔታ የአገር ሽማግሌዎቹ እንዲያብራሩልኝም አንስቼባቸው ነበር። የአገር ሽማግሌዎቹ እንደሚሉት ገዳይ የገደለበትን አካባቢ ወይም ጉጡን የማይለቀው በሚች እና በገዳይ ወገኖች መካከል "የሚገዳደር" ማለትም የደም ወደር ወይም "እኩሌታ " ማለትም አቻ የኖረ እንደሆን ነው።

ገዳይ መንገዝን ሳይለቅ በአንዱ ወረዳ ውስጥ እንዲኖር ስምምነት ላይ የሚደረሰው ደግሞ የገዳይን እና የሚችን ቀዳሚ ግንኙነት ሁኔታ፤ ቤተ-አግባብነት፤ ግለ-ሕይወት እና ማኅበራዊ ህይወት ስሌት ውስጥ በማስገባት ነው። ይኸውም ስሌት በገዳይ እና በሚች መካከል ለፀብ እና ለግድያ የሚያበቃ ምክንያት ሳይኖር በድንገት ባልታሰበ እና ባልታቀደ አጋጣሚ /በገና ጨዋታ፤ በጥምቀት፤ የፈረስ ግልቢያ እና ጉግስ፤ በጦር መሳሪያ መባረቅ፤ በፀብ ወይም አምባንሮ ላይ በመገላገል ሂደት /በሚች እና በገዳይ መካከል ከፍተኛ መፈቃቀድ መኖሩ በተረጋገጠበት ሁኔታ ነፍስ የጠፋ እንደሆነ፤ ሚች በገዳይ ላይ የታወቀ እና "የተነወረ" አድራጎት ፈፅሞበት "ደመ ደመ-ክልብ" ሆኖ የተቆጠረ እንደሆነ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ሚች ልጆች ካሉት እና ልጆቹም "ለእህል የደረሱ ለሥራ ያልጐለመሱ" ሆነው ሲገኙ እና ደጋፊ ሳይኖራቸው ሲቀር ገዳይ ለሚች ልጆች ማሳደጊያ የሚሆን "ወጀ" ማለትም የደም ካሣ ከፍሎ ከገደለበት አካባቢ ራቅ ብሎ እንዲኖር የሚፈቀድበት አነስተኛ አጋጣሚ እንዳለ ተረድቻለሁ።

ይሁንና ሁሉም የመረጃ ተባባሪዎቼ እንደነገሩኝም መንገዝ ውስጥ ወጀ ማለትም የደም ካሣ የሚቆረጥበት እና የሚበላበት አጋጣሚ እጅግ አነስተኛ ነው። ዋነኛው የደም እርቅ ማስማሚያ መንገዝን ማስለቀቅ፤ ከዚያ ከወረደ ገዳይ ወረዳውን እንዲለቅ ማድረግ ነው።

ለመሆኑ ላሎ-ማማ ውስጥ ደመኝነት ሳይኖረው ሰው የገደለ ሰው ወረዳውን ሳይለቅ በገደለበት አካባቢ ይኖር ዘንድ ወይም መንገዝን በጠቅላላው ፈቅዳችሁ ያስታረቃችሁት ሰው ወይም ያስታረቃችሁበት አጋጣሚ አለወይ? በማለት ካነሳሁባቸው ያነጋገርኳቸው አሥር የመረጃ ተባባሪዎቼ መካከል ዘጠኙ "ሰው ገድሎ በአባት አገር መኖር የታለ?" ፤ የገደለ ያባቱን አገር ተነቀለ ነው፤ ሰው ገድሎ በአገር መቀመጥ የለም፤ ሰው ገድሎ በአገር መቀመጥን ያባቶቻችን አስተዳደር አላቆየንም፤ ገደለ ተነቀለ ነው፤ ገድሎ በመንበሩ የሚኖር መንግሥት ብቻ ነው"ወዘተ በሚል አገላለፅ ነፍስ የገደለ ሰው በገደለበት አካባቢ መኖሩን ሰምተውም፤ አስማምተውም እንደማያውቁ ሲገልፁልኝ አቶ መንግስቱ አማረ ብቻ አንድ

አጋጣሚ እንደሚያስታውሱ ነግረውኛል። አቶ መንግስቱ አማረ እንደሚሉት በአንድ ወቅት ብቻ በዕለት ድንገተኛ ጠብ ምክንያት ወምቻ እሚባል አካባቢ አንድ ሰው ነፍስ አጥፍቶ እየሸሸ ከቆየ በኋላ እርቅ ጠይቆ ስለነበር የአገር ሽማግሌዎች የገዳይንም የሟችንም ቤተሰብ ሁኔታ በማጥናት ከተለመደው "የአባት ዕድር" ውጪ የማስማማያ ሐሳብ አቅርበው ማስማማታቸውን ያስታውሳሉ።

አቶ መንግስቱ እንዳጫወቱኝ ገዳይ ለአቅመ-አዳም እና ሔዋን ያልደረሱ ልጆች እና አልጋ ላይ የዋሉ እናት ስለነበሩት የሟችም ልጆች እራሳቸውን ያልቻሉ እና ደጋፊም ስላልነበራቸው የገዳይም የሟችም ቤተሰቦች ችግር ላይ ስለነበሩ ገዳይ ለሟች ልጆች ማሳደጊያ የሚሆን ወጀ /የደም ካሣ/ ከፍሎ አገሩ እንዲገባ ነገር ግን በገደለው ሰው መኖሪያ አካባቢ "ድርሽ እንዳይል" ማለትም በመንገድም፣ በውኃም፣ በሥራ ስምሪትም፣ ላይደርስ ከሞላሌ ከተማ ግን ላይከለከል አገዳድበው አስታርቀዋል።

ገዳይ ከከተማ ያልተከለከለበት ምክንያት ምንድን ነበር? ብያቸውም ከተማ ገበያ፣ ፖሊስ፣ ፍርድ ቤት፣ ህክምና ማግኛ ስለሆነ መከልከል አስቸጋሪ ስለሆነብን ነው ብለውኛል።

ከላይ እንደተጠቀሰው ገዳይ "ወጀ" ማለትም የደም ካሣ ከፍሎ በገደለበት አገር የሚኖረው እጅግ የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥም ነው። የአገር ሽማግሌዎቹ እንዳወሱልኝ "ወጀ" /የደም ካሣ መብላት መንዝ ውስጥ የተወገዘ እና የተነወረ ነው። ስለሆነም ዋነኛው የላሎ-ማማ ምድር ሕዝብ የደም ግጭት ማስማሚያ አገር ማስለቀቅ ነው። እንደ አገር ሽማግሌዎቹም ሆነ እንደሌሎቹ እምነት የነፍሰ-ገዳይ አገር መልቀቅ ከላይ ከአባት የወረደ ልማድ ነው።

የዚህን ገዳይን አገር የማስለቀቅ እና እንዲሰደድ የማድረግ ጥንተ አመጣጥ ለመረዳት መጠነኛ አሰሳ አድርጌያለሁ። እናም ዛሬ የላሎ-ማማ ምድር ሰው "የገደለ ተነቀለ" የሚለው እና የሚተገብረው ከፍትሐ-ነገሥት ከቀሰመው እና እንደልማድ ከያዘው ሥራት የተነሳ ይመስላል። ፍትሐ-ነገሥት (1958:542) "መግደል የተከለከለ እንደ ኃጢአትም የተቆጠረ ነው የገደለ ይገደል" የሚል ጠቅላይ መሠረተ-ሐሳብ ካሰፈረ በኋላ ስለ አገዳደል አድራጉት፣ ስለተገዳይ እና ገዳይ ባህርይ፣ ሁኔታ፣ ማንነት ዘርዘር ያለ የዳኝነት አስተያየት አሰጣጥ እና አፈፃፀም ድንጋጌ አለው። ከነዚህም ውስጥ አንዱ "ሳያውቅ የገደለ ሰው አገር ጥሎ ይሰደድ" የሚለው ነው። ይኸውም እንግዲህ ገዳይ እገድላለሁ ብሎ ሳያስብ እና ሳያቅድ ሟችን በድንገት መትቶ ቢገድል በተመሳሳይ ሁኔታ አይመት ይሰደድ ለማለት ነው። ይሁንና የላሎ-ማማ ሰው "እርቅ የሰው ደም ያደርቅ" ቢልም መልሶ ደግሞ "ዓይን ደምን ይጠላል ገዳይ ገለል ይበል" በሚል አስተሳሰብ ይመስላል በጨዋታም መሀል በአጋጣሚ፣ በዕለት፣

ድንገተኛ ፀብም፣ ይሁን በቂም በቀል የተነሳ ለተፈፀመ ግድያ ገዳይ አገር ጥሎ እንዲሄድ ወይም እንዲሰደድ ያደርጋል። በዚህም ተስማምቶ ይኖራል።

የኋሊት ሲታይ ሰው የገደለ ሰው መሸሸ እና መሰደድ እንዳለበት የተደነገገው በፍትሐ-ነገሥት ብቻ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ ይኸው ተጠቅሷል። ኦሪት ዘኁልቁ ምዕራፍ 35 ቁጥር 9 -28 ላይ "እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው .... በስህተት ነፍስ የገደለ ሰው ወደዚያ ይሸሽ ዘንድ የመማፀኛ ከተሞች እንዲሆኑላችሁ ከተሞችን ለእናንተ ለዩ ..." ይኸው ዓይነት አገላለፅ ኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 4 ቁጥር 41-43 ላይም ይገኛል። ". . . ጠላቱ ያልሆነውን ባልንጀራውን ሳያውቅ የገደለ ሸሽቶ በሕይወት ይኖር ዘንድ....." ከተሞች ተለይተው ተጠቅሰዋል ወይም ተሰጥተዋል።

ስለሆነም ዛሬ ላሉ-ማማ ምድር ውስጥ የሚታየው ነፍሰ-ገዳይን ከአካባቢው እንዲለቅ በማድረግ ባህላዊ የደም እርቅ ሥርዓት መፈፀም ከላይ ከተጠቀሱት ፍትሐ-ነገሥት እና መጽሐፍ ቅዱስ ድንጋጌዎች የመነጨ ይመስላል።

ፍትሐ-ነገሥቱ በአጠቃላይ ይዘቱ ሲታይ ሥጋዊም መንፈሳዊም ነው። መጽሐፍ ቅዱሱም ቢሆን ከታሪክ፣ ከህግ እና ከትንቢት የወጣ ወይም የዘለለ አይደለም።

የአገር ሽማግሌዎቹ እንደሚሉትም ደመኞቹ ቀደም ሲል ከቀረቡት የሰላም መፍጠሪያ አማራጮች በአንዱ ለመታረቅ ይስማማሉ። ስምምነቱም በሰነድ ማለትም በጽሑፍ ይሰፍራል። በጽሑፍ የሰፈረውን ሐሳብም የአገር ሽማግሌዎቹ መሪ ወይም እርሱ የሚሰይመው ሰው ሁለቱን ተደራዳሪ ወገኖች በየተራ በማስጠራት "ግልግሉን ያዘራላቸዋል" ማለትም ያሰማቸዋል።

ምንም እንኳን በግልግል ሰነዱ ላይ የሚሰፍሩት የመገላገያ እና የመታረቂያ ሐሳቦች ቀደም ሲል የሟች እና የገዳይ ወገኖች በወቀሳ ወቅት ያቀረቧቸው፤ የአገር ሽማግሌዎቹም መክረው ዘክረው ለማስማሚያነት የመረጧቸው ነጥቦች ቢሆኑም ለተገላጋዮቹ ወገኖች በየተራ ማስማቱ የተለመደ ነው (አቶ ሽዋይርጋ አስፋው በ11/5/99፤ አቶ መንግሥቱ አማረ በ18/5/99፣ መቶ አለቃ ሽቤ ጣልባቸው በ18/5/99፣ አቶ ደጀጠና እና ቄስ ማሞ ፀደቀ በ7/5/99)። የግልግል ሰነዱን ይዘት በመጀመሪያ እንዲሰሙ የሚደረጉትም ብዙውን ጊዜ የሟች ወገን ተደራዳሪዎች ናቸው። ይህም የሚሆነው በአብዛኛው ተጐጂዎቹ እና ለእርቅ ተጋባጮቹ እነሱ በመሆናቸው ከበፊታ ለመስጠት እንደሆነ ይነገራል።

የሟች ወገኖች የግልግል ገደቡን እና የእርቅ ሐሳቡን ይዘት አዳምጠው መስማማታቸውን አረጋግጠው ሲመለሱ ደግሞ የገዳይ ወገኖች ይጠራሉ። እነሱም በተራቸው የመስማሚያ ሐሳቡን ሰምተው የእርቅ ሰነዱን መቀበላቸውን ካረጋገጡ

ከሽማግሌዎቹ ፊት ለአፍታ ያህል ወደመጡበት መለስ እንዲሉ ይነገራቸዋል። ከዚያም የሚች ወገኖች ተጠርተው የእርቅ ሰነዱ ላይ በቅድሚያ ይፈርማሉ። በመቀጠልም የገዳይ ወገን ተደራዳሪዎች ቀርበው ፊርማቸውን ያሳርፋሉ።

ከላይ የተገለፀው ሁሉ ሲደረግ ማለትም ተገላጋዮቹ ወገኖች ወደ አገር ሽማግሌዎቹ ሲቀርቡ ምንጊዜም በትር ወይም ሌላ የጦር መሣሪያ አይዙም፤ እንዲይዙም አይፈቀድላቸውም። የግልግል ተያዥ ዋሶቻቸው ዋና ተግባርም የድርድር እና የእርቅ ሂደት እንዳይደፈርስ ማድረግ በመሆኑ ተግተው ይቆጣጠራሉ።

የግልግል ሰነዱ ቅጂም በሦስት ኮፒ ተዘጋጅቶ ዋናው በጋራ "ባነሱት" ማለትም በመረጡት የግልግል እና እርቅ የዘመድ ዳኛ እጅ እንዲቀመጥ፤ ቀሪው ለነርሱ እንዲደርሳቸው ይደረጋል። የግልግል እና እርቅ ሰነዱም እርቁ የተደረገበትን ቀን፤ የአስታራቂ ሽማግሌዎቹን ስም፤ ድርድሩ የተደረገበትን የግድያ መንስኤ፤ የተደራዳሪዎች ዋና ዋና የወቀሳ ጭብጦች እና የመስማሚያ ሐሳብ አቅርቦቶች እንዲሁም የአገር ሽማግሌዎቹ ያመነጩትን ማግባቢያ ወይም ማስማሚያ ሐሳብ፤ እና ገደብ ይይዛል ወይም ያካትታል።

በገደብነት የሚሰፍረው ሐሳብ እርቁን ያፈረሰ ወገን የገባበትን ግዴታ እና የዋሶቹን ተግባር እና ኃላፊነት የሚገልፅ ነው። በመሆኑም ብዙ ጊዜ በገደብነት የሚደነገገው ግልግሉን ያፈረሰ ወገን ከአንድ ሺህ እስከ ሦስት ሺህ ብር የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ለባላጋራ እና ለመንግሥት እንዲከፍል የሚል ሀሳብ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ቀደም ሲልም ሁለቱ ተደራዳሪ ወገኖች በሰላም ለመደራደር የሰጧቸውን ሁለት ሁለት ዋሶች /የካሣ እና የዝምድና እንዲሁም የደህንነትና የህግ ዋሶች/ ግዴታዎች ያስቀምጣል።

የግልግል ሰነዱ መኖር ለምን አስፈለገ? የሚል ጥያቄ ሰንዝሬም ነበር። የመረጃ ተባባሪዎቹ ለዚህ የሰጡኝ ምላሽ የተለያዬ ነው። አንዳንዶቹ የግልግል ሰነዱ መኖር ከአባት የወረደ ነው ይላሉ። እንደነዚህኞቹ ገለፃ ጥንትም ቢሆን "የተፃፈ ነገር ይታወሳል፤ በቃል ያለ ይረሳል፤" እየተባለ የግልግል እና እርቅ ሰነዱ በዘመድ ዳኛ እጅ እንዲያዝ እና እንዲቀመጥ ይደረግ እንደነበር ከአባቶቻቸው ሲሰሙ መኖራቸውን ከዚያ ምሪት በመነሳትም ዛሬ ደግሞ በዘመድ ዳኛውም፤ በታራቂዎቹም እጅ እንዲቀመጥ እያደረጉ ናቸው። የዚህም ሰነድ መኖር ጠቀሜታው ታራቂዎቹ ወይም ልጆቻቸው ውሉን ባዩ ቁጥር ለበቀል የመነሳሳት መንፈሳቸው እንዲካክም ማለትም እንዲደክም፤ እንዲቀንስ ለማድረግ ነው። የአካባቢው ሕዝብም "ውለታው በጽሑፍ የሰፈረን ነገር ያከብራል"። በዚህም ምክንያት የግልግል ሰነዱ አስፈላጊ ነው ይላሉ (አቶ ሺፈራው ደምሴ እና አቶ ገብረሕይወት አሳምነው በ9/5/99) እንዲሁም አቶ ቀጥይበሉ አሳምነው በ17/5/99))።

አንዳንዶቹ ደግሞ የግልግል ሰነዱ አስፈላጊነት ከታራቂዎቹ አንዱ ወገን ቢያፈርስ ውሉ የፈረሰበት ወገን ውሉን ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት በመውሰድ እንዲፀናለት ሊያደርግ ስለሚችል ነው የሚል እምነት ወይም አስተሳሰብ አላቸው (አቶ ደጀጠና መንግሥቱ፣ ቂስ ማሞ ጸደቀ በ6/5/99)።

ሌሎቹ ደግሞ የውል ሰነዱ መኖር ከቆየ ልማድ የወረደ እንጂ ዛሬ ፋይዳ የለውም ይላሉ። እንደነዚህኞቹ የአገር ሽማግሌዎች አስተያየት የውል ሰነዱ ዋጋ የነበረው የ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ከመውጣቱ እና ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ነበር። ከዚያ በፊት ውሉ ዳኛ ፊት ቀርቦ ይፀና እንደነበርም አብነቶች እየጠቀሱ ይናገራሉ።
ውሉ በህግ ፊት ዋጋ ከሌለው ለምን ታዋውላላችሁ? ብያቸውም

> "ሁሉም ሰው ይህንን በውል አይገነዘበውም። በተለይም ደግሞ 'የሚገዳደሉት ሰዎች ህጉ ይሄንን ያንን ይላል' የሚል እውቀት ብዙም አይኖራቸውም ወይም የሌላቸው ናቸው። ስለዚህ እኛም የነበረውን ልማድ በመከተል እናዋውላቸዋለን። ታራቂዎቹም ውል ከሌለ የተዋዋሉም የታረቁም አይመስላቸውም" ይላሉ /አቶ ገብረወልድ ገ/ጻድቅ፣ አቶ መንግሥቱ አማረ፣ አቶ ሽቤ ጣልባቸው በ18/5/99/

የካሣ እና የዝምድና ዋሶቹ የሚጣልባቸው ኃላፊነት የተዋሷቸው ወገኖች ግልግሉን ቢያፈርሱ በነርሱ "እግር" ማለትም ፈንታ በተጠያቂነት ቦታ መያዝ እና ለባላጋራ እንዲከፈል የተጣለውን ካሣ መክፈል ሲሆን የህግ ዋሶቹ የሚጣልባቸው ግዴታ ደግሞ ለመንግሥት የተጣለውን ካሣ የመክፈል ነው።

የደም እርቅ ግልግሉ ተሳክቶ የስምምነቱ ውል በሚፈረምበት ወቅትም ከገዳይ እና ከሟች ወገኖች ተደራዳሪዎች በተጨማሪ የገዳይ እና የሟች ለአቅመ-አዳም እና አቅመ-ሔዋን የደረሱ እስከ ሰባት ትውልድ የሚቋጠሩ ዘመዶቻቸው እንዲገኙ ይደረጋል። ይህም የሚደረገው ግድያውን የሚያውቁ እና የሰሙ አዋቂዎቹም ሆኑ ታዳጊዎቹ ወገኖች በሙሉ ሲከነክኑ፣ ሲቆጩ፣ ሲያቁሙ፣ እንዳይኖሩ ነገሩ በእርቅ እልባት ማግኘቱን እንዲያውቁ እና ልባቸው እንዲረጋ በማሰብ ነው በማለት የአገር ሽማግሌዎቹ ይገልጻሉ። እነዚህ ሁሉ በተገኙበትም ከስምምነቱ የፊርማ ሥነ-ሥርዓት ቀጥሎ ተደራዳሪዎቹ ወገኖች የሚፈፅሟቸው የእርቅ ማፅኛ እና መደምደሚያ መሐላዎች ይፈፀማሉ። በተለይም በአብዛኛው የላሎ-ማማ ምድር አካባቢ የመጀመሪያው መሐላ የሚፈፀመው ጥይት የጮረሱ ሦስት ጠመንጃዎችን ወይም በዚሁ ቁጥር በመደዳው የተጋደሙ ጠመንጃ እና ጦሮችን ተደራዳሪዎች /በቅድሚያ የሟች ቀጥሎ የገዳይ/ እንዲራመዱ በማድረግ ነው። በቅድሚያ የሟች ወገኖች እንዲራመዱ የሚደረገውም ብዙ ጊዜ ግልግሉን ሊያፈርሱ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱት እነሱ በመሆናቸው ነው።

የሚችና የገዳይ ወገኖች ጠመንጃዎችን ሲራመዱ

ተደራዳሪዎቹ ወገኖች የተጋደሙትን የጦር መሣሪያዎች በሚራመዱበት ወቅት "በራሴም ሆነ በሰው ማናቸውንም ምድራዊ ጥበብ እና ዘዴ ተጠቀሜ መጥፎ ነገር ብሰራ ከዚህ መሣሪያ አንዱ ቢስተኝ ሌላው አይሳተኝ" እያሉ ሁለቱም ተደራዳሪ ወገኖች ጠመንጃዎቹን ይራመዳሉ። ቀደም ሲል እንደተገለፀው ተገላጋዮቹ ወገኖች ጠመንጃዎቹን ተራምደው እንደጨረሱም የግልግል እና እርቅ የዘመድ ዳኛው ከአጠገቡ አፈር በጥርኙ ዘግኖ ለሚች ወገን ተደራዳሪ መሪ ያስጨብጠዋል። ተገላጋዩም "ይቺ አፈር ቆሚም ምግቤ ብሞትም ልብሴ ነች። ይህን እርቅ ብክዳ ይቺ አፈር ትክደኝ " በማለት መሐላ ይፈፅማል። አፈሯንም ለሌላው ያቀብላል። ሁሉም ማለትም የግራ ቀኙ ተደራዳሪዎች በተመሳሳይ ሁኔታ መሐላውን ከፈፀሙ በኋላ አፈሩን ለዘመድ ዳኛው ይመልሳሉ። የዘመድ ዳኛውም አፈሩን በጨርቅ ቋጥሮ ተደራዳሪዎች በፈቀዱት /ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ጊዮርጊስ፣ በአለወልድ ወዘተ/ በአንዱ ቤተክርስቲያን ግቢ ታቦቲ በተገኘበት ለመቅበር ይይዛል። ኋላም ይቀብራል። አፈር የመጨባበጥ እና የመቀባበሉ መሐላ የሚፈፀምበት ምክንያት እና ተምሳሌት ምንድነው ያልኳቸው የአገር ሽማግሌዎች እንዳብራሩልኝም የሰው ልጅ ህይወቱን የሚመራው /አርሶ፣ ዘርቶ፣ አብቅሎ/ የሚመገበው እና የሚለብሰው እና የሚኖረው በመጨረሻውም የሚያርፈው /የሚቀበረው/ "አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ" እንደሚባለው በርሱ ስለሆነ ቂም በቀልም እንደዚያው ወደ አፈር ገብቷል በሚል መንፈስ ነው (አባ ዘውዴ ደምድም በ13/5/99፣ ቄስ ማሞ ጸደቀ በ7/5/99፣ አቶ ሽዋይርጋ አስፋው በ13/5/99፣ አቶ ገብረወልድ ገ/ጻድቅ በ18/5/99)።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የሟችና የገዳይ ወገኖች አፈር ሲጫበጡ

ሁለቱ ማለትም የግራ እና የቀኙ ተገላጋዮች ተደራዳሪዎች መሣሪያዎቹን ተራምደው እና አፈሩን ተጫብጠው ከጨረሱ በኋላም በመቀጠል በሀገር ሽማግሌነት ወደተሰየሙት ቁስ ወይም መነኩሴ ጠጋ እያሉ መስቀል እየተሳለሙ እና እየሳሙ "ቃልዎ ይድረሰኝ ውለታ አላፈርስም ዘመድ ይሙት መንግስት ይሙት አልከዳም ይቅር ለእግዚአብሔር" እያሉ የመሐላ ቃል ያሳልፋሉ። ከላይ የተጠቀሱት ሥርዓቶች ከተፈፀሙ በኋላ ደግሞ የሥጋ መቋረጥ ሥነ-ሥርዓት ይካሄዳል። የአገር ሽማግሌዎቹ እንደሚሉት የሥጋ መቋረጥ ሥነ-ሥርዓቱም በሁለት መንገድ ይፈፀማል። አንደኛው መንገድ በዕለተ እርቁ ጥቁር ያልሆነ ከብት፣ ፍየል ወይም በግ ከተገኘ እና ወቅቱ "ብልት" ማለትም ፍስክ ከሆነ እርድ ወዲያው ይፈፀማል። ወቅቱ ፍስክ ካልሆነ ደግሞ በቀነ ቀጠሮ ይቆረጣል። እርዱም የሚፈፀመው ከሀገር ሽማግሌዎች መካከል የተሰየሙት ሥልጣነ-ክህነት ያላቸው አባት የመባረኪያ ቢላዋው ላይ ፀሎት አድርሰው ለአንድ የሚባርክ የአገር ሽማግሌ በማሳለፍ ነው። ከዚያም በጉ ይባረካል። ሥጋው ተበልቶ ሽንጡ ከወጣ በኋላም ሽንጡ በሰው ተይዞ ለሟች እና ለገዳይ ወገን ተደራዳሪ መሪዎቹ ይቀርብላቸዋል። ከዚያ እንደገና በተባረከበት ቢላዋ ሽንጡን እራሳቸው እየቆረጡ ይቀምሳሉ። ቀጥሎም ተደራዳሪዎቹ እና የሟች እና የገዳይ ወገኖች ሁሉ እንዲቃመሱት ይደረጋል። የታረደው እንሰሳ የተባረከበት እና የሟች እና የገዳይ ወገኖች ሥጋ የተቋረጡበት አንድ ቢላዋም ከዚያ በኋላ ወንዝ ውስጥ ይጣላል። እቤት አይገባም። ቂም ተቆርጦበታልና።

የሚችና የገዳይ ወገኖች ሽንጥ ሥጋ ሲቋረጡ

ከሚች እና ከገዳይ ተደራዳሪዎች እና ከዘመዶቻቸው የተረፈው ሽንጥ ሥጋ እና ሌላው ብልት ሁሉ ደግሞ ተጠብሶ ለአገር ሽማግሌዎቹ እና በእርቅ ሥርዓቱ ላይ ለተገኙ ሁሉ ከእንጀራ፣ ከጠላ እና አረቄ ጋር ይቀርባል።

የእርድ ሥነ ሥርዓቱ አስፈላጊነት የሚታረደው እንስሳ መስዋዕት ይሆን ዘንድ ቅራኔም የሞተ መሆኑን ለማመልከት መሆኑ ሲገለጽ የሽንጥ ሥጋ መቁረጡም ተምሳሌትነቱ አያያዥ አገናኝ ስለሆነ ነው። ይኸውም የሽንጥ ሥጋ የሚገኘው ከአከርካሬ ግራና ቀኝ ከአንገት እስከ አኒሳ በወጥነት እንደመሆኑ ጉድኖችን አስተሳስሮ ስለሚይዝ ነው የሚል ምክንያት ይሰማል። በመሆኑም እርቅ ፈፃሚዎቹ በጋራ ተቋርጠው ሲቃመሱት ልዩነታቸውን ያጠፋል፣ ከፍተኛ መቀራረብ እና ፍቅር ባይኖር እንኳን ግራ እና ቀኝ ተስማምተው ይኖራሉ እርቅ ካፈረሱም ሽንጡ ተልጦ እንደወጣበት አከርካሬ መለመላ (እርቃን) ያስቀራል ተብሎ ስለሚታመን ነው።

በወይና ደጋ እና በቆላ አካባቢ ተደጋግሞ የሚታየው የሚች እና የገዳይ ወገኖች የሚፈፅሙት ጠመንጃ መራመድ፣ አፈር መጨበጥ፣ የሽንጥ ሥጋ መቋረጥ ሥርዓት ብዙ ጊዜ በደጋ አካባቢ በሚደረግ የደም እርቅ ሥነ-ሥርዓት ላይ እንደማይፈፀምም አቶ ሸዋይርጋ፣ አቶ ገብረወልድ እና አቶ መንግሥቱ ገልፀውልኛል። እንደነርሱ ገለፃ በደጋ የሚዘወተረው የደም እርቅ መሐላ ማስፈፀሚያ አርጥብ ሣር ማስነጨት እና መስቀል ማስጨበጥ ነው። መሐላውም "ይህን ውል ባፈርስ እንደ ሳሩ ይንጨኝ፣ ይበጥሰኝ፣ ያድርቀኝ፣ እንደመስቀሉም፣ ይጠቅጥቀኝ፣ ይበሳሳኝ" ወዘተ የሚል ነው።

እርጥብ ሣር በመንጨት መሐላ የሚፈፀመውም እርጥብ ሣር ከተነጨ በኋላ ልምላሜውን አጥቶ እንደሚደርቅ ሁሉ እርቁን ያፈረሰ ወገንም እርቁን ካፈረሰ እንዲህ እንዳሣሩ ሁሉም እኔም ልነጭ አለ-ዕድሜዬ ልመ-ት ልነቀል ለማለት ነው ይላሉ። (አቶ ሺፈራው፣ አቶ ሽቤ፣ አቶ ገብረወልድ፣ አቶ ሸዋይረጋ አቶ መንግስቱ።) ከአገር ሽማግሌዎቹ ገለፃ እንደተረዳሁት እርቅ ሲፈፀም መሐላው ምንም ይሁን ምን "የሸማግሌ ምሣ" የሚባለው ግን አይቀርም። የሽማግሌ ምሣ ወጪ በወይና ደጋ እና በቆላ አካባቢ እርቅ ጠያቂዎች ሽምግልና ሲጀመር በሚያሲይዙት የሽምግልና መጠየቂያ አርባ ብር ክፍያ እና ተሰብሳቢዎች በሚፈፅሙት የምግብ፣ የመጠጥ እና የገንዘብ መዋጮ ይሸፈናል። በደጋ የገዳይ ወገኖች የእርቅ መያዣ ገንዘብ አይሕፍሉም። በመሆኑም የአገር ሽማግሌ ምላ የሚዘጋጀው በገዳይ እና በሟች ወገኖች ትብብር እንዲሁም እርቁ በመፈፀሙ በተደሰቱ ወገኖች መዋጮ ነው።

ስለሆነም እርቁ ሲፈጸም ታራቂዎች እህል ውኃ "እንዲፋተቱ" ማለት እንዲቃመሱ ይደረጋል። የሚፋተቱት እህል ውኃም ሥልጣነ-ክህነት ባለው ቄስ "ፀሎተ-ቡራኬ" ይደረግበታል። የሽማግሌ ምላ የውለታ ወይም የከበሬታ መግለጫ የክብር ምልክት ሆኖ እንደሚወሰድ የተገላጋይ ወገኖችም አብሮ እህል ውኃ መቃመስ እንደ "ሥጋ ወደሙ" ማለትም ቁርባን እምነት ፍቅር መግለጫ የሚቆጠር መሆኑ ይነገራል። እንደ አገር ሽማግሌዎቹ እምነት እና እውቀት እህል ውኃ በጋራ የሚቀመሰውም በብዙ ምክንያቶች ሳቢያ እና ተምሳሌትነት ነው። አንዱ ምክንያት "ሰው የሚቆመው በእህል ውኃ" በመሆኑ ነው። "እንኑር" ለማለት። ሁለተኛው ተምሳሌት ሰው ከሞተ በኋላ ሀዘንተኞች መሪር ሀዘን አድርገው ሲመለሱ "የእንባ አድርቅ" እንደሚቃመሱት ሁሉ የደረሰውን ደም ያድርቅ ለማለትም ነው።

የአገር ሽማግሌዎችና በእርቅ ሥነ ሥርዓቱ የተገኙ ምግብ ሲፋተቱ።

በአጠቃላይ ሕዝቡ በዚህ ባህላዊ እርቅ ሥርዓት ማለትም የአባት /አገር፣ ወንዝ፣ አደር፣ ዕድር፣ "አዳ" ፣ ልማድ/ እያለ በሚጠራው ሕግ እና ደንብ መሠረት የደም ግጭቱን ይፈታል። ውሳኔውንም ያፀናል። ይህንን ሕግ አለመቀበልም "መልቲ፣ ወስላታ፣ ጋጠወጥ፣ ነውረኛ፣ ባለጌ፣ ወዘተ" ያሰኛል። ከቤተሰብ እና ከማኅበረሰቡም መገለልን ያስከትላል።

4.6. ድህረ- እርቅ

የሟች እና የገዳይ ወገኖች በባህላዊ መንገድ እርቅ ከፈፀሙ በኋላ የሚኖራቸው ግንኙነት እና መቀራረብ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ሞክሬያለሁ። ስለ ሟች እና ገዳይ ወገኖች ድህረ-እርቅ ግንኙነት ሁኔታ ያነሳሁባቸው አውራ የመረጃ ተባባሪዎቼም ሆኑ ሌሎቹ እንደገለፀልኝ እርቁ ሥራዬ ብሎ በደም ላለመፈላለግ ያህል ብቻ ነው የሚያገለግለው። ከዚያ ውጪ ግን በዕለትም ሆነ በቂም በቀል ሳቢያ የተከሰተ የደም ግጭት እርቅ ሆድ ለሆድ መግባባትን፣ አብሮ መብላት፣ መጠጣትን፣ ደቦ ወይም ጅጌ መጠራራትን፣ እና አብሮ መሥራትን፣ ሰንበቴ (ዕዋ) መጠጣትን፣ አዲስ ጋብቻ ለመመሥረት መተጫጨትን፣ አያስከትልም። ይልቁንም "የደም ቤት ነን፣ አበ-ደም ነን"፣ በመባባል ሁለቱም ወገኖች እራሳቸውን፣ ልጆቻቸውን፣ እንዲሁም ተወላጆቻቸውን፣ "በማስተንከር" ማለትም በማስጠናት በየፊናቸው ታቅበው መኖርን እንደሚመርጡ ተረድቻለሁ። ይህን ዓይነቱን ልማዳዊ ተአቅቦ አፍርሰው ከገዳይ ወገኖች ጋር የተለየ መቀራረብ እና ተዛምዶ ካሣዩ አሽመሩሩ እና ሐሜቱ "አይጣል" ማለትም አያድርስ እስከሚያሰኝ እንደሚወርድባቸው፣ ይህም ሲበዛ ደግሞ እደም አዙሪት ውስጥ ሊከታቸው እንደሚችል ነው የሚወጋው።

4.7. ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓቱ ወቅታዊ ሁኔታ

ቀደም ሲል እንደተመለከተው የላሎ-ማማ ምድር ወረዳን ሕዝብ ለግጭት የሚዳርጉት እና የሚያበቁት ምክንያቶች በርካታ ናቸው። ይሁንና ሁሉም የግጭት መንስኤዎች በተለያዬ ደረጃ በሚደረጉ የሽምግልና እና የዳኝነት ጥረቶች ካልተቀጨ ወይም ተጋጪዎቹ ግጭታቸውን ላለማባባስ "ልብ ካልገዙ" ማለትም ትዕግስት ካላደረጉ በስተቀር ሁሉም ዓይነት የግጭት መንስኤዎች እና ዓይነቶች ነፍስ እስከማጥፋት /ግድያ/ የማይሸጋገሩበት ሁኔታ እንደሌለ ከአገር ሽማግሌዎቹም ገለጻ ካካሄድኩትም ቅኝት እና ምልከታ መገንዘብ ችያለሁ።

ስለሆነም ላሎ-ማማ ውስጥ የማያጋድል የፀብ መንስኤ እና ዓይነት አይኖርም ማለት ይቻላል። ይሁንና ግጭቱ ደም መቃባትን ካስከተለ በኋላ ደግሞ መበቃቀልን በሚገታ መልኩ እንዲያርፍ እና እርቀ-ሰላም እንዲወርድ ማድረጊያው አንድ ብቸኛ ዘዴ እርቅ መሆኑ እርቅ ማድረጊያውም ተቋም ሽምግልና መሆኑ በእስካሁኑ ሀቲት ተመላክቷል።

ይሁን እንጂ ይህ የደም ማድረቂያ እርቀ-ሥርዓት መፈፀሚያ ሽምግልና በዘመናዊ የመንግሥት ሕግ ቅቡል እና ተካታች አይደለም። ለዚህም እውነትነት ቀደም ሲል የዳሰስነውን የኢትዮጵያ ሕጐች ተሞክሮ ማስታወስ፤ የአማራ ክልል የፀጥታ እና ደህንነት ቢሮ ህዳር 1996 "ለጐጥ የወንጀል መከላከል ኮሚቴዎች ለማወያያ የተዘጋጀ ጽሁፍ፤" እና ህዳር 1997 ዓ.ም "የግጭት አፈታት ሥርዓት የሥልጠና ሰነድ" እንዲሁም የላሎ-ማማ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት ታህሣሥ 1997 ዓ.ም "የሽምግልና አማራጭ የግጭትና የሙግት መፍቻ ሥርዓት አስፈላጊነትና የተከራካሪ ወገኖች ጉዳይ ከመደበኛ ፍርድ ቤት ሥርዓት ውጭ በእርቅ ለመጨረስ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች" ሰነዶችን ማስተዋል ይቻላል። ሁሉም ሰነዶች ግድያ እና መሰል ወንጀሎችን በሽምግልና አማካኝነት በእርቅ መፈጸም ገዳይ ቅጣት እንዲቀልለት፤ በቀል እንዲቆም ከማድረግ ማለፍ እንደሌለበት ያስረዳሉ። ከአገር ሽማግሌዎችም መካከል የደም እርቅ ውል ከልማድ የወረደ እንጂ በህግ ፊት ተቀባይነት እንደሌለው ጠቁመዋል።

የላሎ-ማማ ወረዳ ፍትህ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ንጉሴ በቀለ በ22/5/99 እና የላሎ-ማማ ምድር ወረዳ ፖሊስ አዛዥ ረዳት ኢንስፔክተር አህመድ መሀመድ በ24/5/99 የክልሉ መንግሥት ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ "የደም አድራቂ ኮሚቴዎችን" በወረዳው ውስጥ በሚገኙ ቀበሌዎች ለማቋቋም ከተገደደባቸው ምክንያቶች አንዱ በተለይ በወይና ደጋ እና በቆላ አካባቢዎች የነፍሰ-ገዳይ እና የሚች ወገኖች በባህላዊ መንገድ እየተሸማገሉ ገዳዮች ከአካባቢው እየለቀቁ እንዲሄዱ በማድረግ የህግ የበላይነትን የሚሸረሽር እና የሚቃረን ተግባር በመፈፀሙ መሆኑን ይገልፃሉ።

ባለሥልጣናቱ እንደሚሉት በልምድ ከሚሸመግሉት የአገር ሽማግሌዎች ይልቅ ሕዝቡ የመረጣቸው "የደም አድራቂ ኮሚቴዎች" ሕጉን አውቀው እና አስከብረው ቂም በቀልን ብቻ ለማስቀረት መሸምገል እንዳለባቸው ነገር ግን ገዳይ አገር ሰቶ እንዲጠፋ ማድረግ እንደሌለባቸው ትምህርት የተሰጣቸው ናቸው።

መንግሥት ባዋቀረው የደም አድራቂ ኮሚቴ ውስጥ ካነጋገርኳቸው የአገር ሽማግሌዎች መካከል ተመርጠው የገቡ ስለመኖራቸው ጠይቄም አቶ ሺፈራው ደምሴ በ9/5/99 ብቻ በቀበሌያቸው የተመረጡ መሆናቸውን ገልፀውልኛል። ስለአሠራራቸው እንዲነግሩኝ አንስቼባቸው ቀደም ሲል ይሰሩበት የነበረው" ገዳይ ከቀጭኔ እና ከሞፈር ውኃ ማዶ ሄዶ ይኑር" ውሳኔ "የህገ-ወጥ ማበራከቻ" ተብሎ መወገዙን እና በዚህም እንዳያስማሙ ሴሚናር መሰጠታቸውን፤ ነገር ግን ገዳይ እሺ ካለ ከሚች ወገኖች ጋር እምቢ ካለም የገዳይ እና የሚች ወገኖችን ብቻ እንዳይበቃቀሉ አስማሙ መባላቸውን ገልፀውልኛል። በዚህ መንገድ ያስማማችሁት አለወይ? ብያቸውም እንዲያውም ሕዝቡ በዚህ ኮሚቴ ውስጥ ከገቡ ወዲህ ከደም በመለስ ላለ ችግሩ እንጂ ስለደም እርቅ አንስቶባቸው እንደማያውቅ ነግረውኛ

ል። ግድያ የለም ማለት ነው? ብያቸው "አለ ግን ከተመረጥኩ ወዲህ እንደ ዳኛ እያዩኝ ነው መሰል ትተውኛል፤ እኔም አርፌያለሁ" በማለት መልሰውልኛል።

በደም አድራቂ ኮሚቴዎቹ በኩል የተደረጉ እና የሚደረጉ እርቆች ምን ይመስላሉ? ያልኳቸው ሌሎች የአገር ሽማግሌዎች እና ነዋሪዎችም "እዬ የለም!" በማለት የደም ችግር ያለበት ሰው ተሸለልክለም ቢሆን የሚሄደው ወደ ነባሮቹ የአገር ሽማግሌዎች መሆኑን ይጠቁማሉ። ደም የተቃቡ ወገኖች ለምን በየአትራቢያቸው ባሉ የደም አድራቂ ኮሚቴዎች በኩል እርቅ አይፈፅሙም ያልኳቸው አንዳንድ ሰዎችም በጥቅሉ ወደነባሮቹ የአገር ሽማግሌዎች የማዘንበል ሁኔታ እንዳለ በመግለፅ ምክንያቱን ከመዘርዘር ተቆጥበዋል።

ከላይ እንደተዘረዘረውም የላሎ-ማማ ሕዝብ በ"ገደለ ተነቀለ" ብሂሉ መሠረት በዋነኛ ነት ገዳይን ከቀጭኔ እና ከሞፈር ውኃ ማዶ ሄዶ እንዲኖር በማድረግ እርቁን የሚያፀናበትን ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት ዘመናዊው ህግ የሚከለክለው መሆኑን መረዳት ይቻለናል።

5. ማጠቃለያ

በዚህ "ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ" በሚል ርዕስ በቀረበ ጥናት እንደተመለከተው ግጭቶች በልዩ ልዩ ምክንያቶች እንደሚከሰቱ ታይቷል። የግጭቶቹም ደረጃ የተለያዩ ነው። የተለያዩ ደረጃ ያላቸው ግጭቶችም በተለያዩ ዘዴዎች ሥልቶች እና ተቋማት የሚፈቱ መሆኑ ተወስቷል። በጥናቱ እንደታየውም ግጭቶች በተለያዩ ምክንያቶች ይቀሰቀሳሉ። የግጭት መንስኤዎቹን ከግጭት መከሰቻ ሰበብ ምክንያቶች ወይም ንድፈ-ሐሳቦች አንጻር ስናያቸው እና ስናጠቃልላቸውም ሕዝቡ እርስ በርሱ የሚጋጨው በአስተሳሰብ አመለካከት እና ተግባቦት (communication) አለመጣጣም፤ በእምነት ማጣት እና እምነት ማጉደል፤ በሥራ ወይም በሙያ ልዩነት፣ ማንነት፣ በሀብት ምንጭ ውሱንነት ወይም እጥረት (limited resource) እንዲሁም በመልካም አስተዳደር እጦት መንደል ምክንያት ግጭቶች እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

ከላይ የተጠቀሱትን በተለያዩ ሰበቦች የሚቀሰቀሱ ልዩ ልዩ ግጭቶችም የላሎ-ማማ ሕዝብ በመኖር ሂደት ካካበተው ልምድ በመነሳት መለስተኛ እና ከባድ እያለ ይፈርጃቸዋል። እንደየደረጃቸውም የመፍትሔ ማስገኛ ወይም መስጫ ባህላዊ ሥልቶችን የመጠቀም ልምድ እንዳለው ተወስቷል።

በባህላዊ መንገድ ግጭቶች መፍትሄ ከሚያገኙባቸው መካከልም የአባወራ እና የባለቤት (ሚስት)፣ የአጐት፣ የአክስት፣ የቡና የሰንበቴ (ዕዋ) ማኅበር፣ የዕድር፣ የንሰሐ አባት፣ የአካባቢ ሽማግሌ እና የአገር ሽማግሌ ሽምግልና እና ምክክር ዋነኞቹ እንደሆኑ ተገልጿል። በተለይም የጥናቱ ዐቢይ ትኩረት የሆነውን ደመኝነት ወይም የደም ግጭት ለመፍታትም የአገር ሽማግሌዎችን ሽምግልና የመጠቀም ባህል መኖሩ ታይቷል። የአገር ሽማግሌዎቹም የሚመረጡት እና የሚሰየሙት ሕዝቡ ሲወርድ ሲዋረድ ወደ ላይ ለሚቆጠር ቤተሰባቸው እና ለነርሱም በሚሰጠው ቤተ-ጨዋነት እንዲሁም ማኅበራዊ ከበሬታ፣ ሐቀኝነት (ታማኝነት)፣ የአስታራቂነት ችሎታ (ጥበብ)፣ ታሳቢነት መሠረት መሆኑ ተስተውሏል።

የአገር ሽማግሌ ሽምግልናውም በንድፈ ሐሳብ የተነሱትን እና የታዩትን የአደራዳሪ ሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት መሻት እና ተነጋግሮ ችግርን የመፍታት ጥረት ማለትም የመሸማገል ሂደት /mediation/፣ ለመደራደር መስማማት እና ዋስትና መስጠት /negotiation/፣ የጋራ ዳኛ ዳኝነት መፈለግ /arbitration/ ወይም የዘመድ ዳኛ ማቆም እና እርቅ /reconciliation/ ማድረግ የሚሉትን ያዳቀለ እና ያካተተ ነው።

የደመኝነት ወይም የደም ግጭት እርቅ ጥያቄ እና ጥሪ የሚደረገውም ብዙውን ጊዜ በገዳይ ወገኖች እንደሆነ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ እንደ ግድያው መንስኤ፤ የገዳዩ ወይም የሟቹ ማንነት ማለትም ማኅበራዊ ደረጃ የእርቅ ጥሪው በተለያዩ ወገኖች ማለትም በገዳዩ በራሱ፤ በወገኖቹ፣ በአገር ሽማግሌዎች፣ በኃይማኖት አባቶች፣ በሟች ወገኖች ወይም በተጠቀሱት ጥምረት የሚጠየቅበት ሁኔታ እንዳለ ታይቷል።

የእርቅ ጥያቄው ወይም ጥሪው ተቀባይነት ያገኝ ዘንድም የአመላለድ ጥበብን፣ ተስፋ አለመቁረጥን፣ እና ልዩ ልዩ አስገዳጅ ሁኔታዎችን መጠቀምን እንደሚጠይቅ፤ ይኸውም በህቡዕ (በድብቅ) ወይም በሚስጥር እና በይፋ (በገሃድ) እንደሚደረግ ተወስቷል። የእርቅ ጥያቄው ቀርቦ ምልጃም ተደርጐ የእርቅ ድርድር ለማድረግ የሚቻለውም ተጋጪዎቹ ወገኖች በሰላም ለመስማማት ዋስትና እንዲሰጡ በማድረግ መሆኑን ድርድሩም የሚቀጥለው ምልጃው በተጀመረበት አኳኋን በቀን ወይም በሌሊት ወይም በምስጢር ወይም በገሀድ በተለያዩ ሥፍራ ማለትም በደጋ ብዙውን ጊዜ በበረሃ፣ በተራራ እና በቤተክርስቲያን፤ በወይና ደጋ እና በቆላ፣ በበረሃ፣ በጫካ እና በወንዝ መሆኑ ተገልጿል።

ድርድሩ የሚካሄደውም በራሱ በገዳይ እና በሟች ወገኖች መካከል አይደለም። ይልቁንም የደም "እኩሌታ" ማለት ወደር እስከሌለ ድረስ ድርድሩ የሚደረገው በገዳይ እና በሟች የቅርብ ቤተሰቦች አማካይነት መሆኑ ታይቷል። በጥናቱ እንደታየው ገዳይ ሟችን በየትኛውም ዓይነት የፀብ መንስኤ ምክንያት ተነሳስቶ ቢገድለው ስምምነት ላይ የሚደረሰው ለገዳይ አገር "በመቆረር" ማለት በመወሰን እንደሆነም ተወስቷል። ምክንያቱም በባህላዊ የእርቅ ሥርዓተ-ደንቡ ማለትም፤ "አዳ"፣ ዕድር፣ የወንዝ ህግ፣ የአባት አደር፣ ልማድ መሠረት ገዳይ ከገደለበት ላሎ-ማማ ምድርም ሆነ ከጠቅላላው መንዝ ለቆ የመሄድ ግዴታ አለበትና። ከዚህ ውጪ ገዳይ በአካባቢው እንዲኖር የሚወሰንበት አጋጣሚ እጅግ አነስተኛ ነው። ስለሆነም ገዳይ ከሞፈር ውኃ እና ከቀጭኔ ወንዞች ማዶ መሄድ አለበት። ከዚህ ውጭ "ወጅ" ማለትም የደም ካሣ መቁረጥም መብላትም እጅግ በጣም አልፎ አልፎ በልዩ ልዩ ታሳቢ ችግሮች ምክንያት ማስማሚያ እንዲሆን ከመደረጉ በስተቀር የተለመደ አይደለም። የላሎ-ማማ ሰው "ወጅ" ማለትም የደም ካሣን ቀርቶ ለሌላም መለስተኛ ግጭት "ለደንቡ" በሚል በሽማግሌ የሚቆረጥ የካሣ ገንዘብን አይበላም። ካሣ መብላትም የተነወረ ተግባር ነው። የእርቅ ማዕኛ መሐላ መፈፀሚያ ትዕምርቱ (symbol) እና የእርቅ ማዕኛ መሐላ ሥርዓቱ (ritual) እንደየአካባቢው የተለያዩ ነው። በደጋ ብዙውን ጊዜ ተጋላጮቹ በራሳቸው ፈቃድ የሚፈፅሙት መሐላ እርጥብ ሣር መንጨት ነው። ይኸውም የፈቃድ መሐላ እንደገና መስቀል በመጨበጥ እና መሐላውን ከሚያስፈጽመው ሥልጣነ-ክህነት ያለው ቄስ የግዝት ቃል በመቀበል ይደመደማል።

በወይና ደጋ እና በቆላ አካባቢ ደግሞ ተገላጮቹ ጥይት የጐረሱ ሦስት ጠመንጃዎችን በመሬመድ፤ አፈር በመጨበጥ፤ እና የጨበጡትንም አፈር በመረጡት ቤተክርስቲያን በመቅበር፤ እና ሽንጥ ሥጋ በመቋረጥ እርቁን ያፀድቃሉ። አንዳንድ ጊዜም ደግሞ እንደ ደጋው ሁሉ የግዘት ቃል በመቀበል እና መስቀል በመጨበጥ ልባቸው ለበቀል ቦታ እንደማይኖረው ያረጋግጣሉ።

ይህ የላሎ-ማማ ሕዝብ የደም ግጭትን የሚገታበት ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት አሁን ያለበት ሁኔታ ሲታይም በደጋ አካባቢ ጥቅም ላይ የመዋሉ ሁኔታ እና ደረጃ እየቀነሰ በወይና ደጋ እና በቆላ ግን አሁንም ተዘውትሮ የሚፈፀም ማለትም አገልግሎት ላይ የሚውል መሆኑ ተወስቷል፤ ተገልጿል።

ከዚህ ምልከታ በመነሳትም የላሎ-ማማ ሕዝብ ቂም ማድረቂያ የሆነው ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት መጻኤ ሁኔታ አደጋ እንደተጋረጠበት መገመት እና መተንበይ ይቻላል። ምክንያቱም ይህን ባህላዊ ሥርዓት ዘመናዊው ህግ እየተግረረው መሆኑ በጥናቱ ታይቷልና ነው።

የተጠቀሱ ምንጮች

መጽሐፍ ቅዱስ : የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፤ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ.ማተሚያ ቤት 1962::

መሉጌታ ነጋሣ፤ በአድኣ ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሴራጨፌ ከግጭት አፈታት አንጻር፤ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል 1997::

ማህተመ ሥላሴ ወልደመስቀል፤ ጎልቄ ትውልድ ዘ፡ንጉሥ ሣህለሥላሴ፤ አዲስ አበባ ቀ.ኃ.ሥ. ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ጥናት ጥናት ድርጅት 1965::

_____ ፤የኢትዮጵያ ባህል ጥናት ቡልጋ፤ አዲስ አበባ፤አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1960::

ሰለሞን ሣህሌ፤ ባህላዊ የግጭት አፈታት በሲቡ ሴሬ ኦሮሞዎች የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል 1998::

በላይ ግደይ አምህ፤ አክሱም፤ አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1995::

ተመስገን ምንዋጋው፤ሀገረሰባዊ የግጭት መፍትሔ ሥርዓት በዶኮ-ጋሞ፤ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል 1998::

ተክለሐዋርያት ተክለማርያም ፤ ኦቶባዮግራፊ (የሕይወቴ ታሪክ) አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ኘሬስ 1998::

ተክለፃድቅ መኩሪያ፤ አፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት፤አዲስ አበባ፤ቦሌ ማተሚያ ቤት 1982::

_____ ፤ የግራኝ አህመድ ወረራ፤ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ. ማተሚያ ቤት 1966::

ታደገኝ መርን፤ በመንዝ ላሎ- ምድር ወረዳ የሚገኙ ውቃቢዎች ልዩ ልዩ ገፅታዎች እና የፍርድ ክዋኔ፤ የቢ.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል 1992::

ነፃነት መኮንን ፤ አበጋር ባህላዊ የግጭት አፈታት በተሁለደሬ ወረዳ፤ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል 1998::

ILS LIBRARY

አየለ ፍቅሬ፤ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በባህርዳር ነገዴ (ወይጦ) ጎበረተሰብ፤ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል 1998።

ወንድወሰን አውላቸው፤ የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ አስተዳደርና የግጭት አፈታት፤ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል 1998።

የላሎ-ማማ ምድር ፍትህ ጽህፈት ቤት፤ የሽምግልና አማራጭ የግጭትና የሙግት መፍቻ ሥርዓት አስፈላጊነትና የተከራከሪ ወገኖች ከመደበኛ ፍርድ ሥርዓት ውጪ በእርቅ ለመጨረስ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፤ ሞላሌ፤ ያልታተመ ታህሣሥ 1997።

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስተዳደርና ፀጥታ ቢሮ፤ ለጉጥ የወንጀል መከላከል ኮሚቴዎች ለማወያያ የተዘጋጀ ጽሑፍ፤ ባህር ዳር ህዳር 1997።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፤ አማርኛ መዝገበ ቃላት፤ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1993።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት፤ አዲስ አበባ 1987።

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፤ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ.ማተሚያ ቤት 1949።

የወንጀል ሕግ፤ አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት 1997።

የፍትሐ-ብሔር ህግ፤ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ.ማተሚያ ቤት 1952።

የፍትሐ-ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ፤ አዲስ አበባ፤ ብርኃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ. ማተሚያ ቤት 1958።

ይልማ ተፈሪ፤ የሽምግልና እርቅ ሥርዓት በወላይታ፤ የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል 1998።

ዮሴፍ ጌትነት፤ባህላዊ እርቅ በምሥራቅ ጉጃም ዞን ደባይ ጥላትግን ወረዳ፤ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል 1998።

ደስታ ተክለወልድ፤ዐዲስ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት፤ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1962።

ዳኛቸው መርቁ፤ አደፍርስ፤ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት 1962::

ፊቃደ አዘዘ፤ የሥነ-ቃል መምሪያ፤ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መጻሕፍት ማዕከል ሁለተኛ ዕትም 1993::

ፍትሐ-ነገሥት፤ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ.ማተሚያ ቤት 1958::

ጳውሎስ ኞኞ፤ አጤ ቴዎድሮስ፤ አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ቤት 1985::

Anderson J. Kuehn M. and McKinney B. **Communication: Skills for Surviving Conflicts at Work**. New Jersey: Hampton Press 1999.

Asaffa, Tolera. **Ethnic Integration and Conflict: The Case of Indigenous Oromo and the Amhara Settlers in Aaroo, Addis Alem, Kiramu area, North East Wollega.** M.A. Thesis A.A.U., 1995.

Assefa Jalta. **Oromia and Ethipia Satate Formation and Ethno-national Conflict 1862-1992**. London: Lonne Rienner Publishers

Aspen,Harald **Spirits, Mediums, and the Human Words, The Amhara Peasants of the North Ethiopian Highlands and their Traditions of knowledge**. University of Trondheim, P.H.D. Thesis July 1994.

Augsburger, David. **Conflict Mediation Across Cultures**. London West Minister, John Tenox Press 1992.

Avruch, Kevin. **Culture and Conflict Resolution**. Washington: United States Institute of Peace, 4th ed. 2004.

Bartos, J. and Wher: **Using Conflict Theory.** UK: Cambridge University Press, 2002.

Berihun Mebrate. **Spontaneous Settlement and Inter-Ethnic Relations in Matekal, North West Ethiopia.** M.A. Thesis A.A.U.,1996.

Boulding , Kenneth. **Conflict and Defense.** New York Harper and Row, Publishers, 1962.

Coser, Lewis. **Conflict, Social Aspect** International Encyclopedia of Social Sciences Vol.3. 232-236. The Macmillan Company and Free Press, 1968.

Eitzen, D.S and Zinn, M.B. **In Conflict and Order:** Understanding Society. Massachusetts, Allyn and Bacon, the , 4th ed. 1998.

Fekade, Azeze. **Some Studies On Traditional and Related Methods of Conflict Resolution**. Addis Ababa: Selected and Compiled 2004.

Fisher, Ronald. **Social Psychology.** An Applied Approach. New York: St. Martin's Press, 1982.

Gray, Jerry. **Organizational Behavior and Applications.** The University of Manitoba Charles. Of Merrill Publishing Co.3rd ed 1984.

Havilland William. **Cultural Anthropology**. Sandiego: Harcourt Bruce Jovanovich, 7th ed. 1997.

Http ://en Wiki Pedia Org/wiki/ **Social conflict theory**.

International Bible Students Association. **Insight on the Scriptures.** Vol.2 New York: Brooklyn 1998.

Kelemework, Tafere. **Indigenous Institutions of Conflict Resolution Among the Aba'ala, Afar & North Eastern Ethiopia**. M.A. thesis, A.A.U. 2000

Kiros, Habteselassie and Mazengia Dina. **Ethiopia: A Short Illustrated History**. Addis Ababa: Berhanena Selam, Haileselassie I Printing Press, 1972.

Kottak, Philip. **Cultural Anthropology.** New York McGraw- Hill inc, 5th ed. 1991.

Leslau, Wolf. **English-Amharic Context Dictionary.** Otto Harrissowitz Wiesbaden, 1973.

Levine, Donald. **Wax and Gold: Tradition and Innovation in Ethiopian Culture.** Chicago University of Chicago Press 5th ed. 1972.

Lulofs, Roxane and Cahn, Dudley. **Conflict from Theory to Action.** New York: Allyn and Bacon 2nd ed, 2000.

New Encyclopedia Britanica Vol. 27. Chicago; Macropaedia, 15th ed. 1997.

Oxford Advanced Learners Dictionary. Nairobi. Oxford University Press, 6th ed. 2000.

Pearce, Barnett and Little, John, Stephen. **Moral Conflict: When Social Worlds Collide.** California: Sage Publications Inc, 1997.

Reminick, Ronald. **The Manze Amhara of Ethiopia: A study of Authority, Masculinity And Sociality.** P.H.D Thesis. Chicago University, 1973.

Seymour, Smith. **The Dictionary of Anthropology.** London: The Macmillan Press 1986.

Yohannes, Birhanu. **Conflict and Conflict Resolution Among the People of Chihera.** M.A Thesis A.A.U. 1998.

አባሪ አንድ

ቁልፍ /አውራ/ የመረጃ ተባባሪዎች ዝርዝር

ተ.ቁ	ሙሉ ስም	ዕድሜ	ቀን	ቦታ	አስተያየት
1.	አቶ መንግስቱ አማረ	72	18/5/99	አመጓ	የአገር ሽማግሌ
2.	ቄስ ማሞ ፀደቀ	56	6-8/5/99	ገበጣ ድንጋይ	"
3.	መቶ አለቃ ሸበ ጣልባቸው	80	18/5/99	ሞላሌ	"
4.	አቶ ሸዋይረጋ አስፋው	70	11-13/5/99	አንገዋ	"
5.	አቶ ሺፈራው ደምሴ	76	9/5/99	ወምሶ	"
6.	አቶ ቀጥይበሉ አሳምነው	76	17/5/99	ወገሬ	"
7.	አቶ ተሰማ ገዙ	65	18/5/99	ሞላሌ	ሽማግሌ
8.	አቶ ኃይሉ እሸቱ	35	22/5/99	ሞላሌ	የግብርና ባለሙያ
9.	አቶ ንጉሴ በቀለ	40	22/5/99	ሞላሌ	የፍትህ ጽ/ቤት ኃላፊ
10.	ረዳት ኢንስፔክተር አህመድ መሐመድ	45	24/5/99	ሞላሌ	ፖሊስ አዛዥ
11.	አቶ እንግዳ አልታዬ	70	13/5/99	አንገዋ	የአገር ሽማግሌ
12.	ወ/ሮ ወለተዮሐንስ ወ/ጊዮርጊስ	65	12/5/99	አንገዋ	የቤት እመቤት
13.	አባ ዘውዴ ደምድም	78	13/5/99	አንገዋ	የአገር ሽማግሌ
14.	አቶ ደምሰው ተምትሚ	30	22/5/99	ሞላሌ	የትምህርት ጽ/ቤት ም/ኃላፊ
15.	አቶ ደምሴ ወልደፃድቅ	79	9/5/99	ሞላሌ	የአገር ሽማግሌ
16.	አቶ ደጀጠና መንግሥቱ	70	6-8/5/99	ጭማ ገረገራ	የአገር ሽማግሌ
17.	አቶ ገብረሕይወት አሳምነው	79	9/5/99	ሞላሌ	የአገር ሽማግሌ
18.	አቶ ገብረወልድ ገብረጻድቅ	73	18/5/99	ዳሳ	የአገር ሽማግሌ
19.	አቶ ግርማ ይታፈር	47	24/5/99	ሞላሌ	የወረዳ አፈ. ጉባኤ
20.	አቶ ፀጋዬ ሰይድ	35	22/5/99	ሞላሌ	የጤና ጽ/ቤት ኃላፊ

የአገር ሽማግሌዎች ማንነት መግለጫ

አቶ መንግሥቱ አማረ በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ ውስጥ ስማቸው ጉልቶ የሚጠራ በኑሮአቸው መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሰው ናቸው። "ከትልቅ ቤተሰብ የተወለዱ ትልቅ ሰው" መሆናቸውም ይነገራል። ደርግ ሥልጣን እንደያዘ አገር ያውሉ ዘንድ የወረዳው ገበሬዎች ማኅበር ሲቀመንበር ሆነው ተመርጠዋል። በቅንነት አገልግለውም ስማቸው ሳይሰበር እንደወረዱ ይወጋላቸዋል። ሕዝቡ የትውልዳቸውን ቤተ-ጨዋነት እና የርሳቸውንም የአገር ሽማግሌነት ችሎታ አድምቆ ይተርክላቸዋል። ቀላል እና ከባድ ግጭቶችን በእመን እና አካባቢው እንዲሁም ራቅ ባሉ አካባቢዎች እየተገኙ የሚያማልዱ እና የሚሸመግሉም ናቸው።

ቁስ ማሞ ፀደቀን በደንገዜ እና አካባቢው የማያውቃቸው የለም። ጠና ያሉ ሰዎች "የልጅ አዋቂ" ይሏቸዋል። በእግር በፈረስ ተፈልገው ግጭት የሚፈቱ፣ የነገር ሐኪም መሆናቸውም ይወራላቸዋል። አሳቸው የተገኙበት ሽምግልናም ሳድሮ እንደማያውቅ፣ ግጭት የመፍታት ገዳቸውም መልካም እንደሆነ ይነገርላቸዋል። በኑሮአቸውም በአካባቢው ሀብታም የሚሰኙ ሰው ናቸው። የአገር ሽማግሌ ሆነው ሲሰሩም አንድ አሥርት አስቆጥረዋል። የሽምግልናውን ዕውቀት የቀሰሙትም ገና በለጋነታቸው ከአባታቸው መሆኑን እራሳቸው አጫውተውኛል።

መቶ አለቃ ሸቤ ጣልባቸው ላሎ-ማማ ምድር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው መንዝም ስማቸው ገኖ ይጠራል። መቶ አለቅነቱ የነጭ ለባሽነት ነው። ከበድ ያለ ግጭት ሲፈጠር "ለመቶ አለቃ" ይነገራቸው የማይል የለም ይባላል። ስለሳቸው የሚያውቁ ሰዎች እንደነገሩኝ ለችግር ፈጥኖ ደራሽ፣ ትጉ፣ ለሰው አዛኝ እና ልጨኛ የሚባሉ ናቸው። እጅግ ሻል ያለ ህይወት እንደሚመሩም ይነገርላቸዋል።

አቶ ሸዋይር ጋ አስፋው በአካባቢያቸው "አይቆረቁሬ፣ ቅመሙ" ይባላሉ። ከሃያ ዓመት በላይ በአገር ሽማግሌነት አገልግለዋል። ስለሳቸው ማንነት የጠየቅኋቸው ሁሉ የእሳቸውን የነገር ብልት አዋቂነት፣ የንግግር ችሎታ፣ የማግባባት ጥበብ፣ አውግተው አይጠግቡም። እሳቸው ያልተገኙበት ሽምግልናም እንደ ጥብቅ ሽምግልና አይቆጠርም ይባላል። ክርክር ማለትም ቁም ነገራም ናቸው በሚል ሕዝቡ ለአማላጅነት፣ ለአስታራቂነት አጥብቆ እንደሚፈልጋቸውም ይነገራል። በአካባቢያቸው ሕዝብ ዘንድ ሀብታም ተብለው ይፈረጃሉ።

አቶ ሽፈራው ደምሴ ከሩብ ምዕተ-ዓመት በላይ የአገር ሽማግሌ ናቸው።"ከትልቅ ሰው ዘርም" ይወለዳሉ። በዚሁም የተነሳ በአሜ ኃይለሥላሴ ዘመነ-መንግሥት ለሕዝብ መማክርት

ጉባኤ ተወዳድረው ነበር። የሞላሌ ጤና ጣቢያ ግምጃ ቤትም ነበሩ። በክተማም በገጠርም ስማቸው የገነነ ነው። ከባድ ግጭትን ለመሸምገል ከሚታጨት የወረዳው ዕውቅ የአገር ሽማግሌዎችም አንዱ ናቸው። "ነገር ይሰምርላቸዋልም" ይባላል። ዛሬም የወሎ እና አካባቢው የደም አድራቂ ኮሚቴ ሰብሳቢ ናቸው። በኑሮአቸውም የመንግሥት ጡረተኛ እና አሳራሽ ሲሆኑ ከበርቴ ከሚባሉት መካከልም ይፈረጃሉ።

አቶ ቀጥይበሉ አሳምነው ላሎ-ማማ ምድር ውስጥ እጅግ ስመ ጥር ናቸው።"እያ አለስልሲ፣ ወጊሻው" ይባላሉ። የሻከረ፣ የገረረ ነገር በማለዘብ ይታወቃሉ። ከሩብ ምዕተ-ዓመት በላይ የባልና ሚስት ግጭትን፣ ከባድ ድብደባን፣ የታላላቅ ሰዎችን አለመግባባት፣ የደም ግጭትን፣ ሲሸመግሉ ኖረዋል። ደጃቸውም በተለይ በበዓላት ቀን ገላግሉኝ ባዮች ስለሚበዙበት "ከድጎ ቤተክርስቲያን" የበለጠ ይደምቃል ይባላል። በኑሮአቸው መካከለኛ ህይወትን ይመራሉ።

አቶ ተሰማ ዝቁን የሞላሌ ከተማ እና አካባቢው ነዋሪ ከልጅ እስከ አዋቂ ማለት ይቻላል ሁሉም ያውቃቸዋል። እጅግ ተግባቢ፣ ሰው አክባሪም መሆናቸውም ይነገራል። በመሆኑም ላለፉት አሥራ አምስት ዓመታት ሕዝቡ ለፀብ እና ግጭቶቹ አብራጅነት በሽምግልና ይቀመጡለት ዘንድ አጥብቆ የሚፈልጋቸው፣ ባለፀጋ የሚሰኙ ሰው መሆናቸው ይወጋላቸዋል።

አቶ እንግዳ አልታዬ በአካባቢያቸው መካከለኛ ህይወት የሚመሩ የአገር ሽማግሌ ናቸው። የሚከበሩት ትንሽ ትልቁን በዕኩል ዓይን የሚያዩ፣ የሰው ችግር የሚገባቸው፣ በሽምግልና ላይ ተቀምጠው ነገሮችን በምሳሌ አስደግፈው በመግለፅ ችሎታቸው እና ተጋጪዎችን በማግባባት ችሎታቸው መሆኑ ሲነገር፣ የሚፈሩት ደግሞ ለሽምግልና ያስቸገረን ሰው ስያሜ ማለትም ዘፈን የሚያወጡበት በመሆናቸው እንደሆነ ይገለፃል። ከሃያ ዓመት በላይም በአገር ሽማግሌነት ሰርተዋል።

ወ/ሮ ወለተዮሐንስ ወ/ጊዮርጊስ በአንገዋ እና በዙሪያው እጅ ሰፊ፣ ምዕመን ስለመሆናቸው በስፋት ይወራላቸዋል። የአካባቢያቸውን ባህልም ጠንቅቀው ያውቃሉ። ብልህነት እና ተሰሚነት እንዳላቸውም ይነገርላቸዋል። ከአካባቢያቸውም የተሻለ ኑሮ የሚመሩ ሴት ናቸው።

አባ ዘውዴ ደምድም እንደ ቤተ-ክህነት ሊቅ እና መነኩሴ ብቻ ሳይሆን እንደ ሞገደኛ የሐቅ ጠበቃም የሚቆጠሩ ናቸው። በመሆኑም በነገሬ ላይ "አባ ይግቡበት" የማይል የለም ነው የሚባለው። በሽምግልና ተቀምጠው በሚያመነጩት የማስማሚያ ሐሳብ እና በሚሰጡት የመክፈቻ እና የመዝጊያ ፀሎት እና ቡራኬም እጅግ የተከበሩ ናቸው።

አቶ ደምሴ ወልደዓድቅ ከልጅነታቸው ጀምሮ ነገር የበሉ፣ እንኳን የሰው "የዝንብ ጠንጋራ" የሚለዩ ብልህ ሰው መሆናቸው ይነገርላቸዋል። ዕድሜያቸውን ያሳለፉት እዚያው ላሎ-ማማ ምድር ርዕሰ ከተማ ሞላሌ በፍርድ ቤት ሥራ ነው። የወረዳው ፍርድ ቤት ዳኛም ነበሩ። የአካባቢው ተወላጅ እንደመሆናቸው ለከባድ ግጭት ከዳኝነት ይልቅ ሽምግልናን አበክረው የሚደግፉ፣ ተጋጪዎችን በመገሰፅ፣ ሽማግሌዎችን በማማረጥ እና ምክርም በመስጠት የታወቁ ሰው እንደነበሩ ይወሳላቸዋል። ዛሬም እሳቸው ሐሳብ የማይጠየቁበት የከባድ ግጭት ሽምግልና እንደሌለ ይነገራል።

አቶ ደጀጠና መንግሥቱ ከሃያ ዓመት በላይ በአገር ሽማግሌነት ሠርተዋል። ሕዝቡ "በነገሬ ይግባበት" እያለ የሚጋብዛቸው የቤታቸውን እንጀራ እንኳን በወጉ አያውቁም የሚባልላቸው ዓይነት የአገር ሽማግሌ ናቸው። በደንገዜ እና በቆላማው ላሎ-ምድር የእሳቸውን የሽምግልና ችሎታ የማያውቅ ደጃቸውን ያልረገጠ ተገላጋይ እንደሌለም ይወጋል። የቤተሰባቸውንም ህይወት መካከለኛ ሊባል በሚችል ሀብት የሚመሩ ስለመሆናቸው ይነገራል።

አቶ ገብረሕይወት አሳምነው በዘመናዊም ሆነ በባህላዊ አስተዳደር ዕውቀታቸው የተመሰገኑ ሰው ናቸው። በተለይ የመንዝ ሰው ደም የሚቃባበትን፣ ሰላምም የሚወርድበትን መንገድ ሁሉ ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ መሆናቸውን ከአብሮ ቆይታዬ ተረድቻለሁ። እሣቸው እንደነገሩኝ ለሽምግልና የሚቀመጡት "ነገር የገባውን ሰው አይተው ነው። ለእነ ዱላ ዳዊቱ" ማለት ከስህተታቸው ለማይፀፀቱ ሰዎች ሽምግልና አይቀመጡም። ሕይወታቸውን የሚመሩት ከመንግሥት በሚገኝ የጡረታ ገንዘብ ነው።

አቶ ገብረወልድ ገ/ዓድቅ ላሎ ማማ ምድር ውስጥ ብቻ ሣይሆን ከዚያም በላይ ስማቸው የዘለቀ የአገር ሽማግሌ ናቸው። ሕዝቡ እንደሚያወጋው ከላይ የወረደ ቤተ-ጨዋነት የረበበባቸው ሰው ናቸው። በኑሮአቸውም ሃብታም ከሚባሉት ይፈረጃሉ። በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ-መንግሥት ምክትል ወረዳ ገዢ ነበሩ። የአገር ሽምግልናን ዕውቀት የቀሰሙት ልጅ ሆነው አባታቸው ሽምግልና የተቀመጡበትን ጉዳይ ይፅፉ ከነበረበት ጊዜ አንስቶ መሆኑን እራሳቸው ነግረውኛል። ዛሬም ሕዝቡ "እንደፈጣሪ" የሚያከብራቸው ሰው ናቸው። ለገላጋይ ያስቸገሩ እንኳን ሳይቀሩ "እምቢ ካላችሁን ለአቶ ገብረወልድ እንነግራለን" ከተባሉ "አይ እሳቸው አይስሙብን፣ እሳቸው ለባሰ ችግራችን ይሆኑናል ለአሁኑ እናንተው ትበቁናላችሁ ብለው ይለዝባሉ" ይባላል።

ማረጋገጫ

እኔ ዓለሙ ካሣዬ ከፊለው የኢ.ኢ.ዩ. ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ተማሪ ይህ ያቀረብኩት ጥናት የራሴ መሆኑን የተጠቀምኩባቸው ተዛማጅ ጽሑፎች እና የመረጃ ምንጮችም በአግባቡ የተጠቀሱ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

ስም ዓለሙ ካሣዬ ፊርማ [signature] ቀን 23/10/1999ዓ.ም